የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES'REPRESENTATIVES OF THE FDRE

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሴት ተመራጮች ኮከስ

2013 ዓ.ም





# ማውጫ


የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈጉባኤ መልእክት 4

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሴት ተመራጮች ኮከስ ሊቀመንበር መልእክት 5

ስለ ኮከሱ አጠቃላይ እይታ 6

- መግቢያ 6
- ኃላፊነቶች 6
- ራዕይ 6
- ተልዕኮ 7
- እሴቶች 7
- አደረጃጀትና የስብሰባ ጊዜ 7
- የኮከሱ መዋቅር 7

ታሪካዊ እይታ 8

- አመሰራረት 8
- የተከናወኑ ተግባራት እና የተገኙ ውጤቶች 10
- ተግዳሮቶች 10

ከመጀመሪያዋ ሴት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈጉባኤ ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ 12

አቅም ግንባታ 19

- ውትወታ/ተሟጋችነት 23

ሕግ ማውጣት እና ክትትል 28

- ሕግ ማውጣት 28
- ክትትል 29
- የምርጫ አካባቢ ማህበረሰብ ውክልና እና ተጠያቂነት 31
- በጎ አድራጎት እና ማህበራዊ ኃላፊት 32
- ትስስሮችን መፍጠር 33
- ከክልል ኮከስ ጋራ ያለ ትስስር 33
- ከወንድ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ጋር አጋርነት 34
- ኮከሱ በወንድ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ዕይታ 35

የመጪ ጊዜ ዕቅድ 39

- ተደራሽነትን ማስፋት እና ተጠያቂነትን ማጠናከር 40
- የአቅም ግንባታ ስራን ማጠናከር 41

አባሪዎች 42

- አባሪ 1. የቃላት መፍቻ 42
- አባሪ 2. የፎቶ ትውስታ 44
- አባሪ 3. መድረኮቻችን፡ መረጃዎች 45

# የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈጉባኤ መልእክት

# የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሴት ተመራጮች ኮከስ ሊቀመንበር መልእክት

# ስለ ኮከሱ አጠቃላይ እይታ

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዴ.ሪ) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 547 መቀመጫዎች ሲኖሩት ከእነዚህ መቀመጫዎች ውስጥ ሴቶች 212 (38.8 በመቶ) መቀመጫዎችን ይይዛሉ። በተለያዩ ሀገራት በምርጫ ወቅት በቂ ድምጽ ያገኙ ሴቶች ምክር ቤት ከገቡ በኋላ በፖለቲካ ተሳታፊነትና አመራር ሂደት ውስጥ እኩል ተሳታፊ እንዲሆኑና ብቃታቸውን ለማሳደግ ከሚወሰዱ እርምጃዎች ውስጥ የመጀመሪያው የሴቶች ኮከስ አደረጃጀትን ማቋቋም ነው። ይህን በመገንዘብ አሁን ያሉና ቀድሞ የነበሩ ሴት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተመራጮች የሴቶች ኮከስ አቋቁመዋል። ይህ የሴት የምክር ቤት አባላት ኮከስ የሴቶችን እኩል ተሳታፊነትና ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ ራዕይ ሰንቆ በ1998 ዓ.ም በይፋ ተቋቋመ። ኮከሱ ሥርዓተ-ፆታን ያማከለ ሕግ እንዲወጣና የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ትኩረት እንዲያገኝ የሚተጉ ወንዶችንም ተባባሪ አባላት አድርጎ አቅፏል። ኮከሱ በሴቶች ጉዳይ ላይ ይመክራል። እንዲሁም ማንኛውም በምክር ቤቱ የሚወጣ ሕግ የሴቶችን ጉዳይ ያገናዘበና ሁለንተናዊ እኩል ተሳታፊነትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸውን የሚያረጋግጥ ሆኖ መውጣቱን ይከታተላል። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ተገቢውን ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ በማድረግ እንዲታረም ይሰራል።

የሴት የምክር ቤት አባላት ኮከስ ኃላፊነቶች የተለያዩ ተጠሪ ተቋማትን ከሚከታተለው፣ ዕቅድና አፈጻጸማቸውንም ከሚገመግመው ከሴቶች፣ ወጣቶች እና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ይለያል። ምንም እንኳ ኮከሱ አስፈጻሚ አካላትን በራሱ መድረክ ጠርቶ በቀጥታ ተጠያቂ የማድረግ ሥልጣን ባይኖረውም ዕቅዶችና የአፈጻጸም ሪፖርቶች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲቀርቡ በሥርዓተ-ፆታ መነጽር እንዲገመገሙ ያደርጋል። የጎላ ችግር በሚታይባቸው ተቋማት ላይ መንግስት አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ እንዲወስድ በቅንጅት ይሰራል። እንዲሁም ኮከሱ ስራዎቹንና መርሀ ግብሮቹን የሚመራበት የራሱ የሆነ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች አሉት። እነዚህም የኮከሱ መሰረቶች ሲሆኑ በቀጣይነትም የሚመራባቸው መርሆዎች በመሆን ያገለግላሉ።

## ኃላፊነቶች

- ሴቶችን ያላሳተፈ የሀገር ዕድገት ውጥን ሁሉ በእጅጉ የሚስተጓጎል መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ኮከሱ የሚከተሉት የስራ ኃላፊነቶች እንዲኖሩት ተደርጓል፡-
- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሴት አባላትንና ተባባሪ ወንድ አባላትን አቅም መገንባት፤
- በሕገ-መንግስቱና በተለያዩ ሕጎች ለሴቶች በተሰጡ መብቶች መሰረት በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች እኩል ተሳታፊነትንና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ ምክክር ማድረግ፤
- ማንኛውም በምክር ቤቱ የሚወጣ ሕግ የሴቶችን ጉዳይ ያገናዘበና ሁለንተናዊ እኩል ተሳታፊነትንና ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸውን የሚያረጋግጥ ሆኖ መውጣቱን መከታተል፤
- የአቅም ግንባታና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ማከናወን፤
- በሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ምክር ቤቶች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፤
- በየክልል ምክር ቤቶች የተመራጭ ሴቶች ኮከስ እንዲደራጅ ማድረግ፣ ከክልል ምክር ቤቶች ሴቶች ኮከስ ጋር የስራ ግንኙነት ማድረግ፣ ልምድ ማካፈል፣ መደገፍና አቅም መገንባት፤ እና
- የሁሉም ክልል እና ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት እስከ ቀበሌ የተመራጭ ሴቶች ኮከስ እንዲደራጅ የማድረግ ስራ መስራት።

## ራዕይ

ሥርዓተ-ፆታዊ እኩልነት የተረጋገጠበት ዲሞክራሲያዊና የበለፀገች ኢትዮጵያን ተገንብታ ማየት

## ተልዕኮ

- የሴት የምክር ቤት አባላትን አቅም ማሳደግና በዚያም አማካኝነት ሴቶችን የሚመለከቱ ሕገ-መንግስታዊ መብቶች እንዲሁም በምክር ቤቱ የሚጸድቁ ሕጎችና በመንግስታዊ አካላት በኩል የሚቀርቡ ዕቅዶች ሁሉ መከበራቸውን ማረጋገጥ
- የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ
- ሴት የምክር ቤት አባላት በሀገሪቱ ላሉ ሴቶች አርአያ ለመሆን የሚያበቃቸውን ማንነት መገንባት

## እሴቶች

- ሥርዓተ-ፆታዊ እኩልነትን ማረጋገጥ
- የሥነ-ምግባር ደንብን ማክበር
- ብቃትና ጥራት ያለው የስራ ባሕል እንዲጎለብት ማድረግ
- ኤች አይ ቪ/ ኤድስን መዋጋት

## አደረጃጀትና የስብሰባ ጊዜ

ኮከሱ የተለያዩ ኮሚቴዎች፣ የስራ ቡድኖችና ስራ አስፈጻሚ አሉት። እያንዳንዱ የስራ ክፍል የራሱ የስራ ድርሻ ያለው ሲሆን ለኮከሱ ተልዕኮዎች መሳካት አስተዋጽኦ ያደርጋል። የኮከሱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰባት አባላትን የያዘ ሲሆን ሁለቱ ከምክር ቤቱ የሴቶች፣ ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና ከምክር ቤቱ ሴቶች ዳይሬክቶሬት በቀጥታ የሚሳተፉ ነገር ግን ድምጽ የማይሰጡ ናቸው። በጉባኤ የተመረጡ አምስት ስራ አስፈፃሚ አባላት ሲኖሩት በተጨማሪም ከአባላት የተመረጡ እያንዳንዱ አምስት የምክር ቤት አባላትን የያዘ የአቅም ግንባታ ዘርፍና የሕዝብ ግኑኝነት ዘርፍ ኮሚቴዎች አሉት። ስራ አስፈፃሚው በዕቅዱ መሰረት በ15 ቀናት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፤ በወር አንድ ጊዜ ከኮከሱ አቅም ግንባታና ሕዝብ ግንኙነት ዘርፎች (ንዑስ ኮሚቴዎች) ጋር ውይይት ያደርጋል። በስድስት ወራት አንድ ጊዜ ጠቅላላ ጉባኤ ያካሂዳል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አስቸኳይ ስብሰባ ይደረጋል።

## የኮከሱ መዋቅር



# ታሪካዊ እዩታ

### አመሰራረት

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሴት አባላት ኮከስ በ1997 ዓ.ም በሁለተኛው ዙር የምክር ቤት ዘመን ተጠነሰሰ። በሶስተኛው ዙር የምክር ቤት የስራ ዘመን (1998-2002 ዓ.ም) መጨረሻ አካባቢ ኮከሱ ተጠናክሮ በተወካዮች ምክር ቤት በአሁኑ የሴቶች፣ ወጣቶች እና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኩል እንደገና ተጠናክሮ ተቋቁሟል። በሶስተኛው የምክር ቤት ዘመን መገባደጃ ላይ ይበልጥ እንዲደራጅና የራሱ ደንብና ስያሜ ወጥቶለት ሰባት ስራ አስፈፃሚና የበላይ ጠባቂ እንዲኖረው ተደረገ። ኮከሱ ሲመሰረት 117 ሴት አባላት ነበሩት። ኮከሱ በአሁኑ ወቅት 212 ሴቶችና 168 ወንድ ተባባሪ አባላት ያሉት ሲሆን የቀድሞ አባል የነበሩትንም በክብር አባላትነት አካቶ ይዟል። የቀድሞ አባላት የአባልነት መብታቸው የተጠበቀ ነው::

ከኮከሱ መስራች አባላት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል ፡-

**የኮከሱ የበላይ ጠባቂ**

የቀድሞ ቀዳማዊ እመቤት የተከበሩ ወ/ሮ አዜብ መስፍን

**የኮከሱ ስራ አስፈጻሚዎች፡-**

የተከበሩ ወ/ሮ ነፃነት አስፋው

የተከበሩ ወ/ሮ ጊፍቲ አባሲያ

የተከበሩ መሰለች ወዳጀ (የኮከሱ ጸሀፊ)

በተጨማሪም አራት ንዑሳን ኮሚቴዎች ነበሩ። እነዚህም፡- አቅም ግንባታ፣ የሕዝብ ግንኙነት፣ ኦዲት፣ የተሞክሮ እና ፈንድ አፈላላጊ የሚባሉ ሲሆኑ እያንዳንዱ ንዑሳን ኮሚቴ አምስት አባላት፣ ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ ነበራቸው። በአራተኛው ዙር የምክር ቤት ዘመን (2003-2007 ዓ.ም) ደግሞ የተከበሩ ወ/ሮ ሮማን ገ/ስላሴ እና ሌሎችም ስራ አሰፈጻሚ ሆነው ተመርጠው የኮከሱን ስራ ሲሰሩ ነበር።

የሴቶች ጉዳይ የጋራ ጉዳይ ስለሆነ የተለያየ የፖለቲካ አቋም ያላቸው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሴት አባላት ለምሳሌ የተከበሩ ዶክተር ሙሉዓለም ታረቀኝን ጨምሮ ሌሎች የተፎካካሪ ፓርቲው የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አባል የነበሩ ሴቶችም ሁላችንም የሴቶች ጉዳይ ያገባናል በማለት የኮከሱ አባል ነበሩ:: የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አባል የተከበሩ ዶክተር ሙሉአለም በነበሩበት አጭር የስራ ዘመን የኮከሱ ስራ አስፈፃሚ አባል ሆነው በምክትል ሊቀመንበርነት ሰርተዋል::

በሶስተኛው ዙር የምክር ቤት ዘመን (1998 -2002 ዓ.ም) መጨረሻ አካባቢ ኮከሱ ወንድ የምክር ቤት አባላትንም ተባባሪ አባል አድርጓል። የወንድ ተባባሪ አባላት ቁጥር እያደገ መጥቶ ባሁኑ ወቅት 168 ደርሷል። በሶስተኛው ዙር ሀምሌ ወር ላይ ምክር ቤት ሲዘጋ የወንድ ተባባሪ አባላት በየምርጫ ክልሉ የሚሰሩትን የተለያዩ መረጃዎችን በመጠይቅ አስሞልተው ማምጣትን ጨምሮ የኮከሱን ስራዎች ሰርተዋል። በወቅቱ የወንድ ተባባሪ አባላት ከኮከሱ አባላት ጋር በመሆን በየምርጫ ክልሉ ሄደው በመጠይቅ በመታገዝ ያመጡት መረጃ የሚያካትተው፡- ሕገ-መንግስቱን ከመተግበር አንጻር ያሉ የሴቶች ችግሮች ምንድን ናቸው? የጤና ተቋማት ለሴቶች ያላቸው ተደራሽነት ምን ይመስላል? ምን ያህል አንቡላንስ አለ? የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ደረጃ ምን ያህል ነው? ታችኛው አደረጃጀት ድረስ በቀበሌ ካቢኔ ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ ምን ያህል ነው? የፖለቲካ ውሳኔ ሰጪነት ላይ ምን ያህል ተሳትፎ ያደርጋሉ? ወዘተ. የሚሉ መረጃዎችን ነበር።

ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ የክልል ፎረም በሚል ስያሜ ኮከሶች በየክልሉ ተመሰረቱ። አንዳንድ ክልሎች ፈጥነው ስራ የጀመሩ ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ ለመደራጀት ጊዜ ወስዶባቸው ነበር። ኮከሱ የሴት ካቢኔዎችን ሰብስቦ በየክልሉ ስልጠና በመስጠትና ከክልል ፎረሞች ለቀጣይ ስራዎቹ ግብአት በመውሰድ እንቅስቃሴውን ቀጠለ። ኮከሱ በመጀመሪያ ስልጠና የሰጠው በውሳኔ ሰጪነት ሂደት፣ ሕገ- መንግስቱ ስለሴቶች መብት ምን ይላል በሚሉ እና የሰልጣኞችን አቅም ሊገነቡ በሚችሉና ግንዛቤ በሚያስጨብጡ የተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ነበር።

የስልጠናውን ሂደት አሰመልክቶ የተከበሩ ወ/ሪት አንችናሉ ይግዛው ተፈሪ የቀድሞ ምክር ቤት አባል እና የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ የነበሩ/አሁን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽህፈት ቤት የፖሊሲ ጉዳዮች ጥናትና ምርምር ቡድን መሪ የሚከተለውን ብለዋል፡-

“በመጀመሪያው ዙር የኮከሱ አባላት ይዘውት የመጡት አጠቃላይ መረጃ ነበር። በቀጣዩ ሁለተኛ ዙር ላይ መረጃው እየተሻሻለ ዝርዝር እየሆነ ሄደ:: በመጀመሪያ ጥናት መሰረት ሴቶች በየእርከኑ መወከላቸው ከታወቀ በኋላ በፖለቲካ ውሳኔ ሰጭነት ላይ ያሉ ሴቶች ተወካይ በማስጠራት በየክልሉ ስልጠና ሰጠን፡: ክረምት ላይ የየክልል ሴቶችን ስልጠና ስንጠራቸው ለምሳሌ አማራ ክልል ከሄዱት ውስጥ አንዷ እኔ ነበርኩ። ያኔ የምክር ቤቱ የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ነበርኩ። የክልል ምክር ቤት አባላትና ስራ አስፈፃሚ የሴት ካቢኔዎችን ባህርዳር ላይ ስልጠና ሰጠን። በሁሉም ክልል ነው የሰራነው። ከእነሱ ደግሞ ያገኘነውን መረጃ ለወደፊት ስራችን ግብአት እንዲሆን አስሞልተን መጣን።” **(የተከበሩ ወ/ሪት አንችናሉ ይግዛው ተፈሪ)**

ኮከሱ አቅሙን እያጠናከረ ሲሄድ ከሌሎች ሀገራት የሴት የምክር ቤት ኮከሶች አባላት ጋር ተሞክሮዎችን ለመቅሰም እድሎችን ማመቻቸት ችሏል። ከእነዚህም ሀገራት መካከል ሱዳን፣ ኬንያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ቱኒዚያ፣ ሴኔጋል፣ ሩዋንዳ፣ ህንድና ቻይና ይገኙበታል።

## የተከናወኑ ተግባራት እና የተገኙ ውጤቶች

ከምስረታው ጀምሮ ኮከሱ በራሱና ከተለያዩ አጋር ደርጅቶች ጋር በመተባበር የረጅምና አጭር ጊዜ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎችን ለአባላቱና ለተባባሪ አባላቱ መስጠቱ ውጤት ካስመዘገበባቸው ስራዎች መካከል ዋነኛው ነው። በእነዚህ ስልጠናዎች ሴት የምክር ቤት ተመራጮችን አቅም ከመገንባት በተጨማሪ ወንድ የምክር ቤት ተመራጮችን ስለ ሥርዓተ-ፆታ ግንዛቤ ማስጨበጥ በመቻሉ በሴቶች መብት ጉዳይ ላይ ወንድ የምክር ቤት ተመራጮች በብርቱ ድምፃቸውን የሚያሰሙበት ዘመን ላይ ተደርሷል።

በኢትዮጵያ ታሪክ ኮከሱ አሻራ ያስቀመጠበትና ትልቅ እውቅና ያገኘበት የውትውታ/የተሚጋችነት ስራው ሴት የምክር ቤት አባላት በቁጥር እንዲበዙና የሴቶች የፓለቲካ ተሳትፎ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲጨምር ማድረጉ ነው። በተለይም ከአራተኛው ዙር የምክር ቤት ዘመን (2003-2007 ዓ.ም) እስከ አምስተኛው ዙር የምክር ቤት ዘመን (2008-2012 ዓ.ም) ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ ኮከሱ በምክር ቤቱ ሊኖር የሚገባውን የሴቶች ኮታ 40 በመቶ እንዲሆን ግብ አስቀምጦ የሴቶች አባላት ቁጥር ከ 27.8 በመቶ ወደ 38.8 በመቶ እንዲያድግ ያደረገው በገዢው ፓርቲና በአጋር ድርጅቶቹ መካካል ብርቱ የማሳመን ስራ በመስራቱ ነው። የተለያዩ የሲቪል ማህበረሰብ አካላትና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች በሀገሪቱ ውስጥ የሴቶች የፓለቲካ ተሳትፎ እንዲጨምር የሰሩት ስራም ለዚህ ውጤት አስተዋጽኦ በማበርከቱ እውቅና ያሻዋል።

ሴት የምክር ቤት አባላትን ወደ ምክር ቤቱ አመራር እንዲመጡ ማስቻልና በዚህም የቋሚ ኮሚቴዎችን 60 በመቶ በሴት የምክር ቤት አባላት እንዲመሩ ማስቻል ሌላው ኮከሱ የሴቶች የፓለቲካ ተሳትፎና ውሳኔ ሰጪነት እንዲጎለብት ያበረከተው አስተዋጽኦ ነው።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 55 መሰረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ማውጣት፣ የወጡት ሕጎች ተግባራዊና ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ ዋነኛው ስልጣኑና ተግባሩ ሲሆን ኮከሱ በሀገሪቱ ውስጥ የሚቀረጹትና የሚተገበሩት ሕጎችና ፖሊሲዎች ለሥርዓተ-ፆታ በጎ ምላሽ ማድረጋቸውን ይከታተላል። የኮከሱ አባላት ከአስፈጻሚ አካላት የሚቀርቡላቸውን ዕቅዶችና የአፈጻጸም ዘገባዎች እየገመገሙ ተጠያቂነትን እንዲፈጥሩ አባላቱን በማብቃትና እነዚሁ ዕቅዶችና ሪፖርቶች የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ አማክለው ከወጡ ሕጎችና ፖሊሲዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን እንዲከታተሉ ያደርጋል።

## ተግዳሮቶች

ከምስረታው ጀምሮ እስካሁን ድረስ ኮከሱ የተለያዩ ተግዳሮቶችን ተጋፍጧል። ኮከሱን ለመመስረት ካጋጠሙ ችግሮች መካከል የኮከሱ አስፈላጊነት ላይ ጥያቄ ማንሳትና የአመለካከት ተግዳሮቶች ይገኙበታል።

"'ከአሁን በፊት መንግስት ለሴቶች እየሰራ ነው፤ እናንተም ሴት ሆናችሁ በምክር ቤት በኮሚቴ እየሰራችሁ ነው፤ ተጨማሪ አደረጃጀት ምን ያስፈልጋል' የሚል የአመለካከት ዝንፈት ነበር። ይህም ከወንዶች የምክር ቤት አባላት ብቻ ሳይሆን የምክር ቤት ተመራጭ ሴቶችም እራሳቸው 'ይህ ጊዜ የተመደበለት ስራ ስላልሆነ ጊዜ በተመደበለት በታ አድምተን ከሰራን የሴቶችን ተጠቃሚነት ልናረጋግጥ እንችላለን' የሚል አመለካከት ነበራቸው። በኋላ በእነሱ አመለካካት ላይ ረጅም ጊዜ ተሰርቶ፤ ግለሰባዊ ግምገማም ጭምር ከተደረጉ በኋላ አመለካከቶቻቸውን አስተካክለው አሁን ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ ወንዶችም የኛ ደጋፊዎች መሆን ችለዋልው።" **(የተከበሩ ወ/ሮ ፋንታዬ ባቡሎ፣ የምክር ቤት አባል፣ የኮከስ ጸሀፊ)**

ኮከሱ ከተመሰረተም በኋላ የሰዎች ተሟልቶ ካለመገኘት ባሻገር የበጀት ምንጭም አልነበረውም። ስለሆነም አባላቱ በየወሩ ከደሞዛቸው 10 ብር ተባባሪ ወንድ አባላት ደግሞ 5 ብር ያዋጡ ነበር። በተጨማሪም ኮከሱ ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር እና የሚያስፈልገውን ገቢ በማፈላለግ እስከ 2008 ዓ.ም ድረሰ ስራውን ቀጠለ። በ 2008 ዓ.ም የምክር ቤቱ የአሰራርና የአባላት የሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር

6/2008 ሲወጣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሴት ተመራጮች የኮከስ አደረጃጀት በስም ተጠቅሶ ከምክር ቤቱ አደረጃጀት ቋሚ ኮሚቴዎች ጋር እኩል የሆነ የሕግ አካል ሆኖ የተቋቋመ ሲሆን የራሱ የሆነ የመንግስት በጀትም እንዲኖረው ተደርጓል። ኮከሱ እውቅና በማግኘቱ ምንም እንኳን ቋሚ በጀት ኖሮት በዕቅዱ መሰረት ተከታታይ የሆኑ ስራዎችን ማከናወን ቢችልም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ መሆኑ እራሱን ችሎ እንዳይንቀሳቀስ ነፃነቱን ሊሸረሽር ይችላል የሚል ስጋት ያላቸው አንዳንድ አባላት አሉ። **(የተከበሩ ወ/ሮ ናፈቁሽ ደሴ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የበጀት እና ፕላን ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ የኮከስ ስራ አስፈጻሚ)**

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ለኮከሱ የተመደበለት ቢሮ ከምክር ቤት ጽህፈት ቤት ቅጥር ግቢ ራቅ በማለቱና ጠባብ በመሆኑ ለስራ ቅልጥፍና ምቹ አልነበረም። ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ግን ኮከሱ አዲስ ቢሮ አግኝቶና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተ.መ.ድ) የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትና ሴቶችን የማብቃት ክፍል (ዩ ኤን ውመን) እና የተባበሩት መንግሥታት የልማት መርሀ ግብር (ዩ ኤን ዲ ፒ) አጋር ድርጅቶች ድጋፍ የቢሮ ቁሳቁስና ኮምፒውተር አሟልቶ እየሰራ ይገኛል።

የኮከሱን ተግባራት ለማከናወን የተመደበ የስራ ሰዓት ስለሌለና የተመረጡት የኮከስ ስራ አስፈፃሚ አመራሮች ከፍተኛ የስራ ጫና ስላለባቸው ካላቸው የመደበኛ ስራ በተደራቢ የእረፍት ጊዜአቸውን ተጠቅመው ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በምሳ ሰአታቸው ስራቸውን ያከናውናሉ። ስለዚህም በስራ መደራረብና ከጊዜ ጥበት የተነሳ ከኮከሱ ራዕይ አንጻር ማቀድና ሰፊ ስራ መስራት አለመቻል ትልቁ ተግዳሮት ሆኖ ቆይቷል። ለምሳሌ ተከታታይነትና ቀጣይነት ባለው መልኩ የአቅም ግንባታ ድጋፉ ምን ውጤት አመጣ የሚለውን ለመከታተልና ለመመዘን ሳይቻል ስልጠናዎች ሲያካሄዱ ቆይተዋል። ኮከሱ ይህን ችግር ለመቅረፍ እንዲረዳ አመራር የመቀየር ሀሳብ ተነስቶ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ከፍተኛ አመራር ኃላፊነት የሌለባቸውና የስራ ጫና የማይበዛባቸው ስራ አስፈፃሚ አመራሮችን ማስመረጥ ጀምሯል።

“አንዲት ሴት የምክር ቤት ተመራጭ የአንድ ኮሚቴ አባል ከሆነች የኮሚቴዋን ስራ ነው የምትሰራው። ምክር ቤቱ ኮከሱ ሴቶች ላይ እንደሚሰራ እምነቱ ኖሮት የምክር ቤቱ ደምብ ውስጥ እንዳስገባ ሁሉ፤ ሰብሳቢ፣ ምክትል ጸሀፊ፣ ቢያንስ አንድ ሶስት ስራ አስፈፃሚዎች ከምክር ቤቱ ተደራቢ ስራ ማለትም የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኃላፊነት ውጭ አድርጎ የኮከሱን ስራ እንዲሰራ አድርጎ በጀት አስቀምጦ ቢሆን በደንብ መስራት ይቻላል። ቀደም ሲል ፋይሉን ተሸክመን ነው ስንሰራ የነበረው። ቢሮ ፋይል ‘ቦክስ’ እንኳን አልነበረንም። መጀመሪያ ያገኘነው ቢሮ ሩቅ ነበር እኛ በተገኘችው በትርፍ ሰዓት ስንሰራ ስለነበር በተገኘችው ትርፍ ጊዜ ወደዚያ እየሄድን መጠቀም አልቻልንም። ክብርት ወ/ሮ ሽታዬ ሰብሳቢ በነበሩ ጊዜ ከሳቸው ቢሮ አንድ ካቢኔ ያስቀምጡ ነበር። ለመሰባሰብ ክፍት ቦታ እየፈለግን አንዳንዴ ወ/ሮ ሽታየ ቢሮ ነበር የምንሰራው። የተሰጠን ቢሮ ምክር ቤቱ ከሚገኝበት ቅጥር ግቢ ውጭ በመሆኑ እዛ ድረስ ስንሄድ ያስቀመጥነው ሰዓት ያልቃል፤ ስለዚህ ባገኘነው ቦታ እንሰባሰባለን።” **(የተከበሩ ፋንታዬ ባቡሎ)**

ብዙ ሴት የምክር ቤት አባላት ሴት በመሆናቸው ብቻ ከሚሰሩት የሙያ ስራ በተጨማሪ ልዩ ተግዳሮት አለባቸው። ሴቶች በተፈጥሮ የማርገዝ፣ የመውለድ እና ጡት የማጥባት ኃላፊነት አለባቸው። በማህበረሰቡ ደግሞ የሚጠበቅባቸውን የቤት ውስጥ ስራን የመስራት፣ ቤተሰብ የመንከባከብ ብሎም በማህበራዊ ህይወት ውስጥ አገልግሎት የመስጠት ሚናን መጫወት ያሉ ተደራራቢ ኃላፊነቶችን ይሸከማሉ። ስለዚህ ሴት የምክር ቤት አባላት ከወንዶች የበለጠ ጫና ተቋቁመው ስራቸውን ያከናውናሉ።

“ሴት የምክር ቤት አባላት ከወንድ አባላት በተለየ መልኩ ከቤት ውስጥ ኃላፊነቶች ባሻገር የምክር ቤቱን ተልዕኮ በኃላፊነት የመወጣት ድርብርብ ኃላፊነት አለብን። ከሌላ የስራ መስክ ወይም መስሪያ ቤት በተለየ መልኩ ምክር ቤቱ አምስት ደቂቃ አሳልፈሽ እንድትመጪ አይፈቅድም። አጀንዳውን አስቀድመሽ አንብበሽና ተዘጋጅተሽበት አፈጉባኤው ወደ ጉባኤው ከመግባታቸው በፊት አስቀድመሽ ሥፍራሽን መያዝ አለብሽ። ‘ልጄን ትምህርት ቤት ሳደርስ ረፈደብኝ’ ወይም ‘ሆስፒታል አድርሼ መጣሁ’ የሚለው ምክንያት ተቀባይነት የለውም። ስለዚህ ቢያንስ ቢያንስ በሰዓት አጠቃቀምና ፕሮቶኮል አተገባበር ዙሪያ ራስን በዲሲፕሊን ማነጽ ይኖርብሻል። አንዴ ሴት ልጄ ስምንት አመቷ ላይ

ስትጫወት ከዛፍ ስትንጠላጠል ወድቃ እግሯ ተተርትሮ በሌለሁበት ወስደው አሰፏት። ማታ ከስራ ስመጣ በጣም አዘንኩ፤ እንደገና በጠዋቱ ስራ መሄድ ስለነበረብኝ ባለቤቴ ሆስቲታል ወሰዳት። በጣም ነው ወንጀለኝነት የተሰማኝ። ለልጆቼ የምሳ ዕቃ ለትምህርት ቤት በምቋጥርበት ዘመን ማታ ገብቼ ለነገ የሚመገቡትን እስከ ምሽቱ አምስት ሰዓት የማበስልበት ጊዜም ነበር።” **(የተከበሩ ወ/ሮ አበባዬ ገዛኸኝ፣ የአካባቢ ጥበቃ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልና የኮከስ ሰብሳቢ)**

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ከ400 በላይ ሰራተኞች ያሉት ቢሆንም እስከዛሬ ድረስ ኮከሱ አንድም መደበኛ የቢሮ ሰራተኛ ኖሮት አያውቅም። ኮከሱ መደበኛ ባለሙያ ቢኖረው የስራ ጫና ከመቀነስና የመረጃ ቅብብል ክፍተት ከማስወገድ ባሻገር በኮከሱ ራዕይና ዕቅድ መሰረት ተከታታይና ቀጣይ የሆኑ ስራዎችን ለማከናወን ይረዳል በማለት ኮከሱ ይህን ለማሳካት እየሰራ ይገኛል።

## ከመጀመሪያዋ ሴት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈጉባኤ ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ

**የተከበሩ ወ/ሮ ሽታዬ ምናለ ለረጅም ጊዜ ያገለገሉና የመጀመሪያዋ ሴት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈጉባኤ ናቸው።**

**ኮከሱ የተመሰረተበት ዋና ዓላማ ምን ነበር?**

እንደሚታወቀው ባለፉት የፓርላማ ዘመናት በፓርላማ ውስጥ የሴቶች ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነበር። በሁለተኛው የፓርላማ ዘመን በፓርላማ ውስጥ የነበሩ ሴቶች ቁጥር 42 (13 በመቶ) የደረሰ ሲሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቶ አሁን 38.8 በመቶ ደርሷል። ይህም ባለፉት ጊዚያት ከነበረው በቁጥርም በትምህርት ደረጃም የተሻሉ የሚባሉ ሴቶች ወደ ፓርላማ የመጡበት ጊዜ ነበር። ኮከሱ የተመሰረተበት ምክንያትም ሴቶች አንድ ላይ ሆነን የምንመክርበት የምንነጋገርበት በዋናነት ደግሞ የራሳችንን አቅም ጨምር ልንገነባበት የምንችልበትን መድረክ ለምን አንፈጥርም ብለን ተነጋገርን። የራሳችንን መድረክ ብንፈጥር አንዳችን ላንዳችን እንተጋገዛለን፤ የበለጠ በግልጽ እናወራለን፤ ክፍተቶቻችንን እርስ በርስ መሙላት እንችላለን፤ በይበልጥ ደግሞ ብዛት ባላቸው ወንዶች ድምፃችን እንዳይዋጥ ይረዳናል ብለንም አሰብን። ስብስባችን ከተለያየ ሙያ፣ ከተለያየ አካባቢና ልምድ እንደመሆኑ መጠን አንዳችን ከአንዳችን የተሻለ ነገር ሊኖረን ይችላል፤ ይህንንም እንደ መልካም አጋጣሚ ብንጠቀምበት ከራሳችን አልፎ የሌሎችንም ሴቶች ችግር ልንፈታ እንደምንችልና አባላቱም በተለያየ ዘርፍ ውስጥ የምንገኝ በመሆናችን በየዘርፉ ያሉ ችግሮችንና መልካም ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥና መረጃ ለማግኘት ትልቅ አቅም እንደሚሆነን አምነን ነበር ኮከሱን የመሰረትነው። በዋናነት ግን የዚህ ኮከስ ዓላማው የሴቶችን አቅም መገንባት ነው። እያንዳንዳችን በምንሰራቸው ስራዎች፣ በሚኖረን የመሪነት ኃላፊነት ላይ ሆነ በየቋሚ ኮሚቴዎች ለምናደርገው ውይይት መድረኩ የሚፈቅደውን አቅም በመገንባት ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ እንዲኖረን ማድረግ ነው ዓላማው። ከተመሰረተ በኋላ መጀመሪያ ያደረግነው “ምንድንነው የምንሰራው” የሚለውን ማወቅ ነበር:: ሰለተለያዩ ሀገራት ኮከሶች መረጃ የፓርላማው ጽህፈት ቤት እንዲሰበስብልን አደረግን። “እንዲህ ዓይነት አደረጃጀትስ ተቀባይነትና ሕጋዊነት አለው ወይ” የሚለውን ማጥናት ጀመርን። እንዲህ እንደ አሁኑ መረጃ በቀላሉ የሚገኝበት ጊዜ ባይሆንም እንኳን የቻልነውን ሁሉ በማድረግ መግባባትና እርስ በርስ መደጋገፍ ታክሎበት ስራችንን ጀመርን።

**በወቅቱ በኮከስ አማካኝነት የእናንተ እርስ በርስ መረዳዳት ምን አስተዋጽኦ አበረከተ ብለው ያስባሉ?**

ቋሚ ኮሚቴ ስትሆኚ የኮሚቴ ስራሽን ሰርተሽ ከዚያ ውጭ ወደ ራስሽ ጉዳይ ነው የምትሄጂው። መደበኛ ስብሰባ ሲካሄድም 547 ሰው ባለበት ትገኛለሽ። የሚቀርበውን ርዕሰ ጉዳይ አድምጠሽ ሀሳብ ካለሽ ሀሳብሽን ሰንዝረሽ ትወጫለሽ። እርስ በርሳችን የመተዋወቅ እድልም በጣም ዝቅተኛ ነበር። በፓርላማው ውስጥ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ሙሉ ለሙሉ ላታውቂ ትችያለሽ።
ለምሳሌ አንድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሪፖርት የሚያቀርብ ቢሆን መረጃው የሚደርስሽ ያ ሪፖርት ሊቀርብ ሁለት ቀን ሲቀረውው ሊሆን ይችላልው። በአምስተኛው ዙር ፓርላማ እንደውም የመረጃ ልውውጡ ከወረቀት ስራ ወጥቶ ግንኙነታችንን ዘመናዊ ለማድረግ ተችሏል። ሁሉም ሰው በእጅ የሚያዝ አነስተኛ ተንቀሳቃሽ ኮምፒውተር (ታብሌት) አለው። አዳዲስ መረጃዎች ሲኖሩ ባጭሩ ይገለጽልሻል። በቀደመው ጊዜ ምን አልባት ስብሰባ መኖሩን ቦርድ ላይ ተለጥፎ ሳታነቢ ልትሄጂና ሊያመልጥሽ ይችላል። የግንኙነት መንገዱ በጣም ዝግ ያለ ስለሆነ የራስሽ ቅልጥፍና ታክሎበት ይህን ባደርግ ለስራዬ ጥሩ ነው ብለሽ ማሰብ ካልቻልሽ ብዙ ነገር ሊያመልጥሽ ይችላል። የፓርላማ መደበኛ ስብሰባ የሚካሄደው ሁሌም ማክሰኞና ሀሙስ ነው። የኮሚቴ ስራ ውስጥ ከሌለሽ እነዚህን ስብሰባዎች ብቻ እየተካፈልሽ ወደ ቤትሽ ልትሄጂ ትችያለሽ። በርግጥ አሁን ሁሉም በየኮሚቴ ውስጥ አለ እንጂ ባብዛኛው ብዙ መረጃ ላታገኚ ትችያለሽ። ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት መረጃዎችን ለመለዋወጥ ኮከሱ በጣም ይጠቅመናል።

**ኮከሱ ከመመስረቱ በፊት ምንም ዓይነት የግንኙነት መንገድ አልነበራችሁም?**

አልነበረንም።

**ስለዚህ ይህ የመጀመርያችሁ ነበር ማለት ነው?**

አዎ። ከዚያ ሰብሰብ ብለን እያንዳንዳችን ይዘን የመጣነውን ልምዳችንን መጠያየቅ ጀመርን። ዕቅድም ለመስራት ሞከርን። በወቅቱ እንደውም እኔ አንድ ንዑስ ኮሚቴ እሰበስብ ነበር። አምስት ስራ አስፈፃሚዎች ነበሩ። አሁንም እንደዚያው ነው የቀጠለው። ኮሚቴዎች ግን ሁለትም፣ ሰስትም፣ አራትም ይሆናሉ። የምንጨምረውም የምንቀንሰውም እንደነበር አስታውሳለሁ።

**ኮከሱ ሲመሰረት በየትኛው ኮሚቴ ውስጥ ነበሩ?**

የኮከሱ የአቅም ግንባታ ኮሚቴ ሰብሳቢ ነበርኩ። በፓርላማው ውስጥ ደግሞ የመሰረተ ልማት ቋሚ ኮሚቴ አባል ነበርኩ።

**ወደ ኮከሱ ከገቡ በኋላ ነው እርስዎ የምክር ቤቱ ምክትል አፈጉባኤ ሆነው መስራት የጀመሩት?**

አዎ። ግን በኮከሱ አማካኝነት አልነበረም። በፖለቲካ ሹመት ነበር ቦታው የሚያዘው። ለምሳሌ ከደቡብ ክልል አምባሳደር ተሾመ ቶጋ አፈጉባኤ ሆነው ነበር። ከአማራ ክልል ደግሞ እኔ ምክትል አፈጉባኤነት ተመረጥኩኝ።

**በቋሚ ኮሚቴዎች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ እንዴት ነበር?**

የነበረው የኮሚቴ ቁጥር ትንሽ ከመሆኑ ባሻገር አንዳንዶች የትምህርት ዝግጅታቸው ዝቅተኛ ነበር። ወደ ኮሚቴ የሚገቡት ደግሞ የተሻለ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መሆን አለባቸው። ምክንያቱም ሕግ ሲወጣና ቁጥጥር ሲደረግ በደንብ አንብቦና ተረድቶ የሚሰራ ሰው ያስፈልጋል። በእርግጥ ሴቶችም ብቻ ሳይሆኑ ወንዶችም ሁሉም አይሳተፉም ነበር። አሁን ነው ሁሉንም ማሳተፍ የተጀመረው እንጂ ያኔ ውስን ሰው ነበር በቋሚ ኮሚቴ ውስጥ የሚሳተፈው።

**ቋሚ ኮሚቴ የሚመሩ ሴቶች ነበሩ?**

ያኔ በሁለተኛው የፓርላማ ዘመን (1993-1997 ዓ.ም) ሴት መሪ አልነበረም፤ ሴት አባላት ብቻ ነበሩ። አሁን ግን ከ10 ቋሚ ኮሚቴዎች ውስጥ 6ቱን (60 በመቶ) ሴቶች ይመራሉ።

**ኮከሱ ከተቋቋመ በኋላ በግል ምን ተጠቀምኩ ይላሉ?**

ዕቅዳችንን ለመተግበር ከሴቶች ጋር ተገናኝቶ ለመወያየት፣ የምታገኛቸውን ሀሳቦች ደግሞ ለስራ አስፈፃሚ ማቅረብ የሚያስችል እውቀት እንድናዳብር አድርጎናል። በሙሉ አቅም

እንድንቀሳቀስ ረድቶኛል። ሁላችንም ንግግር ለማድረግ እንፈራ ነበር። ወንዶችን እንደውም “የናንተ ተጽእኖ እኮ ነው ፈሪ ያደረገን” ስንላቸው “እኛም እኮ እንፈራለን ሰለማይታወቅ ነው እንጂ” ይሉን ነበር። ኮከሱ ውስጥ መሳተፍ ከጀመርን በኋላ ግን ፍርሀታችንን እያስወገድን የንግግር ልምድም እያዳበርን መጥተናል።

## ኮከሱ ከመመስረቱ በፊት የንግግር ልምድ አልነበራችሁም?

አልነበረንም። በትላልቅ መድረኮች ላይ ንግግር የማድረግ ልምዱ አልነበረንም። በጣም ነበር የምንፈራው:: እኔ ራሴ ተናገሪ ስባል ልቤ ይመታ ነበር። ጥሩ ነገር እያለሽ መግለጽ ግን አትችይም። እዚህ ከመምጣቴ በፊት አስተማሪ ነበርኩ። ግን ተማሪ ፊት መናገርና በእንደዚህ ዓይነት የፖለቲካ መድረክ ላይ መናገር ይለያያል። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ‘ካሪኩለም ኤንድ ኢንስትራክሽን’ የማስተር፣ በሳይኮሎጂ ደግሞ የመጀመሪያ ዲግሪ አለኝ። ይህ ከባድ ነበር። የተሻለ የትምህርት ደረጃ ስላለኝና ስለማነብ ጥሩ ሀሳብ ላነሳ እንደምችል አስባለሁ። ሆኖም ልክ ላልሆን እችላለሁ እያልኩ ልቤ ይመታል። የመናገር እድል ሳገኝ እንኳን መናገር የምፈልገውን ሁሉ ሳልናገር እጨርሳለሁ:: በኋላ ደግሞ እኔ እናገረዋለሁ ብዬ ድፍረት አጥቼ ሳልናገረው የተውኩትን ሰው ሲናገረው በጣም እናደዳለሁ:: ግን ልምምድ ስታደርጊና እንደዚህ ዓይነት ትንንሽ መድረኮች ከሴቶች ጋር ሲፈጠሩልሽ ይህ እየጠፋ ይሄዳል። ለእኔ ትልቅ ጉልበት የሆነኝ ኮከሱ ነው። በኮከሱ ውስጥ በድፍረት ነው የምትናገሪው:: እንደገና ደግሞ ሁሉም ከእኔ ጋር እኩል ናቸው ብለሽ ከምታስቢውና ከምታምኛቸው ሴቶች ጋር ስትሆኚ በራስ መተማመን ይሰማሻል። ሴቶች እርስ በርሳችን ቅርብ ነን፤ አሁን ወንድ ቃለ-መጠይቅ ብታደርጊ በዚህ ልክ ቅርብ አንሆንም። ቶሎ እንግባባለን። ለመማማርም ለመደጋገፍም እርስ በርሳችን ስንሆን የተሻለ እንቀራረባለን ብዬ አስባለሁ። እንደገና ጥሩ ነገር ሲኖርሽም ያበረታቱሻል። ወንዶቹ ግን ከነሱ እንደምትሻይ እያወቁ ሁሉ እውቅና አይሰጡሽም፤ ተገደው ካልሆነ በቀር።

## በእርሶ የስራ ዘመን ወንዶች ተገድደው ነው እውቅና የሰጡኝ ብለው የሚያስታውሱት ነገር አለ?

ለምሳሌ በፓርላማ ውስጥ እኔ ስብሰባውን ስመራ ዋናው አፈጉባኤ ሲመራ የማያደርጉትን ከስርዓት ውጭ የሆነ ባህርይ ያሳዩ ነበር። እሱ ወንድ ነውና ትክክል ነው ብለው ነው የሚያስቡት። ብዙም ሳይጠነቀቁ ዘና ብሎ መጠየቅ፣ የምትሰጭውን አቅጣጫ አለመቀበል ወይም አንዳንዴ እኔ አሁን ድምጽ ስሰማም ምን እየሆነ ነው ለማለት እሞክራለሁ፤ ወንዶች ጉርምርምታ ቢኖርም ይቀጥላሉ። እየለመድኩት ስሄድ ቢንጫጩም መቀጠል ነው፤ ግን ይረብሹሻል። በሕጉ መሰረት ሳይፈቀድ መናገር አይቻልም። ነገር ግን ፈቃድ ሳያገኙ መነጋገሪያውን አብርተው ይናገራሉ። አሁን ቀርቷል እንጂ እኔ ላይ ይበዛ ነበር። የመጀመርያው አካባቢ እንደውም ከባድ ከባድ እሰጥ-አገባ ያለበት አጀንዳ ላንቺ ይደርስሻል ይሉኛል።

## ኮከሱ ወንዶችን ተባባሪ አባላት አድርጓል፤ የወንዶች በተባባሪ አባልነት ኮከሱን መቀላቀላቸው ጠቀሜታ አለው?

ሴቶች በተናጥል እንዳንሰራ ወንድ ተባባሪ አባላት ለኮከሱ ደጋፊ በመሆን ኮከሱ ምን እየሰራ እንደሆነ በተለያዩ አካላት እንዲታወቅም ሊደግፉ ይችላሉ። ለምንሰራው ማንኛውም ስራ ሀሳብ ይሰጡናል። አጀንዳዎችን ወደ ፓርላማ ይዘን በምንሄድበት ጊዜም ከነሱ ጋርም ተወያይተንና ሀሳባችንን በደንብ አስረድተናቸው ስለምንሄድ አጋዥ ይኖረናል ማለት ነው። ዋናው ዓላማው ደግሞ እንደሚታወቀው በፓርላማ ውስጥ የሴቶች ቁጥር አነስተኛ ነው። የሶስተኛ ዙርን ስንመለከት የሴቶች ቁጥር 117 (21.9 በመቶ) ነበር ። አንድ አንድ ጊዜ ፓርላማው ውስጥ የምናቀርባቸውን ሀሳቦች በሙሉ በምንፈልገው መንገድ ማስወሰን አንችልም፤ ምክንያቱም ያው ፓርላማው የሚወስነው ባብላጫ ድምጽ ስለሆነ በዚህ ጊዜ ወንድ ተባባሪ አባላት ያግዙናል። ድምጽ ይሆኑልናል። ይህ ማለት የሴቶች ብቻ ሀሳብ አይሆንም፤ አጠቃላይ የፓርላማ ሀሳብ ይሆናል።

### ከመረጣችሁ ሕዝብ ጋር እንዴት ትገናኛላችሁ?

እኔ ተወክዬ የመጣሁት ከአማራ ክልል ነው። ተመርጬ የመጣሁትም በክልሉ ውስጥ ከምትገኝ ጎንጂ ቆለላ ወረዳ ነው። ወደ መጣሁበት ወረዳ በዓመት ሁለቴ እሄዳለሁ። ሁላችንም የፓርላማ ተወካዮች በዓመት ሁለቴ ወደ መረጠን ሕዝብ እንሄዳለን። ከህብረተሰቡ ጋርም እንወያያለን። ምን እንደሰራን ሪፖርት እናቀርባለን፤ የነሱንም ጥያቄዎች እንቀበላለን። "ይሰራል ያላችሁን መንገድ አልተሰራም፣ ይገባላችኋል ያላችሁን መብራትና ውሃ የታል" የሚሉትንና መሰል ጥያቄዎችን ህብረተሰቡ ይጠይቃል። በተሰሩት ላይ ምስጋናን ተቀብለን ባልሰራናቸው ላይ ደግሞ ተወቅሰን ያልተሰሩበትን ምክንያት አስረድተን እንመጣለን።

### ከመረጣችሁ ሕዝብ ጋር የሚኖራችሁ ውይይት ነፃነትና ግልፅነት የታከለበት ነው ብለው ያስባሉ?

አርሶ አደሮች የሚሰማቸውን በስርዓት ነው የሚያነሱት:: ከህብረተሰቡ የተነሱ ጥያቄዎችን መርጠሽ ደግሞ ፓርላማ የምታመጫቸው ይኖራሉ። ለምሳሌ በመብራት ጉዳይ የተነሱ ጥያቄዎች ተሰብስበው ለሚመለከተው አካል ይቀርባሉ። ትምህርት ጉዳይ ለትምህርት ሚኒስቴር ይላካል። ሆኖም ፓርላማው ስራ አስፈጻሚውን ተጠያቂ የምናደርግበት መንገድ ጠንካራ ባለመሆኑ በእርግጥ መልሱ ያን ያህል የሚያረካ አይደለም። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች የሚቀርቡ ሲሆን ለምሳሌ "መሬት ቆፍሬ ውሃ አልገኝ አለ፣ እያጠናሁ ነው" የሚሉ ምላሾች ይሰጣሉ።

### ተመልሳችሁ ስትሄዱ ሕዝብ ምን ይላችኋል?

እዚያ ለመሄድ ያሳቅቅሻል። ንዲሁ እየመጣቻሁ እያወራችሁን ትውላላችሁ እንጂ ምንም ነገር አኮ አይሰራም፤ ባትመጡ ይሻላል ሁሉ ይሉሻል፤ ከባድ ነው። አርሶ አደሩ የጎደለበትን፣ የሚፈልገውን ነው የሚጠይቅሽ። አንዳንድ ባለስልጣናት ደግሞ ከዐቅም በላይ የሆነ ነገር ቃል ገብተው ይመጣሉ፤ አርሶ አደሩም የተባለውን አስታውሶ እንዲህ እኮ ተብለን ነበር ለምን አይደረግልንም ይልሻል። ስለዚህ በጣም ከባድ ነው። ሁለት ሶስት ዙር በፓርላማ ውስጥ ከሰራሽ ትችገሪያለሽ። ጥሩ ነገር የተሰራ ጊዜ ደግሞ በዚያው ልክ ብን ብለሽ ነው የምትሄጀው። ለምሳሌ እኔ ተመርጬ በመጣሁባት ጎንጅ ቆለላ ወረዳ ከባህር ዳር 40 ኪሎ ሜትር አቋርጦ የሚመጣ ጎጃምና ጎንደርን የሚያቋርጥ ሰዎች ወገባቸውን ታስረው የአባይን ወንዝ የሚሻገሩበት ገደል ነበር። ህብረተሰቡ ሁሌም መንገዱ እንዲሰራለት ይጠይቅ ስለነበር እሱ መንገድ ባለፈው ዓመት ተሰርቶ ያለቀ ጊዜ በጣም ነበር የተደሰትኩት። እንደዚህ ዓይነት ስራዎች በጣም ያረኩሻል። ግን ሁሌም እንደሱ ላይሆንልሽ ይችላል። ብዙ ሴቶች በዚህ መንገድ ሲሻገሩ ሞተዋል። እርጉዝ ሴቶች ምጥ ተይዘው መሻገር ስላልቻሉ ብቻ ህይወታቸውን አጥተዋል፤ ህፃናት ሞተውበታል። አሁን ግን በተገጣጣሚ ብረት መሻገርያ ተሰርቶለት መኪናም ያልፋል። ሰዎችም በእግራቸው ይሻገሩበታል። ይህ ድልድይ ሲሰራ እንደተደሰትኩት በህይወቴ የተደሰትኩበት ጊዜ የለም። አሁን ድረሰ በጣም ነው የምደሰተው። ያም ሆኖ አርሶ አደሩ በቀጣይ ሌላ ጥያቄ ይኖረዋል። በአንድ ወቅት እኔ እርዳታ ጠይቄ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አሰርቼ ነበር። በጣም ተደሰተው ነበር፤ በቃ ከዚያ በኋላ ምንም የለም ብለሽ ስትሄጂ አሁን ደግሞ የቴክኒክ ትምህርት ቤት ብትሰሩልን ይሉሻል።

### ድልድዩ ሲሰራ የእርሶ ሚና ምንድን ነበር?

አንደኛ በታውን ድልድዩን በደንብ አይቸዋለሁ፤ ገመድ ታጥቄ እንደነሱ ለመሻገር ሞክሬያለሁ።

### እሞታለሁ ብለው አልፈሩም?

አልፈራሁም! እኔ ገጠር ነው ተወልጄ ያደግኩት። በእርግጥ እንደዚህ ዓይነት አይቼ አላውቅም፤ ግን ታጥቄ ተሻገርኩ፤ ልክ እንደ እነሱ። አርሶ አደሩ ሞራል ይሰጥሻል። እዚህ መጥቼ ከመንገዶች ባለስልጣን ጋር ብዙ ተነጋግሬያለሁ፤ ጎትጉቻለሁ። በሱ ብቻ አይሳካልሽም። በግል ነው ብዙ ስራ የሚሰራው። በጎን በማሳመን ነው እንጂ ምክር ቤት ላይ የምታነሻቸው ጥያቄዎች ለሕዝቡ ይሆናል የሚጠቅምሽ እንጂ ስራው ላይሰራልሽ ይችላል። በግልሽ ብዙ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብሻል:: እንደውም መንገዶች ባለስልጣን ድሮና ዘንድሮ እያለ የሚያሳየው አንድ ፎቶ ግራፍ ነበር። ሰዎች በገመድ ታዝለው ሲሻገሩ የሚያሳይ። ይህን አንስቼ ምን ድሮ ትላላችሁ አሁንም እኔ የመጣሁበት

አካባቢ እንዲህ ነው እያልኩ ብዙ ጎትጉቻለሁ። በኋላ ላይ አንድ የአካባቢው ተጽዕኖ መፍጠር የሚችል ሰው አግኝቼ ስለሁኔታው ሳስረዳው መንገዱን ሊሰሩ ከሚችሉ ኩባንያዎች ጋር አገናኝቶኝ ከብዙ ጥረት በኋላ መንገዱን ለማሰራት ችያለሁ።

**እርስዎ ተመርጠው ለመጡበት ሕዝብ ለተገነባው መንገድ ሲሚገቱ ኮከሱ ምን አስተዋጽኦ ነበረው?**

ስለ ፓርላማ አሰራር እንዴት ጫና መፍጠር እንደምትችይ እስከምን ድረስ የመሄድ መብት እንዳለሽ ትማሪበታለሽ። በራስ መተማመንን ፈጥሮልኛል።

**የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ከመጨመር አኳያ ኮከሱም ሆነ እርስዎ ምን ሚና ተጫውተዋል?**

በአምስተኛ ምርጫ የሴቶች ቁጥር በምክር ቤቱ እንዲጨምር በዚህ ምክር ቤት ውስጥ የሴቶች ቁጥር ስንት በመቶ መሆን እንዳለበትና እኛም ምን መስራት እንዳለብን ጉዳዩን የምክር ቤት የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ወደ ኮከሱ አመጣው። እሱን ወስደን በስራ አስፈፃሚ ከተወያየን በኋላ ምን እናድርግ ብለን ዕቅድ አወጣን። አንደኛ ፓርቲ ስለሆነ የሚወስነው የፓርቲ መሪዎችን ማወያየት አለብን። ያን ጊዜ ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ኢህአዴግ ነበር ምክር ቤት ውስጥ የነበረው። ስለዚህ ስራ አስፈጻሚ የነበርነው ወ/ሮ ሮማን ገብረ ስላሴ፣ ወ/ሮ ሙፈሪሃት ካሚልና እኔ ሆነን አሁን 28 በመቶ ነን፤ 40 በመቶ እንድንሆን ምን መደረግ አለበት ብለን እንወያይ ጀመር። 40 በመቶ የሚለውን ይቀበሉን ይሆን እያልን እንደውም እየፈራን ግን እንታገል ብለን መስራት ጀመርን። ስራ አስፈፃሚውን ፕሮግራም አስይዘን ከፓርቲ መሪው ጋር ተወያየን፤ ብዙ ከተወያየን በኋላ ሀሳቡን ተቀበሉን።ግን መመዘኛውን የሚላይህን ያህል ሴት ይገኛል ወይ አሉ። ሁሌም እንዲህ ነው ሚባለው፡ ስለዚህ በግብርና፣ በትምህርት፣ በጤና ምን ያህል የተማሩ ሴቶች እንዳሉ እንድናጠና ስራ ተሰጠን። እሱን ይዘን መጣን። በየሴክተሩ የሴቶች ዘርፍ አለ። ከነሱ ጋር ከሚኒስትር መስሪያ ቤቶቾ ጋር ተቀራርበን ሰራን። ምን ያህል ዲግሪ፣ ምን ያህል ማስተርስ ያላቸው ሴቶች አሉ? ምን ልምድ አላቸው? ብለን ማጥናት ጀመርን። ከበቂ በላይ ሴቶች እንዳሉ መረጃ አገኘን። እንኳን 40 በመቶ ከዚያ በላይ ማምጣት ይቻላል። ስለዚህ ሴቶች በዚህ ደረጃ እንዲመጡ ነው ድርጅቱ መስራት ያለበት ብለን የምርጫ መመሪያ ሲሰጥ ይህ አንድ መመዘኛ እንዲሆን ተደረገ ማለት ነው። በድርጅት ኢህአዴግ የሚመራባቸውን ክልሎች በዚህ መልኩ ሰራን። አጋር ድርጅቶችን ደግሞ ተከፋፈልን። በምክር ቤቱ ትልቅ መቀመጫ 23 ወንበር ያለው ሶማሌ ነው።

ስለዚህ እነዚህንም አንድ ከስራ አስፈፃሚ አንድ ከኮሚቴው ሆነን በአካል ሄደን የክልል ፕሬዝዳንቶችን እና የፖለቲካ ኃላፊዎችን ተከፋፍለን አወያየን። እኔ የሄድኩት ሶማሌ ክልል ነበር፤ አስታውሳለሁ።

**ወይይቱ ውጤታማ ነበር?**

ሶማሌ የሚመራው በጎሳ ነው። "ሴቶች ይመሩናል ብለው ላያስቡ ይችላሉ" የሚለው አስተሳሰብ በልዑካኑ ዘንድ ስለነበር ለማሳመን በጣም ትግል ነበረው። ሕዝቡ "እንዴት ሴት የኔን ጎሳ ትወክላለች" ብሎ ይሞግተናል የሚል ትልቅ ትግል ነበር። ሌሎች አፋር ሄደዋል፤ ቤንሻንጉልም ሄደዋል፡ ፡ ለውጥ እንደምታመጡ እርግጠኞች ነን ብለን አበረታታናቸው። ኢህአዴግም እንደዚህ ዓይነት አቋም አለው ብለን አስረድተን ተማመንን። መጨረሻ ላይ ምርጫ ሲያልቅ 38.8 በመቶ ሆንን። 40ው ያልተሳካው አንዳንድ ክልሎች ላይ ክፍተት ስለነበረ ነው። ሶማሌ እንዲያውም 14 ሴት ተመራጮችን በማምጣት ትልቅ ቁጥር ያመጣ ክልል ሆነ። አሁን ይሄ የኮከሱ የስራ ውጤት ነው። አድካሚም ነው ግን ስኬታማ ሆነናል።

**ሕግ ሲወጣም ሆነ ሲጸድቅ ምን ያህል ለሴቶች ጠቃሚ እንዲሆን ያበረከታችሁት አስተዋጽኦ አለ?**

የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ከመጽደቁ በፊት የሴቶችን መብት ለማስከበር በደንብ ሰርተናል። ለምሳሌ አንዱ ይነሳ የነበረው ከአንድ በላይ ማግባት የሚቻልበት ሁኔታ ወይም 'ፖሊጋሚ' ከባድ ክርክር ያስነሳ ጉዳይ ነበር። ይህም በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ መከልከሉ ተቀባይነት ያልነበረው በመሆኑ ነው። ሆኖም ሴት የፓርላማ አባላት ይህ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፤ ሴቶችን ለበለጠ ጉዳት ይዳርጋል ብለን በጣም ድምጻችንን አሰምተን ነው ሊቀር የቻለው። የወንጀል ሕጉ ተሻሽሎ ሲወጣም የሴቶችን መብት ለማስከበር ረጅም ጊዜ የወሰደ ክርክር ነበር። ምሳሌ አስግድዶ መድፈር አሁን ከፍተኛ ወንጀል ነው። ቅጣቱም ከነፍስ ግድያ ጋር እኩል ነው

የሚታየው። እነዚህ ነገሮች ክብደት እንዲሰጣቸው የኮከስ አባላት እነ ወ/ሮ ገነት ዘውዴና ወ/ሮ ጊፊቲ አባሲያን ጨምሮ ሌሎች ትልቅ ሰዎች አስተዋፆ ነበራቸው::

### በኮከሱ አማካኝነት ነው ይሄ የሆነው ብለው ያስባሉ?

አንድ ላይ መሆናችን በጣም ጠቅሞናል ብዬ አስባለሁ። በተጨማሪም ትላልቅ ደረጃ ላይ የደረሱ ሴቶችን ስልጠና ላይ፤ ልምድ ልውውጥ ላይና ለየት ያለ ትልቅ ኮንፈረንስ ላይ እንጋብዛለን። ሴቶች ከተጽዕኖ ነፃ እንዳልሆንን አውቀን መታገል እንዳለብን ይነግሩናል። ስልጠና ይሰጡናል። ማህበረሰቡ አመለካካቱ እስኪቀየር መታገል አለብን ይሉን ነበር። በማህበረሰቡም በወንዶች ብቻ ሳይሆኑ በሴቶችም ዘንድ "ሴት ትችል ይሆን፣ ይሆንላታል ወይ" የሚል አመለካከት አለ። ሴቶችን ዝቅ ወንዶችን ከፍ የሚያደርግ ማህበረሰብ አስተሳሰብ ውስጥ ነው የመጣነው። ስለሆነም ሴት እንደመሪ ተቀባይነትን ለማግኘት ከወንዱ እጥፍ መስራት አለባት።

### ኮከሱን በሰብሳቢነት ለምን ያህል ጊዜ መርተውታል?

በሶስተኛውና በአራተኛው የፓርላማ ዘመን ሙሉ ለሙሉ፣ አምስተኛውን ሁለት ዓመት፣ በአጠቃላይ 12 ዓመት መርቸዋለሁ። በጣም ስራ ስለበዛብኝ ነው የተውኩት። ያደክማል፤ ምክንያቱም ተደራቢ ስራ ተደርጎ ነው ሁሌ የሚያዘው። መደበኛ ስራዬ እንዳለ ሆኖ ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜዬን የሚወስድብኝ የኮከሱ ስራ ነበር::

### ይህን ሁሉ ዓመት እንዴት ለመስራት ቻሉ?

የመጀመርያዎቹን ዓመታት እንኳን ደስ እያለኝ በጣም ብዙ ጥሩ ጥሩ ስራ ሰርተናል። ሴቶች ሀሳባቸውንና እይታቸውን ለውጠውበታል። የንግግርና የአመራር አቅማቸውን አሳድገውበታል። ፖለቲከኛ መሆን ማለት የሚነገረውን ነገር ሰው በሚገባው መንገድ መግለጽ መቻል ነው። ይህንን ሲያደርጉ ስታይ ደስ ይልሻል። በመድረኮች ላይ ከወንዶችም በሚሻል መልኩ ስታያቸው በጣም ያስደስትሻል::

### ስለ እርስዎ ሰዎች እንዲያውቁ የሚፈልጉት ነገር አለ? ለምሳሌ ባህሪይን በተመለከከተ አንዳንድ ሰዎች ከሰጡዎት አስተያየቶች በመነሳት?

ሰዎች "በአካል ሳቂታ ነሽ መድረክ ላይ ስብሰባ ስትመሪ ግን ትኮሳተሪያለሽ" ይሉኛል። መድረክ በምመራበት ጊዜ በጣም የምኮሳተርባቸው ጊዜዎች አሉ። ይህም የሆነበት ምክንያት በጣም ነው የሚፈትኑኝ። የሌለ ስነ-ስርዓት የሌለ አካሄድ ነው የሚያመጡት፤ ሴት ናት ብለው። በዚያ ላይ ምክትልም ነኝ። ሁለቱ ይደራረብና "እያበላሸችው ነው፤ ልክ አይደለም እየሄደች ያለችው" ብለው ያስቡና "እናርምሽ እናስተካክልሽ" ብለው ይላሉ። ጠቃሚ ነገር መናገር እኮ መብታቸው ነው። ግን እንደሱ አይደለም። የእነሱ አስተሳሰብ "አትችልም፤ ሴቶች እኮ አይችሉም" ለማለት ነው። እኔ በነገራችን ላይ በዚህ ስራ ውስጥ በጣም የጣርኩት ለራሴ ብቻ አልነበረም። "ሴቶች አይችሉም ይሄው ቦታ ቢያገኙም አበላሹት" እንዳይባል ነበር የምሰራው። እኔን አይተው ወደ አመራር የሚመጡ በእድሜ የሚያንሱ ከእኔ በታች ያሉ ልጆችም አሉ፤ እኔ ባይሳካልኝ ተስፋ ይቆርጣሉ:: እንደምንችል ደግሞ በጣም አውቃለሁ። ሴቶች ጠንቃቃ ነን፤ ሁሌ በጥንቃቄ የሚያየን እንዳለ እያሰብን ነው የምንሄደው። እኔን ትችላለች ብለው የተረዱኝ በሁለተኛው ዙር ይመስለኛል እንጂ በመጀመርያው ዙር ብዙ ሰው አልተቀበለኝም። ይህን የሚያክል ቤት እኔ ደግሞ የመጀመሪያ ነኝ። ብዙም ሴት የለም ወደ ስልጣን የመጣ፤ በወቅቱ አንድ ሴት የሴቶች ሚኒስትር ብቻ ነበር የነበረችው። ደግሞ መማሬን ቢያምኑበትም በፖለቲካው ግን አልቆየችም የሚል ስሜት ነበራቸው።

### ለብዙ ሴት መሪዎች ምሳሌ እንደሆኑ አስበው ያውቃሉ?

እንደሚቻል ማሳየት በመቻሌ አዎ፤ ማድረግ የምችለውን ያህል አላደረኩም እንጂ። በርግጥ የተማረ ሰው ወደ ፓርላማ መምጣት አለበት ስለተባለ ነው እንጂ እኔ ፖለቲከኛ አልነበርኩም። በዚህም ያገኝሁት እድል አመለካከቴ ሰፍቷል። አለም ዓቀፋዊ እውቀት አግኝቼበታለሁ። እኔ ጠቅላይ ሚኒስተሩንም ፕሬዘዳንቱንም ፊት ለፊት አይቻቸው አላውቅም ነበር። አስታውሳለሁ የመጀመሪያ ቀን በጣም ነበር የፈራሁት። መስከረም የመጀመርያው

የፓርላማ መክፈቻ ቀን ሁሌም በጣም ነው ሞቅ የሚለው። ግቢው ስለሚፀዳ እና አትክልቱ ስለሚስተካከል በጣም ውብ ነው የሚሆነው። ወደ ውስጥ ደግሞ ሲገባ አዳራሹ በቀይ ምንጣፍ ይደምቃል፤ የሁላችንም ስም ደግሞ ተፅፏል። ስለዚህ ስሜን ፈልጌ መቀመጥ ነበረብኝ። የዛን ቀን በጣም ደንግጬ ነበር። ግን ከዚያ ወጥቼ አሁን መድረክ ስመራ እድሉ ሰፊ ነው፤ ቀላል አይደለም። አሁን ምንም አይመስለኝም። 547 አባላት ባሉበት ምክር ቤት ገብቼ መርቼ ነው የምወጣው። ተፎካካሪ ፓርቲዎች እነ አቶ ልደቱ አያሌው፣ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስና ፕሮፌሰር መራራ ጉዲና የነበሩበት ጊዜ የፓርላማ ስብሰባዎችን መርቻለሁ።

## በፓርላማ ዘመኖት የማይረሱት ገጠመኝ ይኖራል?

አንድ ቀን ተፎካካሪ ፓርቲዎች በነበሩበት ጊዜ ነው። ለተፎካካሪዎቸ እድል ሰጥቻቸው የራሳቸውን ተናግረው ሲጨርሱ ለሌላ እድል መስጠት ስጀምር ሁሉም ቦርሳቸውን ይዘው በሙሉ ወጥተው ሄዱ። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊም ነበሩ። አዲስ ስለነበርኩ ራሴም የተፈተንኩበት ጊዜ ነበር። ምን ማለት እንዳለብኝ ራሱ አላውቅም ነበር። "ቁጭ በሉ" ብለሽ አታስቀምጫቸው። የሚደረገው ዝም ማለት ነው፤ ስብሰባው ይቀጥላል። ሁሉም ደግሞ እንናገራለን ግን የነሱን አንሰማም ተባብለው ነው የገቡት፤ ተነጋግረው፤ ያኔ ፓርላማው አዲስ ነበር። ደንግጬ ዝም ብዬ እያየሁ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ መለስ ዜናዊ መደንገጤ ስለገባቸው ልናገር ብለው ጃቸውን አወጡ። ደስ አለኝ፤ የፓርቲ ሊቀመንበርና ጠቅላይ ሚኒሰትር ናቸውና እርሳቸው ያሉት ትክክል ነው ብዬ ሰጠኋቸው። ከዚያ የሆነ ሀገር ፓርላማ ታሪክ መናገር ጀመሩ "አንድ ፓርላማ ላይ አንድ ብቻውን የሚናገር ሰው ነበር አሉ፤ በጣም ይጮሀል። እዛ ስክሪን እያዩ ነው የሚያወሩትና በስክሪኑ ፓርላማውን ሲያሳየው ብቻውን ነው እየጮኸ ያለው፤ ያኔ ዝም አለ የሚሰማኝ ስለሌለ ብሎ" አሉ። ሰውንም አሳቁ። እኔ ያኔ ምን ተረዳሁ አንድ ሰውም እያለ ስብሰባ ይመራል እንኳን ይሄ ሁሉ ሰው እያለ ስለዚህ ብዬ ቀጠልኩ ማለት ነው። ይህ ሌላ ቀን ግን ተደርጎ አያውቅም፤ እኔ ላይ ብቻ ነው የተደረገው።

ሌላ ጊዜ የገጠመኝ ነገር ፕሮፌሰር መራራን "ሰዓትዎትን ጨርሰዋል" ብዬ ሳስቆማቸው እምቢ አሉና መነጋገሪያውን ዘጋሁባቸው። ከዚያ በጣም ተበሳጭተው ጠቅላይ ሚኒስትሩም በነበሩበት "ተናግሪያለሁ የሚበላው ያጣ ሕዝብ መሪውን ነው የሚበላው" አሏቸው። የሚያወሩት ስለ ኢኮኖሚው አለማደግና ስለ ሕዝቡ ችግር ነበር። ዘንድሮ ጀርመን ተገናኝተን አስታወስነው "ዘግተሽብኝ ነበር እኮ" ሲሉኝ "አዎ አንተም እኮ ስርዓት አልጠበክም ነበር" አልኳቸው:: "እንኳን ዘጋሽብኝ። ተበሳጭቼ ነው እንደዚያ የተናገርኩት፤ ባልበሳጭ እንደዚያ አልናገርም ነበር እኮ" አሉኝ። በዚያ ንግግር ከፍተኛ እውቅና ነበር ያገኙት።

## ምን አሉዎት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወቅቱ?

ምንም፤ ለሳቸውም እኔ እኮ ነኝ እድል የምሰጠው። ፓርላማ እንደሱ ነው። እንዲህ ዓይነት አጋጣሚዎች እድሎች ትልልቅ ናቸው።ሁሉም ሰው መሆን የማይችለው እኔ የገጠመኝ እድል ብለሽ መውሰድ ትችያለሽ። ግን በሆነው ልክ ደግሞ እየወደቅሽ እየተነሳሽ ነው የምትማሪው።

ኮከሱ ያስመዘገባቸው ውጤቶች

ኮከሱ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ ባደረጋቸው ጉዞዎች በርካታ ስኬቶችን አስመዝግቧል። የተንቀሳቀሰባቸው ዋነኛ መስኮች የአቅም ግንባታ፣ ውትወታ/ተሟጋችነት፣ ሕግ ማውጣትና ክትትል፣ ሕዝብን መወከልና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣ የበጎ አድራጎት ተግባራትና ማህበራዊ ኃላፊነት እንዲሁም ከሌሎች አካላት ጋር ትስስር ፈጥሮ መስራት ናቸው። ምንም እንኳ ሥርዓተ-ፆታዊ እኩልነትን የማረጋገጥን ግብ ተይዞ የተሄደበት ርቀት ካለው የችግሩ ጥልቀት ጋር ሲነጻጸር ገና በጅምር ላይ ያለ ቢሆንም በኮከሱ በኩል ጉልህና ዋነኛ የሚባሉ ውጤቶች ተመዝግበዋል። ኮከሱ ስኬትን ለማስመዝገብ አዳዲስና ፈጠራ የታከለባቸውን መንገዶች በተግባር ላይ እንዲውሉ አድርጓል።

# አቅም ግንባታ

የአቅም ግንባታ ስራዎችን መስራት ለኮከሱ መመሥረት ዋነኛ ምክንያት ሲሆን መደበኛ እንቅስቃሴውም ሆኖ ቆይቷል። ኮከሱ ከተለያዩ አጋሮች ጋር በመተባበር በሳል ከሆኑ የቀድሞ የምክር ቤት አባላትና የተለያዩ ተቋማት ባለሙያዎች ጋር በቅንጅት በመስራት ፈርጀ ብዙ ስልጠናዎችን ለኮከሱ አባላት ሲሰጥ ቆይቷል። የኮከሱ አባላት የምክር ቤት ተመራጭ ከመሆናቸው በፊት በተለያየ የስራ ዘርፍና የሕይወት መስክ ተሰማርተው የነበሩ እንደመሆናቸው ኮከሱ ጊዜና ሃብት በመመደብ አባላቶቹ ብቁ የምክር ቤት ተመራጭ መሪዎች እንዲሆኑ ይሰራል:: ምንም እንኳን ተከታታይነትና ቀጣይነት ባለው መልኩ ክትትልና ምዘና በማድረግ ስልጠና ለማካሄድ ባይችልም ኮከሱ በአመራርነት፣ በስትራቴጂክ መሪነት፣ በሥርዓተ-ፆታ ኦዲት፣ በሥርዓተ-ፆታ ስርጸት (ጀንደር ሜይንስትሪሚንግ) እና መሰል መስኮች የተለያዩ ስልጠናዎችን ይሰጣል።

ሴት የምክር ቤት አባላትን በማብቃት በኩል ከተገኙ ለውጦች መካከል የአባላቱን የንግግር ክህሎት ማሳደግ፣ ሃሳብን አደራጅቶ፣ አስተካክሎና አሟልቶ መግለጽ መቻል፣ የተሻለ የራስ መተማመን፣ ለውጥን እንዴት ማምጣት እንደሚቻል ማወቅ፣ የአመራር ክህሎት ማዳበር፣ በቋሚ ኮሚቴዎችና ንዑሳን ኮሚቴዎች ውስጥ የመሪነት ስፍራን መቀዳጀትና ከሁሉም በላይ ደግሞ ሕጎች ሲረቀቁ ዕቅዶችና የአፈጻጸም ሪፖርቶች ሲገመገሙ በሥርዓተ-ፆታ መነጽር መመርመር ይካተቱበታል። በአሁኑ ወቅት ካሉት 10 ቋሚ ኮሚቴዎች መካከል 6ቱ እንዲሁም ካሉት 33 ንዑሳን ኮሚቴዎች መካከል ደግሞ 13 ያህሉ በሴቶች ይመራሉ።

በኮከሱ የአቅም ግንባታ ስራዎች ተጠቃሚ የሆኑ አባላት ተሞክሮአቸውን እንዲህ ያጋራሉ፡-

“ወደ ምክር ቤት ተመርጠን ስንመጣ ከተለያዩ የሙያ ዘርፎች በመሆኑ የምክር ቤቱን አሰራሮች፣ ስርዓቶችንና ደንቦችን ማወቅ ላይ ግንዛቤ አልነበረንም ማለት ይቻላል። ለምሳሌ እኔ ቀድሞ አስተማሪ ነበርኩ። ከዚያ በኋላ ሴቶች ጉዳይ ሆኜ ስሰራ ስለነበር በዚያ ዘርፍ የራሴ ልምድና እውቀት ቢኖረኝም ‘በምክር ቤት ውስጥ የአሰራር ስርዓቶችና ደንቦች፣ ሕጎችስ ምንድን ናቸው’ በሚለው ላይ አዲስ እንደመሆኔ መጠን በቂ ስልጠና ስላልነበረን በምክር ቤቱም ሆነ በኮከሱ ስለአባላት ፕሮቶኮል፣ ስለ ምክር ቤቱ አሰራሮችና ደንቦች፣ ስለ ሕግ አወጣጥ፣ በቁጥጥርና ክትትል ላይ የምክር ቤቱ አባላት ሚና በሚሉትና በሌሎችም ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ስልጠናዎችን ኮከሱ ሰጥቶናል። ትላልቅ ስብሰባዎች ላይ እምንሳተፈው ሕዝቡንና ምክር ቤቱን ወክለን ነው። እኔ ምክር ቤቱንና የወከልኩትን ሕዝብ ግርማ ሞገስ በጠበቀ መልኩ መሳተፍ እንደሚገባኝ ስልጠና ወስጃለሁ:: ስለዚህ ምክር ቤት ላይ እንዴት እጄን አውጥቼ ሀሳብ ማቅረብ እንደሚገባኝ፤ እሚቀርቡ አዋጆችና ሪፖርቶች እንዴት የሴቷን መብት ማካተትና የሴቷን ጥቅም ማስከበር ይችላሉ የሚለውን መፈተሽ እንዳለብኝ፤ እንዴት አድርጌ ለይቼ ማየት እንዳለብኝ የተረዳሁት በስልጠናዎቹ አማካኝነት ነው። አሁን ሴቶች እንዴት ተጠቃሚ መሆን እንዳለባቸው ስላወቅሁ ከየሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚመጡልን ሪፖርቶች ተገቢ የፆታ ምላሾችን የሚሰጡ መሆንና አለመሆናቸውን በሚገባ መመዘን ችያለሁ። ለአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ለተግባራት ማስፈጸሚያ በጀት ሲመደብ በክትትልና ቁጥጥር ‘የሴቷ ተጠቃሚነት ግን የቱ ጋር ነው ጎልቶ መታየት ያለበት’ የሚለውን ፈትሼ እንዳወጣና እንድከራከርላት፣ እንድታገልላት እድል ሰጥቶኛል:: በኮከሱ አማካኝነት ሪፖርት ማዘጋጀት፣ መምራት፣ ማደራጀትና ሰዎችን ማስተባበር እንደምችል ተምሬአለሁ። ትዕግስት ስለማድረግና ውጤትን ለማምጣት ማድረግ ስለሚገባኝ ነገሮች በትኩረት ተምሬአለሁ። ስልጠና እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻልና ስልጠናዎች ሰው ተኮር የሆኑና መስህብ ያላቸው እንዲሆኑ ምን ማድረግ እንደሚገባኝ፤ ስብሰባዎችን እንዴት እንደምመራ፤ ሃሳቦቼን እንዴት እንደማደራጅ፤ ነገሮችን እንዴት

መመዘን እንዳለብኝና ኃላፊነቶቼን እንዴት አቀናጅቼ መምራት እንዳለብኝ ተምሬአለሁ። እንደ ኮከሱ ሁሉ የምክር ቤቱ ሴት አባላት ከተለያየ የስራ ዘርፍ የመጡ በመሆናቸው ለአዳዲስ የምክር ቤት አባላት ስለቤቱ የአሰራር ስርዓትና እነርሱም ስራቸውን በብቃት እንዲወጡ ለማስቻል ከምክር ቤቱና ከተለያዩ አጋር አካላትና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን እንሰጣለን።" **(የተከበሩ ወ/ሮ አበባዬ ገዛኸኝ)**

"ስልጠናዎችን በተለያየ ጊዜ እንወስዳለን። የንግግር ክህሎት ስልጠናዎችን ወስደናል፤ ተሞክሮ ልውውጥም እናደርጋለን። በሰው ፊት በመናገር በራስ መተማመን ታዳብሪያለሽ። 'የምክር ቤት አባል ነኝ' ማለት በራሱ የሚፈጥርልሽ ነገር ይኖራል። ከኮከሱ አባላት ጋር አብረሽ መስራትሽ ላንቺ ጥሩ ነው። ሴቶች ላይ በራስ መተማመን ትመለከቻለሽ። በሴቶች ላይ የምታይው ለውጥ ትልቁ ነገር ነው። እኔ አሁን በጣም ተናጋሪ ነኝ፤ አልፈራም። መጀመሪያ ወደ ፓርላማ ስመጣ ግን ፈሪ ነበርኩ። ይህን ያገኘሁት ከስልጠናው ነው። ቀድሞ በየትኛውም መድረክ ላይ አልናገርም ነበር። ልጅ በነበርኩበት ጊዜ ተማሪ እያለሁ ጎበዝ ግን ፈሪና ዝምተኛ ነበርኩ። አሁን ጓደኞቼ አያምኑም፤ ይገረማሉ 'ረግጠንሽ እንኳን ብንሄድ አትናገሪም ነበር' ይላሉ። 'ሴቷ መሪ መሆን አለባት' ከተባለ ማንም መብቷን ሳይረግጥ በትክክል ታግላ መብቷን እንድታውቅ የማብቃት ስራ ነው የሚሰራው።" **(የተከበሩ ወ/ሪት አንችናሉ ይግዛው ተፈሪ)**

"ከወሰድኩት የ'ትራንስፎርሜሽናል' አመራር ስልጠና የተነሳ መምራት እንደምችል በእጅጉ ይሰማኛል። ጓደኞቼና እኔ በራስ ተነሳሽነትና እችላለሁ በሚል ስሜት በመሪነት ሚና ውስጥ እየተሳተፍን እንገኛለን። የያዝነው የመሪነት ሥፍራ በችሮታ የተሰጠን ሳይሆን በብቃታችን ያገኘነው ነው። ከዚህ ቀደም እንደሚሰማኝ ያለመብቃት ስሜት አይሰማኝም።" **(የተከበሩ ወ/ሮ የሺመቤት ነጋሽ፣ የምክር ቤት አባልና የኮከስ ሕዝብ ግንኙነት ዘርፍ ኮሚቴ ሰብሳቢ)**

"በውስጤ ያለውን ነገር አውጥቼ ለመስራት ትንሽም ቢሆን እድሉን አግኝቻለሁ። ለወቅታዊ እውቀት አጫጭር ስልጠና እጅግ ወሳኝ ነው። በተለይ ሕግ አውጪ ስንሆን ሁሉም ነገር ከሀገር፣ ከሕዝብ፣ ከየማህበራዊ መሰረትና ፆታ ተጠቃሚነት አንፃር፣ ከእኩልነትና ፍትሃዊነት አንፃር የሚለካ በመሆኑ ጥያቄ ከመጠየቅ፣ አስተያየትና ውሳኔ ከመስጠት በፊት ስለጉዳዩ እውቀት ሊኖረኝ ይገባልና ስልጠናው ጠቅሞኛል። በኮከስ ተመድቤም ስሄድ ታችኛው የመንግስት እርከን ላይ ያሉትንም ለመደገፍ ያየሁትንም ለመናገር ጠቅሞኛል። መረጃዎችን የማግኘት፣ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ለመገንባትና ለመስራት እድል ሰጥቶኛል:: በኮከሱ ኬንያ ሄጄ 'ስትራቴጂክ ሊደርሽፕ' ስልጠና ለአምስት ቀን ያህል አግኝቻለሁ:: ስልጠናው ጠቃሚ እና ጥልቅ ነበር። አምጥተን ወደ እኛ ቀይረን ከሴቶች ኢ-መደበኛ አደረጃጀት፣ ከድርጅትና ከኮከስ ጋር እየሰራንበት ነው። ስልጠናው አቅሜን እንድገነባ ጠቅሞኛል። በምክር ቤቱ ከማገኘው ስልጠና ይልቅ በኮከሱ በማገኘው ስልጠና የገነባሁት አቅም ትልቅ ነው። አቅሜን ተጠቅሜ ለመስራት እድል ሰጥቶኛል::" **(የተከበሩ ወ/ሮ ፋንታዬ ባቡሎ)**

"ብዙ የምክር ቤት አባላት ከወረዳም ከዞንም የሚመጡ ናቸው። በአቅምም አንዱ ከአንዱ ይለያያል። ብዙዎች ሴቶች የመጀመርያውና ሁለተኛው ዓመት በመድረክ ላይ ሀሳባቸውን አይሰጡም፤ አይናገሩም። እንደውም አንዳንዶች ወንዶች ከተናገሩ ይበቃል ይላሉ። እዚህ ሲመጡ ሌላውን እንደ አዋቂ አድርገው ስለሚቆጥሩ እኔ ብናገር የእኔ ንግግር ከእነሱ በታች ሊሆን ይችላል ብለው ዝም ይላሉ። ኮከሱ ይህን ዓይነት ችግሮችን ቀርፏል። ሁሉም ሰው ትክክለኛ የመሰለውን ሀሳብ እንዲናገር ሆኗል። የመጀመርያውና ሁለተኛው ዓመት ያየሻቸውን በአምስተኛው ዓመት ስታገኚአቸው ልዩነቱን ታይዋለሽ። በደንብ ነው እየተሻሻሉ የሚመጡት። በየጊዜው እያደገ የሚመጣ ለውጣቸውን ታያለሽ። በኮሚቴ ደረጃም እንዲሁ ነው። እኔ አሁን እምመራው ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ መጀመሪያ አካባቢ ምንም የማይናገሩ ተሳትፎ የማያደርጉ ሴቶች ነበሩ። እንደውም አንዳንዴ በግድ እንዲናገሩ ትጎተጉቻቸዋለሽ፤ እሰቲ ዛሬ ተናገሩ ስትይ 'እናንተ ነባሮች እያላችሁ እናንተ እኮ ታውቃላችሁ' ይሉሻል። አንዳንዶቹ ደግሞ በቋንቋ ያመካኛሉ። 'ቋንቋ ስለማልችል ነው' ይሉሻል። ግን አይደለም፤ እውነታው መናገር ስለሚፈሩ ነው። በኋላ ግን ሌላውንም እያዩ ድጋፍም አድርገሽላቸው

ወደዚያ ይገባሉ። ስለዚህ ኮከሱ በዚህ በኩል የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል። ኮከስ ውስጥ ንዑስ ኮሚቴ ላይ የነበሩ ልጆች እዚህም አመራር ላይ ናቸው:: እንደየብቃታቸው ኮከሱ ውስጥ የአመራር ልምድ እያካበቱ መጥተዋል። ስለዚህ ኮከስ ብቃታቸው እየታየ የሚመጣበት አንዱ መድረክ ሆኗል ማለት ነው። እኔ ቀድሞ በነበርኩበት ቦታም ላይ አመራር ነበርኩ፤ የዞን መምሪያ ኃላፊ ነበርኩ። እዚህም ከመጣሁ ቀጥታ የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆኜ አመራር ነው የሁንኩት። በእርግጥ በሚሰጡ ስልጠናዎች የምታዳብሪያቸው ልምዶች አሉ። ለእኔ ግን ኮከሱ ብቻ ነው አልልም፤ በፊትም የመናገር ልምዱ ነበረኝ። ግን እዚህ ሁሉም ከተለያየ ክልል የሚመጣ ስለሆነ ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው ስትሄጂ ምን አለ የሚለውን የምታገኚበት የተለያዩ ልምዶች አሉ። እንደ ሀገርም ማሰብ የምትጀምሪው እዚህ ስትመጪ ነው። በክልላችንና በዞናችን እያለን ስለክልልሽና ዞንሽ እንጂ እንደ ሀገር ሰፋ አድርጎ ማሰብ አይኖርም። እነዚህን ልምዶች እዚህ ፓርላማ ከመጣን በኋላ ነው እያሳደግናቸው የመጣነው። ድሮ አማራ ክልል ውስጥ ሆኜ ደቡብ ክልል ውስጥ ስላሉ ሴቶች ‘ምን ችግር ምን በደል ይደርስባቸዋል፣ ምንዓይነት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አሉ’ የሚለውን አላውቅም ነበር:: የምታውቂው ያለሽበትን ብቻ ነው። እዚህ ስትመጪ ግን በደቡብ፣ በኦሮሚያ፣ በቤንሻንጉል ክልል ላይ ምን አለ የሚለውን ራሱ ፖሊሲዎች የበለጠ ግልጽ ይሆንልሻል።” **(የተከበሩ ወ/ሮ አበባ ዮሴፍ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሴቶች፤ ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ/ የኮከስ ስራ አስፈጻሚ)**

“በኮከሱ ውስጥ ከተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የመጡ ሴቶች ናቸው ያሉበት። የልምድ ልውውጥ፣ የሀሳብ ልውውጥ ስታደርጊ አዳዲስ ነገር ታገኛለሽ። ለምሳሌ ትግራይ አካባቢ የማውቀው የሴቶች ችግር ደቡቡ ካለው ጋር ይለያያል። ስለዚህ ለትግራይዋ ብቻ ሳይሆን ስለ ደቡቧ ሴት እንዳውቅ፣ እንድታገል አድርጎኛል። ውስን ሳይሆን ሰፊ አቅም አገኘሽ ማለት ነው። ስለዚህ ለሴቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትም በዚያዘው ልክ ታስቢያለሽ ማለት ነው። በዚህ በኩል እኔ ጥሩ ነው እላለሁ። በተለይ ወደ አመራርነት ስመጣ እንዳየሁት ጠቅሞኛል። በተለያዩ ስልጠናዎች አንዳንድ የማናውቃቸው አቅሞችን ጭምር አግኝቻለሁ። ሴቶችና ሕግ በሚለው የቤተሰብ ሕግ የሌላቸው ክልሎች መኖራቸውን አላውቅም ነበር። እዚህ ስመጣ ግን ሶማሌና አፋር ክልሎች የተሻሻለ የቤተሰብ ሕግ የላቸውም። ስለዚህ አቅም አግኝቼ እነሱ የቤተሰብ ሕግ እንዲያወጡ ድጋፍ እያደረግን ነው።” **(የተከበሩ ወ/ሮ ናፈቁሽ ደሴ)**

ኮከሱ በራሱ አባላቶች ላይ ተጽኖ ከመፍጠር ባሻገር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሴክሬታሪያት የሥርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነት እንዲኖረው አሰተዋጽኦ ሲያበረክት ቆይቷል። ይህም የሆነው የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት የሴቶች፣ ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የኮከሱ ስራ አስፈፃሚ ቋሚ አባል ስለሆኑ ነው። ዳይሬክተሯ አቅማቸው ሲገነባ ዳይሬክቶሬቱ ከራሱ ሰራተኞች ጀምሮ ትኩረት አድርጎ ሴቶችን የማብቃት ስራ እና የሴቶችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የማረጋገጥ የበለጠ ውጤታማ ሰራ ስለሚሰራ ነው።

“በኮከሱ ብዙ ተሞክሮ አግኝቻለሁ። እያንዳንዱ ክልል ላይ መድረኮች አዘጋጅተን ስለምንገናኝ ብዙ ስለ ክልሎች አውቄያለሁ። ሁለተኛ ለመምራት ሴቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ አቅም ፈጥሮልኛል። የጽህፈት ቤቱ ሴቶች እንደ ምክር ቤት አባላት እንዴት ተምረው፣ አቅም ፈጥረው ወደ ውሳኔ ሊመጡ ይችላሉ የሚለውን አውቄአለሁ፤ ውጤትም አምጥቻለሁ እላለሁ። ኮከሶች የፓርላማ አካል ናቸው፤ ውሳኔ ሰጭዎች ናቸው። ስለዚህ የኮከሱ አቅም እየተገነባ ሲሄድ የፓርላማው ጽህፈት ቤትም አንዳንድ ጊዜ ከነሱ ተሞክሮ ይወስዳል። ለምሳሌ እኔ ከኮከስ ተሞክሮ በመውሰድ በፓላማው ጽህፈት ቤት ላሉ ሴት ሰራተኞች አካፍዬ የተሻለ ሁኔታን መፍጠር እችላለሁ የሚለውን ከኮከሱ ነው የወሰድኩት። በፓላማው ጽህፈት ቤት (በሴክሬታሪያቱ) ውስጥ ባጠቃላይ ከ500 በላይ ሰራተኞች አሉ:: ከነዚህም ውስጥ 250 ሴቶች አሉ። ኮከሱ መምራት እንድችል አግዞኛል፤ የዲፕሎማሲ ስራዎችን እንድሰራ፣ ከግል ተቋማትና ከተለያዩ የክልል አመራሮች ጋር ተሞክሮ እንዳገኝ አድርጎኛል። በተጨማሪም እንዴት ሰው ማሳመን እንደሚቻል ለምሳሌ ከግል ዩኒቨርስቲዎች ጋር በመነጋገርና በማሳመን ሴቶች በነፃ ወይም በግማሽ ክፍያ እንዲማሩ እናደርጋለን። 90 በመቶ ሴቶችን አስተምረን አሳድገናል። በስራ ቦታቸውም በየዓመቱ ቢያንስ 40፣ 50 ሴቶች የግል ኮሌጅ አስገብተን አስተምረናል። አሁን የስራ

ልምዳቸው አድጎ ቡድን መሪዎች በብዛት ሴቶች ናቸው። አብዛኞች ያስተማርናቸው ከ90 በላይ እድገት አግኝተዋል። ከዳይሬክተር ቀጥሎ ቡድን መሪ ነው ያለው። በዚህ ሥፍራ ላይ ድሮ ሁለት ሴቶች ብቻ ነበሩ፤ አሁን እስከ ስምንት ይደርሳሉ። ዳይሬክተር ላይ ምንም ሴት የለም ገና ነው። ወደ ከፍተኛ ባለሙያነት፣ ኦፊሰርነት ያደጉ ሴቶች አሉ። ይማራሉ፣ ያድጋሉ፣ የኢኮኖሚ አቅማቸው ያድጋል፣ አስተሳሰባቸው ያድጋል፣ ጤንነታቸው ይጠበቃል። ማስተማር ብቻ ሳይሆን ጤንነታቸው እንዲጠበቅ ካንሰርና የመሳሰሉትን እናስመረምራቸዋለን፤ በግማሽ ክፍያና በነፃ። ከቤተሰብ መምሪያ ጋር በመሆን በኒውትሪሽን፣ ስነ-ተዋልዶና ኤች.አይ.ቪ ዙሪያ ስልጠና ይሰጣል። ዝቅተኛ ገቢ የነበራቸውን አደራጅተን ገቢ ለመፍጠር ሞክረናል። ሰዎች በትርፍ ጊዜ እንዴት መስራት እንደሚችሉ ንግድ ላይ እናሰለጥናቸዋለን። ካስተማርናቸው በኋላ በየቤታቸው በርበሬ፣ ቅመም እየሰሩ የሚሸጡ አሉ።" **(ሲስተር መብራት ታደሰ፣ የቀድሞ የምክር ቤት ጽ/ቤት ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት)**

ከአጭር ጊዜ ስልጠናና ልምድ ልውውጥ ባሻገር ኮከሱ የምክር ቤቱ ሴት አባላትና የሀገራችን ሴቶች በመንግስት ድጋፍና በራስ አገዝ በስነ-ልቦና፣ በሳይኮሎጂ፣ በአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት በትምህርት ራሳቸውን እንዲያበቁ ይሰራል። ስለሆነም የከፍተኛ ትምህርት ዕድል የሚያገኙበትን አጋጣሚዎች ከምክር ቤቱና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያመቻቻል። የትምህርት ዕድል ያገኙ አባላት በትምህርታቸው ላይ ሙሉ ትኩረታቸውን እንዲያደርጉ የሚበረታቱ ሲሆን በፌዴራል ምክር ቤት ወይም በምክር ቤቱ በሳምንት ሁለት ጊዜ በሚካሄደው የምክር ቤቱ መደበኛ ጉባኤ ላይ ከመሳተፍ በቀር በሌሎች የኮሚቴ ስራዎች እንዲሳተፉ አይጠበቅባቸውም። በዚህ ድጋፍ እስካሁን ድረስ ወደ ምክር ቤት ከገቡ ሴት የምክር ቤት አባላት ዲፕሎማ ያላቸው በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን እያጠናቀቁ እየወጡ ናቸው። አልፎ አልፎም የውጭ ሀገር የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ የማፈላለግ ጥረቶች ይደረጋሉ። በምሳሌነት ለመጥቀስ በሶስተኛው የምክር ቤት ዘመን ኮከሱ ባመቻቸውና ባደረገው የጋራ ትብብር ሁለት የኮከሱ ሴት አባላት ወደ ሕንድ ሄደው የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን እንዲማሩ ተደርጓል። በአራተኛው ዙር የምክር ቤት ዘመን ከዲፕሎማ ወደ ዲግሪ ከተሸጋገሩት 72 አባላት ውስጥ 24 በመቶ ያህሉ ሴቶች ናቸው። የመመረቂያ ወረቀታቸውን በሚሰሩበት ጊዜም ለእያንዳንዳቸው 3000 ብር ከኮከሱ ካዝና ወጥቶ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። ይህ መርሀ ግብር እውን የሆነው ምክር ቤቱና ኮከሱ ከሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ባመቻቸው እድል ነው። በአራተኛው ዙር በዲግሪ የተመረቁ ሴቶች ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ በራሳቸው ጥረት በግላቸው በመንግስትና በግል ዩኒቨረሲቲዎች የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል።

ኮከሱ ከክልል ምክር ቤቶች የሴቶች ኮከስ ጽህፈት ቤት ጋር ሴቶችን እንዴት ማብቃት እንዳለበት ውይይትና ምክክር በማድረግና የጋራ የቤት ስራ በመከፋፈል ሴቶችን የማብቃት ስራን ከማስፋት አንፃር ከሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴርና ከሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ለምክር ቤት ሴቶች ኮታ በመስጠት ከሶስተኛ ዙር የምክር ቤት ዘመን ጀምሮ በየሁለት ዓመቱ ከ120 እስከ 190 ለሚደርሱ ሴቶች የሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል በማዘጋጀት ሴቶች ብቻ እንዲማሩ ተደርጓል። በቀጣይነትም እየተሰራ ነው። የሁሉም ክልል ኮከስ ጽህፈት ቤቶች ከምክር ቤትና ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ቢሮ ጋር በመሆን በየክልሉ የሚገኙ ዩኒቨረሲቲዎችን ትብብር በመጠየቅና በመንግስት በጀት እንዲመደብ በማድረግ ከክልል ክልል ቁጥሩ የሚለያይ ቢሆንም በየዓመቱ በየክልሉ ቁጥራቸው ከ20 እስከ 60 የሚሆኑ ሴቶች የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪና በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ትምህርታቸውን በመከታተል ራሳቸውን እንዲያሻሽሉ እየተደረገ ነው። ለምሳሌ በደቡብ ክልል በቋሚነት በየዓመቱ 60 ሴቶች ከሁሉም አከባቢ የመግቢያ ፈተና ወስደው በመንግስት በጀት በክልል ደረጃ ባሉ ዩኒቨርሲቲዎች፣ በየዞኑ ዩኒቨረሲቲዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ከ7-14 ሴቶች (ዲላ፣ ሀዋሳ፣ ወልቂጤ፣ አርባምንጭ፣ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨረሲቲዎች)፣ በሶማሌ ክልል(በጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ) እና በኦሮሚያ ክልል በሀሮማያ ዩኒቨረሲቲዎች ወዘተ. በቀጥታ እንዲማሩ እየተደረገ ነው። **(ከሴቶች ኮከስ ሪፖርት)**

“በሶስተኛው የምክር ቤቱ የስራ ዘመን እያንዳንዱ የምክር ቤት አባል ወንድም ይሁን ሴት ሶስት አጫጭር ስልጠናዎችን የግድ ይወስዳል። በምክር ቤት የሚሰጡት እነዚህ ስልጠናዎች በሕግ መሰረታዊ እውቀት፤ በኮምፒውተርና እንግሊዝኛ ቋንቋ ላይ ትኩረት ያደረጉ ሲሆን ሁሉም የምክር ቤት አባላት ሶስቱንም ስልጠናዎች ለሶስት ወራት ይሰለጥናሉ። በተለይም ሴት የምክር ቤት አባላት ይህን ስልጠና በተገቢው መንገድ እንዲወስዱ ተደርጓል። በወቅቱ የምክር ቤቱን የአቅም ግንባታ ዘርፍ የሚከታተሉና የሚያስፈጽሙ የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ ወ/ሮ ሮማን ገብረ ስላሴ ነበሩ። የምክር ቤት አባላት በተለይም ሴቶች በረዥምም ሆነ በአጫጭር ስልጠናዎች እራሳቸውን እንዲያበቁ ከኮከሱ አመራሮች ጋር በቅንጅት ይሰራ ነበር። አባላቱ መማር እንዲችሉ የሚያደርጋቸው መስፈርት ላይም ማሻሻያ ተደርጓል። ይህ ለሴቶች ተብሎ የተደረገ ነበር። ለምሳሌ የአገልግሎት ጊዜያቸውንና እድሜአቸውን ግምት ውስጥ ያስገባ መስፈረት እንዲካተት በማድረግ የዕድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑና የብቃት ማረጋገጫ ወስደው እንዲማሩ የተደረገ ሲሆን መመዘኛው ራሱ ከሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ፕሬዘዳንቶች ጋር በመነጋገር ማሻሻያ ተደርጎ ተስተካክሏል። ይህ ማሻሻያ የተደረገው ሴቶች በስፋት እድሉን እንዲያገኙ ነው ። ከ2003 -2008 ባለው ጊዜ ውስጥ አንድ የምክር ቤት አባል ቢያንስ ዲግሪ መያዝ አለበት ተብሎ ሁሉም ተምሯል። በራሱ ፍላጎት ካልተወው በስተቀር የትምህርት እድሉ ለሁሉም ነው የተሰጠው። ከዚያ በኋላም የማስተርስ ዲግሪያቸውን የቀጠሉ አሉ። እኔን በተመለከተ በሶስተኛው የፓርላማ ዘመን ከቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል ተመርጬ ነው ፓርላማ የገባሁት። የስራ ልምዴን በተመለከተ፡- በመተከል ዞን በድባጤ ወረዳ ለስድስት ዓመታት አስተምሬያለሁ። ከመምህርነት በኋላም የወረዳ የሴቶች ጉዳይ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ሆኜ ሰርቻለሁ። ከዚያ ነው ወደ ፓርላማ የመጣሁት። ፓርላማ ውስጥ የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አባል ሆንኩ። በንዑስ ኮሚቴ ውስጥም ለተወሰነ ጊዜ ሰብሳቢ ሆኜ ሰርቻለሁ። የትምህርት ደረጃዬን በተመለከተ ወደ ፓርላማ ስመጣ በ‘ፐብሊክ አድሚኒስትሬሽን’ ዲፕሎማ ነበር የነበረኝ። ፓርላማ ከገባሁ በኋላ ግን በራሴ ጥረት ነው በግሌ ዲግሪዬን የተማርኩት። በሶስተኛው ዙር ምክር ቤት ወቅት ምክር ቤቱ ወይም ኮከሱ በጀት ይዞ አባላትን አያስተምርም ነበር። ሁሉም አባላት ክልሎቻቸው ስፖንሰር አድርገዋቸው ነበር የተማሩት። እኔም እንደ ሌሎቹ አባላት ክልሌ ስፖንሰር እንዲያደርገኝ ጠይቄ ነበር። አፋጣኝ ምላሽ ስላልሰጡኝ በራሴ ወጪ ተምሬያለሁ። የማስተርስ ዲግሪየን ግን በምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት ስፖንሰር አድራጊነት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማርኩኝ። የመጀመሪያ ዲግሪዬንም ሆነ የሁለተኛ ዲግሪዬን ስማር ኮከሱ በገንዘብ ባያግዘኝም በሀሳብና መረጃዎችን በቀላሉና በቅርብ እንዳገኝ በማድረግ ረድቶኛል። ለምሳሌ የሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ ወረቀት ስሰራ ክርብት ወ/ሮ ሽታዬን ‘ኢንተርቪው’ አድርጌያቸው ነበር። በቂ መረጃ በመስጠትና በማበረታታት በጣም ነበር ያገዙኝ። ያኔ ዋናው አፈጉባኤ የተከበሩ አቶ አባዱላ ስላልነበሩ ደርበው በመስራት የስራ ብዛት ነበረባቸው። ስራቸውን አቋርጠው ነበር ጊዜ ሳይኖራቸው ለቃለ-መጠይቅ የተባበሩኝ። እኔም በወቅቱ በጣም አመስግኜያቸዋለሁ። ያዘጋጀሁትን መጠይቅ የኮከሱ አባላት በአግባቡ ነበር ሞልተው የሰጡኝ። ከ90 በመቶ በላይ አባላቱ ምላሽ ሰጥተውኛል። አብዛኞቹ የኮከሱ አባላት ያበረታቱኝና አይዞሽ በርቺ ይሉኝ ነበር። ከዚህ የተረዳሁት ሰውን የሚያበረታታውና ሞራል የሚሆነው ገንዘብ ብቻ አለመሆኑን ነው። ሴት ለሴት የመደጋገፍ ሁኔታ አለ። እኔ ያየሁት እሱን ነው።” **(የተከበሩ ወ/ሮ ነጮቴ ፍላቴ፣ የቀድሞ የምክር ቤት አባል እና የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ንዑስ ሰብሳቢ፣ አሁን የምክር ቤት ጽህፈት ቤት አሰፈፃሚ)**

## ውትወታ/ተሟጋችነት

ኮከሱ ለሴቶች መብት ያከናወነው የተሟጋችነት(አድቮኬሲ) ተግባር ሶስት ገጽታዎች ነበሩት።

1. ሴት የምክር ቤት አባላት ቁጥር እንዲጨምር ይታገላል፤ ለክልል ኮከሶች ድጋፍ ያደርጋል፤ ሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታል፤

2. በሀገሪቱ ውስጥ የሚቀረጹትና የሚተገበሩት ሕጎችና ፖሊሲዎች ለሥርዓተ-ፆታ በጎ ምላሽ ማድረጋቸውን ይከታተላል፤ እና

3. ሴት የምክር ቤት አባላት ኮከስ አባላቱን በማብቃት ከአስፈጻሚ አካላት የሚቀርቡላቸውን ዕቅዶችና የአፈጻጸም ዘገባዎች እየገመገሙ ተጠያቂነትን እንዲፈጥሩ፤ እነዚሁ ዕቅዶችና ሪፖርቶች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይን አማክለው ከወጡ ሕጎችና ፖሊሲዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን እንዲከታተሉ ያደርጋል።

ከኮከሱ ዋነኛ የስራ ኃላፊነቶች መካከል አንዱ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ማሳደግ/ማጎልበት ነው። ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በነበሩ አራት ዙር ምርጫዎች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከሚገኘው 547 መቀመጫዎች መካከል በሴቶች ተይዞ የነበረው ቁጥር ከ2 በመቶ ወደ 38.8 በመቶ አድጓል። ሴት የምክር ቤት ተመራጮች ቁጥር ከ1988-1992 ዓ.ም በአንደኛ ዙር 13 ሴቶች፤ ከ1993-1997 ዓ.ም ሁለተኛ ዙር 72 ሴቶች፤ ከ1998-2002 ዓ.ም ሶስተኛ ዙር 117 ሴቶች፤ ከ2003-2007 አራተኛ ዙር 152 ሴቶች፣ ከ2008-2012 አምስተኛ ዙር 212 ሴቶች ነበር። ከአራተኛው ዙር (2003-2007 ዓ.ም) እስከ አምስተኛ ዙር (2008-2012 ዓ.ም) ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ የሴቶች አባላት ቁጥር ከ27.8 በመቶ ወደ 38.8 በመቶ አድጓል።ይህ ከፍተኛ የሴቶች አባላት ቁጥር መጨመር ኮከሱ ራሱን አደራጅቶ ከፖለቲካ አመራሮች ጋር በመተባበር ሲያደርግ የነበረው ጉትጎታና የማሳመን ስራ ውጤት ማሳያ ነው። በአምስተኛው የምርጫ ዙር በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአባልነት ያሉትን የሴቶች ቁጥር ለመጨመር ኮከሱ ከሴቶች ቋሚ ኮሚቴ መነሻ ሀሳቡን ተቀብሎ በምክር ቤቱ ሊኖር የሚገባው የሴቶች ኮታ 40 በመቶ እንዲሆን ግብ አስቀምጦ ብዙ እንቅስቃሴ አድርጓል። ሴቶች ወደ ምክር ቤት እንዲመጡ ምን ምን እርምጃዎች መወሰድ እንደሚኖርባቸው የውስጥ ውይይት ከተደረገ በኋላ ከፓርቲ መሪዎች ጋር መወያየት አስፈላጊ ነበር። ያን ጊዜ ምክር ቤቱ ሙሉ በሙሉ ኢህአዴግ ስለነበር የኮከስና የሴቶች ቋሚ ኮሚቴ ተወካዮች ከፓርቲው ምክትል ሊቀመንበር ጋር በመወያየት ከ28 በመቶ ወደ 40 በመቶ ከፍ እንዲል ስምምነት ላይ ተደርሷል። ይሁንና መመዘኛውን የሚያሟሉ በቂ ሴቶችን ከማግኘት ጋር ተያይዘው የተነሱ ስጋቶች ነበሩ። ለዚህም በየሴክተሩ ካሉ የሴቶች ዘርፍ ጋር እና ከየሚኒስትር መስሪያ ቤቶች ጋር ተቀራርቦ በስፋት ሰራ። ኮከሱ በግብርና፣ በትምህርት፣ በጤና እንዲሁም በሌሎች መስኮች የሚገኙ ሴቶችን የማፈላለግ ስራ ሰርቷል።

ኮከሱ የክልል ፕሬዘዳንቶችና የፖለቲካ ኃላፊዎችን እያወያየ ሴቶች ወደ ፖለቲካ መሪነት መምጣት እንዳለባቸው ትልቅ የሆነ የማሳመንና የማበረታታት ስራ ሰርቷል። የኮከሱ ኃላፊዎች የሴቶች ተሳታፊነት አናሳ ወደሆነባቸው ወደ ሶማሌ፣ ጋምቤላና ቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልሎች በመጓዝ የሴቶች ተሳታፊነት ላይ ቅስቀሳ በማድረግ ተሟግተዋል። በዚህ ጉብኝት ወቅት የሥርዓተ-ፆታ አካታችነት ጥቅሞችን በተመለከተ ቁልፍ ከሆኑ የማሕበረሰብ መሪዎችና የመንግስት አካላት ጋር ውይይት አካሂደዋል። በእነዚህ ጥረቶች አማካኝነት ኢህአዴግም በቀጣዩ ምርጫ 38.8 በመቶ ሴቶችን አቅርቧል። ለአብነት በሶማሌ ክልል ያለው የሴቶች ተሳታፊነት ቁጥር በአራተኛው ዙር (2003-2007 ዓ.ም) ከነበረው 1 (4 በመቶ) ሴት ተወካይ ወደ 14 (60 በመቶ) በአምስተኛው ዙር (2008-2012 ዓ.ም) ማሻቀቡን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተመራጭ ሴቶች ኮከስ የ2007 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ይገልፃል። ይህ ኮከሱ ለሴቶች እድል ከመፍጠር አኳያ ካስመዘገባቸውው ድሎች አንዱ ነው።

ሴቶች በፖለቲካና አመራር ዙሪያ ያላቸው ተሳትፎ እንዲያድግ ኮከሱ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አማካኝነት ሴት እጩዎችን ለሚያቀርቡ ፖለቲካ ፓርቲዎች የበጀት ማበረታቻ ሕግ እንዲወጣም ተጽእኖ አሳድሯል።

ኮከሱ የሥርዓተ-ፆታ አካታችነትን የማስፈን ኃላፊነቱ አንዱ መገለጫ በወረዳ ደረጃ ያሉ የሴት ማህበራት ላይ የሚሰራው ስራ ነው። የምርጫ ወቅት ሲቃረብ ኮከሱ በወረዳ ደረጃ ካሉ አመራር አካላት ጋር በመቀናጀት ሴቶች የምርጫ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የማነሳሳት እንዲሁም ለአጠቃላይ ዝግጅት የሚሆን በቂ መረጃ ለሴቶች እንዲደርስ የማድረግ ስራዎችን ያከናውናል።

ኮከሱ ለሴቶች መብት መከበር ባደረገው አስተዋጽኦና በፖለቲካው ውስጥ እንዲካተቱ ብሎም አቅማቸውም እንዲጎለብት በማድረጉ ኩራት ይሰማዋል። 60 በመቶ በሚሆን ደረጃ ሴቶች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመሪነት ሥፍራን ሊይዙ ችለዋል። ይህም ሴቶች ከ10ሩ የፓርላማ ቋሚ ኮሚቴዎች ውስጥ 6ቱን ስለሚመሩ ነው።

ኮከሱ በውተወታ ስራው ሰለአስመዘገባቸው ስኬቶች አባላቱ የሚከተሉትን ብለዋል፦

“በታዳጊ ክልሎች የሴቶች ውክልና አናሳ ነበር። ለምሳሌ ሶማሌ ክልል አንዲት ሴት ብቻ ነበረች። እዚያ ጋር በኮከስ መክረን ሄድን። ሴቶች እድሉን ካገኙ የሚመረጡበት እድል አለ፤ እድሉን ካገኙ ውውጤታማ ይሆናሉ። በዚያን ጊዜ ግን ወንዱ ያንን ወንበር ለቅቆ ለሴቷ መስጠት ስለሚከብደው እዚያ ችግር ላይ ትኩረት አደረግን። የሚያሳምን ስራ ሰራን። በታዳጊ ክልሎች ለምሳሌ ቤንሻንጉል፣ ጋምቤላና ሶማሌ ላይ አሁን የሴቶች ቁጥር ጨምሯል። ከሶማሌ ክልል እስከ ሚኒስትር ዴኤታ ድረስ የሄዱት ክብርት ወ/ሮ ሳህረላ አብደላ ጥሩ ምሳሌ ናቸው:: የዚህን ጊዜ እኔ የሕዝብ ግንኙነት ነበርኩ። ስለዚህ መክረን እነዚህ ሴቶች ላይ ምን ማድረግ አለብን የሚል እቅድ አወጣን፤ በዚያ መሰረት ተሰራ። ከስራ ባልደረቦቼ ጋር በመሆን ስትራቴጂክ እቅድ አውጥቻለሁ፤ መነሻውን እኔ ነኝ የሰራሁት። በኋላ አባላት በጋራ አዳብረውት ሴቶችን እንዴት ነው ወደፊት ልናስኬድ የምንችለው የሚል የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ቼክ ሊስት በእቅዱ መሰረት ተሰራ::” **(የተከበሩ ወ/ሮ ብርቱካን ሰብስቤ፣ የሕዝብ ተውካዮች ምክር ቤት አባልና የኮከስ ስራ አስፈጻሚ)**

“እኛ ሶማሌ ክልል 23 ወንበር አለን። በፓርላማው ውስጥ 14ቱ ሴቶች ናቸው። ወንዶች 10 ነን። ‘ሴት እንዴት ምርጫ ውስጥ ትገባለች’ በሚል ብዙ ችግር ተፈጥሮ ነበር። ግን መንግስት ባደረገው ግፊት እንደዚያ እንዲሆን ተደረገ:: በወቅቱ ወንዶች ቅር ብሏቸው ነበር። አሁን በትላልቅ ቦታ ላይ ሁሉ ያኔ ወደ ፓርላማ ሴቶች ይምጡ ሲባል ‘እንዴት ሴት’ ይል የነበረው ሕዝብ አሁን ገብቶታል። ከክልሉ የመጡ ሴቶችንም ኮከሱ የትምህርት እድል ሰጥቷቸዋል:: እንደነ ክብርት ሳህርላ አብደላ ከጤና ሚኒስትርና ሚኒስትር የሆኑ፤ ወ/ሮ ፍሬ አሊ ሙሳ ከመረብ ደህንንት ኮሚሽን ይገኙበታል:: ፈትሀ አህመድ የባህልና ቱሪዝም ኮሚቴ ውስጥ ምክትል ሰብሳቢ ናት። ለዚህ ሁሉ ኮከሱ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው። ድሮ ሴቶችን ዝቅ እናደርግ ነበር። ‘ምን ይሰራሉ፤ ቤት ውስጥ ይሁኑ’ እያልን። አሁን ግን ጥቅማቸው ታውቆ ወደ ፖለቲካው መጥተዋል። የሶማሌ ክልል ምክር ቤት ምክትል አፈጉባኤዋም ሴት ሆናለች። ድሮ ‘ቤት ትቆይ’ የሚባለው ኋላ ቀርነት ነበር።” **(የተከበሩ አብዱ ሙሴ አርቴ፣ ከሱማሌ ክልል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል)**

“ሹመት ሲሰጥ ሀገራችን የጋራ ናት ስልጣን የጋራ ነው። የበቁ ሴቶች አሉን። ስልጣን ስጧቸው ሕዝባቸውንና ሀገራቸውን ያገልግሉ ብለን ትግል እናደርጋለን:: አሁን ራሱ በፓርላማ ውስጥ ከ10 ኮሚቴ አባላት አራት ወንድ ስድስት ሴት እንዲሆን ያደረግነው በምክር ቤቱ ውስጥ ብዙ ጥረት አድርገን ነው። አንዳንዱ ብሔራዊ ድርጅት መቶ በመቶ ወንድ ያመጣ አለ። እንዲያውም አባሉ በአንደኛ ደረጃ ያስቀመጣትን ሴት ትተው ወንድ ያመጡበት ጊዜ ሁሉ ነበር:: ለምሳሌ የደቡብን ብሔራዊ ድርጅት መውሰድ እንችላለን። ከደቡብ ስምንት የንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢና ሁለት የዋና ኮሚቴ ሰብሳቢ በድምሩ 10 ተወካዮች እንዲያቀርቡ ይጠበቃል። 10 ሰው ለመመልመል 20 ሰው መጥቶ ልክ እንደ ምርጫ በወረቀት ድምጽ ተሰጥቶ ካስመረጥን በኋላ ከ 1-3 የወጡ ሴቶችን ትተው ጭራሽ በምልመላ ጊዜ ያልነበረና የደቡብ ፓርላማ መንግስት ረዳት ተጠሪ 10ኛ የወጣውን ጨምሮ ሁለት ወንዶች ይዘው መጡ። በክልሉ መድረክ ታግለን ወደ ትልቁ መድረክ ሁሉ ወስደነው፤ ወደ ሚዲያ ሁሉ አወጥተነው ችግሩ እንዲታይ አድርገን አንድ ሴትና አንድ ወንድ በውድድሩ ከነበሩት ውስጥ ተመርጠው እንዲገቡ አድርገናል። በዚህ ጉዳይ ከደቡብ ብቻ ሳይሆን ከሁሉም ክልል ነበር ሴቶች የታገሉት:: ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር የላከውን ሳይቀር አንቀበልም ብለን መልሰን

እናውቃለን። እሳቸው በኮሚቴ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ሊመድቡ አይችሉም። ተጠርተው ይነገራቸው ወይም መግለጫ ይስጡን ብለን መልሰናል። ይህ የሉአላዊነት ጉዳይ ነው። ሕጋችንን አክብሩልን፤ እሳቸው ማድረግ የሚችሉት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው አልን። እሱም ቢሆን ካላሳመነን ለእኛ ሲያመጡት የማስቀየር መብት አለን። ሁለት ጉባኤ ተበትኖ በሶስተኛው ነው ያጸደቅነው። እንደውም አንዳንዶች በልዩ ሁኔታ እኛ ስልጣን መያዝ ሲገባን ታግለው ስልጣን አሳጥተውናል የሚሉ ሁሉ ነበሩ። ግን ለአላማ ከቆምሽ ሁሉንም ማድረግ ትችያለሽ። አሁንም ገና ሰፊ ቁርጠኝነት ይጠይቀናል።" **(የተከበሩ ወ/ሮ ፋንታዬ ባቡሎ)**

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ የሴቶችን መብት ለማስከበር ከሚሰራው ስራ ባሻገር ኮከሱ በሚሰራባቸው ሥፍራዎች ሁሉ በየማህበረሰቡ የሚታዩትን የሥርዓተ-ፆታ ክፍተቶች ለማጥበብ አበክሮ ይተጋል። ኮከሱ ለሴቶችና ወጣት ሴቶች መቆሙን ያሳየበት አንዱ ተግባር ለሴት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች 2007 ዓ.ም ላይ ያደረገው ተሟጋችነት/ውትወታ ነበር። ከሴቶች ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከ23 ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር ሴት ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው የሚቀሩባቸው ዋነኛ ተግዳሮቶች እንዲለዩ፤ በተለይ በሴት ተማሪዎች ላይ ከሚደርሰው ሥርዓተ-ፆታዊ ትንኮሳ ጋር ተያይዞ በሴት ተማሪዎች ላይ ያለውን ተጽዕእኖ አስመልክቶ ጥልቅ ምርምር አስደርጓል። ይህንን ጥናት መሠረት በማድረግ በቀጥታ ወደ ተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች በመሄድ ሴት ተማሪዎች በሚገጥሟቸው ተግዳሮቶች ዙሪያ ውይይት አካሂዷል። በዚህ ጥናት መሠረት የኮከሱ አባላት ሴት ተማሪዎችን ለማገዝ ግልጽ እርምጃዎችን ወስደዋል። ኮከሱ ለዩኒቨርሲቲ አመራር፣ ለሴት የዩኒቨርሲቲ መምህራንና ተማሪዎች የሃሳብ ማንሸራሸሪያ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ለተለዩ ጉዳዮች ምክረ ሃሳቦችን አፈላልጓል። ለምሳሌ የሴት መምህራንና ፕሬዝዳንቶች ቁጥር መጨመር፣ ሴት መምህራንና ሴት ተማሪዎች ያላቸው ቅርርብ መሻሻልና የሴት መምህራንና ተማሪዎች ፎረም መቋቋም የዚህ ውጤት ነው።

"ከአዲስአበባዩኒቨርስቲውጭሁሉምዩኒቨርሲቲዎች በስልጠናው ተካትተዋል ማለት ይቻላል። ከምክር ቤቱ የተሻለ አቅም ያላቸውን ሴቶች በመመደብ የአሰልጣኞች ስልጠና እየሰጠን ስልጠና እንዲሰጡ በማድረግ ነው ይህን የሰራነው:: በሂደቱ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን ብቻ አይደለም ያወያየነው፤ ይዘን የመጣነውን ግብዓት በአንድ ላይ ጨምቀን ሁለት ጊዜ ትላልቅ መድረኮች ተዘጋጅተዋል። የዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንቶች፣ የተማሪዎች ተወካዮችና ሴት አስተማሪዎች ባሉበት ለሁሉም አስተላልፈናል። አንዱ ከአንዱ ጥሩ ተሞክሮ እንዲያገኝ መጥፎ የሆነውን ደግሞ ያኛው እንዳይወርሰው የማድረግ ስራ ተሰርቷል። ከዚህም ባለፈ ሴቶች ተማሪዎች ሊያጋጥሟቸው የሚችሉትን ተግዳሮቶች ለይተን በማውጣት ከተሳታፊዎቹ ጋር መፍትሄዎችን አውጥተናል። ተከታታይነቱ ላይ አንድ አምስት ዩኒቨርስቲዎችን መርጠን ችግሮች ተፈትተዋል ወይ ብለን አየን። የተፈታ አለ፤ ያልተፈታ አለ። እሱን ገምግመን ከትምህርትና ከሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴሮች ጋር ተቀናጅተን ጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጠውም አስደርገናል። ለዚህም አፈጉባኤዎች በሚመሩበት መድረክ ቀርቦ ክቡር አባዱላ ባሉበት የጋራ ውይይት ተደርጎ አቅጣጫ ተሰጥቷል። በተጨማሪ የተማሪዎች ተወካይ ቢበዛ ሰባት ዓመት ነው በከፍተኛ ትምህርት ውስጥ በተማሪነት የምትቆየው፤ እሷ ትምህርቷን ጨርሳ ስትለቅና በአዲስ ሰው ስትተካ ስራው መቀጠል አለበት። እንደዚያ ዓይነቱ የማስቀጠል ስራ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት::" **(የተከበሩ ወ/ሮ ብርቱካን ሰብስቤ)**

"ከአምስት አመት በፊት ሴት ተማሪዎች በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የትምህርት ተሳትፎና በሚያጋጥማቸዉ ተግዳሮት ሰፊ ችግር ያለበትና ትምህርት አቋርጠዉ ወደ ቡና ቤት ይገባሉ የሚባልበት ጊዜ ነበር። ትምህርት ካቆረጡ ወደ ቤተሰብ ስለማይመለሱ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎቸ ዉስጥ ሰፊ ችግር ይታይ ነበር። ከትምህር ሚኒስተርና ከሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ሚኒስተር ጋር ተነጋግረን ችግሩን ለመቅረፍና ምቹ የመማር ማስተማር ሁኔታ ለመፍጠር ስራዎችን ለመስራት የሚያስችሉ ዉይይቶችን በማካሄድ ችግሮችን

ነቅሶ በማዉጣት ቀጣይ የመፍትሄ እርምጃዎችን ለማስቀመጥና አሰራሮችን ለመዘርጋት ያሞች ዘንድ በማዕከል ደረጃ እቅዶች በማዘጋጀት ከመምህራን ጋር ዉይይት መድረክ ፈጠርን። ለምሳሌ ጅማ ማዕከልን የመራሁት እኔ ነበርኩ። ያን ጊዜ የሙቱ፣ የጋምቤላ፣ የነቀምት፣ ጊንቢና አሰሳ የኒቨርሲቲዎች ሴት መምህራን ተገኝተው ነበር። ጅማን ማዕከል በማድረግ ስምንት ዩኒቨርስቲዎችን ባህር ዳር ላይ እዚያ አካባቢ ያሉትን ዩኒቨርስቲዎች በማምጣት፣ ድሬዳዋ ላይ ራሱን አስችለን፤ ሀሮማያ፣ ሐዋሳና አርባ ምንጭ ላይ ሰባት ማዕከላት አዘጋጅተን 'ያሉት ችግሮች ምንድን ናቸው፣ ተማሪዎችን እንዴት እየደገፋችሁ ነው' የሚለውን ጠየቅን፤ የመወያያ ጥያቄም አቀረብን:: ክልል ላይ ያሉ አደረጃጀቶችም ውስጥ ያሉ ሴቶችን ስልጠናው ላይ አሳተፍን። እኛ በቀጣይነት ስለማንሰራ፤ ስራችንም ሕግ አወጣጥና ሀገራዊ ስራ ላይ ስለሚያተኩር በአካባቢያቸው ያሉትን የዩኒቨርስቲ ሴት መምህራንና ሴት ተማሪዎች በባለቤትነት በጋራ ችግሮችን ለመቅረፍ እንዲሰሩ የሴት ተማሪዎችና መምህራን ፎረም ተቋቋመ። እንደ የዩኒቨርስቲያቸዉ ነባራዊ ሁኔታ ፎረሙ የሚመራበት መመሪያና ፎረሙን የሚመሩ ከሴት ተማሪ፣ ከሴት መምህራንና ከሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ቢሮ ተወካዮችን አደረግን። ይህም ሴቶች ችግር ሲገጥማቸው፤ 'ይህ የሥርዓተ-ፆታ ቢሮ ቀጥታ ችግሬን ይቀርፍልኛል' ብለው እንዲተማመኑ ነው ያደረገው። በቀጣይም የተለዩ ችግሮችን መነሻ በማድረግ ችግሩን ለመፍታት ምን ላይ ማተኮር እንደሚገባቸዉና ሁሉም የየድርሻዉን ለመወጣት ምን ማድረግ እንዳለበት መግባባት ላይ ተደርሶ ስራዉን በኃላፊነት እንዲወጡት አቅጣጫ አስቀምጠን ለስራዉ መሰረት ጥለናል ማለት ይቻላል:: ከዚያም በኋላ የፋይናንስ ችግር ያለባቸዉን የሥርዓተ-ፆታ ቢሮዎች ዩኒቨርስቲዉ በጀት እንዲመድብላቸዉና ሴት ተማሪዎችን እሚደግፉበትን አቅጣጫ እንዲያስቀምጡ፤ ለሴት ተማሪዎች ራሱን የቻለ ስልጠናም እንዲሰጡ ጭምር ነዉ ያደረግነዉ። በጣም እምረካበት (ነገር) በወንድ መምህራን የሚፈጠርባቸዉ ጫና እንዲወገድ ከትምህር ሚኒስተር ጋር ሆነን እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ያደረግናቸዉ መምህራን አሉ። ሴቶች ወተዉ የሚደርስባቸዉን ችግር ለየኒቨርስቲዉ ማህበረሰብ የማሳወቅ አቅም በመፍጠር በኩልም ሰርተንበታል። በዚያ ዙርያ የሰራነዉ ስራ ቀጥሏል ወይስ አልቀጠለም የሚለዉን መጠነኛ ዳሰሳ አደረግን፤ ዳሰሳዉ 'ጀንደር' ቢሮዎች ተጠናክረዉ መቀጠላቸዉን፣ ማናጅመንት አባል መሆናቸዉን፣ በጀት እየተመደበላቸዉ መሆኑን በዉጤት አስቀጥለናል፤ ግን ከአካባቢዉ ሴቶች አደረጃጀቶች ጋር ያለዉ ግኑኝነት መቀዛቀዝ ታይቶበታል። የሴት ተማሪዎች ትንኮሳ ሙሉ ለሙሉ ባይጠፋም በመጠን መቀነሱንና አሁንም ተለይቶ ሊሰራበት እንደሚገባ የጥናቱን ዉጤት ለትምህርት ሚኒስተርና ለሴቶች እና ህፃናት ሚኒስተር ግብረ መልስ ልከንላቸዋል። እኛ ዉጤት አግኝተንበታል። በቀጣይም ስራዉን በባለቤትነት ለማስቀጠል የሥርዓተ-ፆታ ተወካዮችም ቢሆኑ ኮከሱ በተለያዩ ምክንያቶች የስራ ለዉጥ ሊያደርግ ስለሚችል ስራዉን የሚያስቀጥል አካል በሚቀጥለዉ ጊዜም ሊሰራበት ይገባል ምክንያቱም ትዉልድን በእዉቀትና በሥነ-ምግባር አንጾ የማሳደግና ከአልባሌ ተግባራት የማዳንና ብቁ ዜጋን የማፍራትና ትዉልድን የማስቀጠል ስራ በጋራ የመስራት ስራ ነዉ መስራት ያለብን።" **(የተከበሩ ወ/ሮ አበባዬ ገዛኸኝ)**

# ሕግ ማውጣት እና ክትትል

## ሕግ ማውጣት

ኮከሱ የሕግ አውጪ የመንግስት ክንፍ የሆነው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አንዱ አካል ነው። እንደ ሕግ አውጪ አካልነቱ ኮከሱ ሕግ በማሻሻል እንዲሁም ውድቅ በማድረግ በከፍተኛ ደረጃ ይሳተፋል። ረቂቅ ሕጎች ለውይይት ከመቅረባቸውና ድምጽ ከመሰጠቱ አስቀድሞ ለኮከሱ የሚቀርቡበት ሥርዓት ተበጅቷል። ኮከሱ የሚወጡት ሕጎች የሴቶችን ጥያቄዎች/ፍላጎቶችና የእነርሱን ልዩ ተግዳሮቶች ያካተተ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት ተሸክሟል።

ኮከሱ ተጽዕኖ ካሳደረባቸው ሕጎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡-

1. በአዲሱ የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 1064/2017 የወሊድ ፍቃድ ከሶስት ወራት ወደ አራት ወራት እንዲሆን ማድረግ፣ ለአባቶች ከአምስት ቀናት ወደ አስር የስራ ቀናት፣ ለዉርጃ ከአንድ ወር እስከ ሶስት ወራት፣ ለህጻናት ክትባት በስራ ቀን ያለ ፈቃድ እንዲወጡ ወዘተ.
2. በወንጀል ሕጉ አዋጅ ቁጥር 414/2004 አስገድዶ መድፈር ከነፍስ ግድያ እኩል ትልቅ የወንጀል ቅጣት መደረጉ፤
3. እያንዳንዱ የመንግስት ተቋም የህፃናት ማቆያ ራሱን የቻለ ተቋም መገንባትና ህፃናትን በመንከባከብ ሴቶች በስራቸው ውጤታማ ስራ እንዲሰሩ ማድረግ ግዴታ እንዲሆን:: (የሰብአዊ መብት የድርጊት መርሀ ግብር ተብሎ በምክር ቤት ደረጃ የጸደቀው ብሔራዊ ሰነድ እያንዳንዱ አስፈፃሚ አካል በሚሰራበት መስሪያ ቤት ተቋም ላይ ግዴታ ይጥላል።)
4. የሴቶችና የሕዝቦች መብቶችና ፕሮቶኮል (የማፑቶ ስምምነት) ምንም እንኳን ብዙ በጎ ጎኖች ቢኖሩትም ከስምምነቱ ጉዳዮች አንዱ የሆነው ድርብ ጋብቻንና ሚስቶች በባሎቻቸው ስም እንዲጠሩ የሚፈቅደውን አንቀፅ የኢትዮጵያ መንግስት በ’ሪዘርቬሽን’ ማጽደቅ፤
5. ሴት እጩዎችን ለሚያቀርቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የበጀት ድጋፍ ማበረታቻ ሕግ መውጣት፤
6. የፌዴራል ቤተሰብ ሕግን መሰረት ያደረገ የክልል የቤተሰብ ሕግ እንዲወጣ ግፊት ማድረግ፤
7. የወንጀል ሕጉ ተሻሽሎ ሲወጣም ረጅም ጊዜ በወሰደ ክርክር መጽደቁ፤
8. የሀገሪቱ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሲዘጋጅ የባለ-ብዙ ዘርፍ ጉዳይ እንድ ምሰሶ ሆኖ እንዲቀመጥና እንዲተገበር መደረጉ፤
9. እጅግ በጣም አከራካሪ የነበረው መድኃኒት እና መጠጥ አዋጅ መጽደቁ፤
10. እያንድንዱ በምክር ቤት የሚጸድቅ አዋጅ ሥርዓተ-ፆታን ማዕከል ያደረገ እንድሆን ልዩ ትኩረት እንዲያገኝ መደረጉ ወዘተ. ይገኙበታል።

የቤተሰብ ሕግ ከወጣ 15 ዓመታት አስቆጥሯል። ይህ ተግባራዊ በሆነባቸው ክልሎች ሴቶችም ህፃናትም ተጠቃሚ ሆነዋል። ሁለት ክልሎች ግን እስካሁን የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አላጸደቁም:: ኮከሱ ምንም ዓይነት የቤተሰብ ሕግ በሌለባቸው በሶማሌና አፋር ክልሎች ለሴቶች መብትና የፖለቲካ ተሳትፎ ሲሟገት ቆይቷል። በእነዚህ ክልሎች የሴቶችን ጥበቃና ተሳታፊነታቸውን ለማሻሻል የዳሰሳ ጥናቶች ተካሂደው የመፍትሄ ሃሳቦች ተሰጥተዋል።
“ሕጉን የማውጣት ዋናው ስልጣን የክልሎች ነው። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስልጣን አይደለም። ነገር ግን ሕጉን ያወጡ ክልሎች ተሞክሮን አቅርበን እንዴት አድርገው ማውጣት እንዳለባቸው አስገንዝበናል። ሕጎቹን ለማውጣት ችግር የሆነባቸው ምንድን ነው ብለን እንጠይቅና ከዚያ መፍትሄው ይቀርባል። ሕጉን ሴቶች ብቻ አያወጡትም። ርዕሰ መስተዳደር አለ፤ የተለያዩ የሴቶች ጥምረት፤ የሴቶች ሊግ አደረጃጀቶች ሊሆኑ ይችላሉ፤ በሴቶች ዙሪያ የሚሰሩ ተቋማት ይኖራሉ፤ ከዚህ በፊት ሕጉን ያወጡ ክልሎች እንዴት እንዳወጡት ለእነዚህ አካላት ማሳወቅ ነው። ለምሳሌ እኔ የትግራይን ክልል የቤተሰብ ሕግ አወጣጥ ሂደት አውቃለሁ። እንደ ኮከስም ተሞክሮ ለማድረግ ሰነድ አዘጋጅተናል።

ሕጉ ባልወጣባቸው ክልሎች ውስጥ የማስተማርና ሕጎች እንዲወጡ የማበረታታት ስራ በመጀመር ላይ ነን። ለመደገፍም እየተዘጋጀን ነው። በሶማሌና በአፋር ክልል የተሻሻለ የቤተሰብ ሕግ እንዲጸድቅ ለማድረግ ተፅእኖ ፈጣሪ የሚባሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን ለምሳሌ የሀይማኖት መሪዎችን፣ የጎሳ መሪዎች፣ የሴቶች አደረጀጃቶችን፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ እንዲያደርጉ አቅማቸውን የማጎልበት ስራ መሰራት አለበት። ይህ ብዙ ስራ የሚፈልግ ጉዳይ ነው። የቤተሰብ ሕግ ያላወጡ ክልሎችን ሰብስቦ ማግባባት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ መግባባትና መፍትሄ መፈለግ ይኖራል። አንድ ግንዛቤ በማስጨበጥ ሁለተኛ ደግሞ ሕግ በማውጣት ደረጃ በደረጃ መፍትሄ እያስቀመጡ መሄድ ነው::" **(የተከበሩ ወ/ሮ ናፈቁሽ ደሴ)**

"የቤተሰብ ሕግ ተግባራዊ በሆነባቸው ክልሎች ሴቶችም ህፃናትም ተጠቃሚ ሆነዋል:: በዚያው ልክ ደግሞ እንደ አፋርና ሶማሌ ያሉ የቤተሰብ ሕግ ያላወጡ ክልሎች አሉ። ይህም ሆኖ የሴቶን ችግር አይፈታም። 'በሕገ-መንግስት ጭምር የተሰጣትን መብት የሚገድብ ስለሆነ መሻሻል አለበት' ብለን ጥረት አድርገናል። አሁን ከሶማሌ ክልል ጋር ወደ መስማማቱ ደርሰናል። የክልሉ ፕሬዝዳንት የፍትህ አካላትና የሀይማኖት መሪዎችም አምነዋል ግን ወደ ወረቀት ቀይሮ ተግባራዊ ለማድረግ መስመር ላይ ነው ያለው። አፋር ላይ ግን እስካሁን ወደ ኋላ ማለት አለ። ግን ተስፋ ሳንቆርጥ ከፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ፣ ከሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴርና ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ጋር ሆነን እየሰራን እንገኛለን። የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የአምስት ዓመቱ የድርጊት መርሀ ግብር ይህን ይዟል። ይህ ሀገራችን እንደተልቅ ስትራቴጂ የያዘችው ዕቅድ ነው። በዚህ ዕቅድ ላይ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ፣ ሰብአዊ መብት ኮሚሽንና ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት በጋራ ይሰራሉ። ነገር ግን በዋናነት ኮከሱ ነው የሚሰራው። ከዚህም ስንወጣ የኮከስ አባል የመሆን መብት ስላለን የማያቋርጥ ጥረት እናደርጋለን::" **(የተከበሩ ወ/ሮ ፋንታዬ ባቡሎ)**

## ክትትል

የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት በሁሉም መስክ ለሴቶች መብትን አጎናጽፏል። በሕገ-መንግስቱ መሠረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከ1000 በላይ የሆኑ ሕጎችን ያጸደቀ ሲሆን ኮከሱም እነዚህ ሕጎች ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ እንዲሰጡ የበኩሉን ጥረት አድርጓል። በሹመት ጊዜ የሚሾሙ ሴቶችን ቁጥር በማየት እንዲሁም ሴቶች በብዛት ወደ ውሳኔ ሰጪ ኃላፊነቶች እንዲመጡ ምን እርምጃዎች እንደታቀዱና ምን ያህሉ እንደተተገበሩ ይከታተላል። ይሁን እንጂ ከወጡ ሕጎችና ፖሊሲዎች አንጻር የሴቶችን እኩል ተሳታፊነትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ረገድ በተለይም ደግሞ ሥርዓተ-ፆታዊ እኩልነት የተረጋገጠባቸውን ሕጎች እስከታችኛው የአስፈጻሚ እርከን ደረጃ (ቀበሌ) ድረስ አውርዶ በመተግበር ረገድ ገና ብዙ መሥራት ይጠይቃል።

የኮከሱ አባላት እንዲሁም ተባባሪ ወንድ አባላት በሥርዓተ-ፆታ መነጽር ሕጎችን የሚመረምሩበትን ብሎም ደግሞ የአስፈጻሚ የመንግስት አካላት የስራ ዕቅዶችና የአፈጻጸም ሪፖርቶች በሚያቀርቡበት ወቅት ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሏቸውን በርካታ መንገዶች ቀይሷል። የአስፈጻሚው አካል የአፈጻጸም ሪፖርት ሲመዘንና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች የመስክ ጉብኝት ሲያደርጉ የወጡ ሕጎችና ፖሊሲዎች መሬት ላይ ካለው ዕውነታ አንጻር ለማነጻጸር እንዲረዳቸው ኮከሱ ቼክ ሊስቶችን ያዘጋጃል:: ኮከሱ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን አፈጻጸም ግምገማ ለማካሄድ እንዲያስችል እንዲሁም ሥርዓተ-ፆታዊ እኩልነትና የሴቶች ተጠቃሚነት መረጋገጡን ለመገምገም እንዲቻል የሥርዓተ-ፆታ ሥርጸትን (ጀንደር ሜይንስትሪሚንግ) እና የሥርዓተ-ፆታ ኦዲትን ጨምሮ በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ስልጠናዎችን ያዘጋጃል።

"የምንሰራው አዲስ ሕግ አውጥተን አይደለም:: መንግስት ያስቀመጠው ፖሊሲም ሆነ ሕግ-መንግስቱ የሰጣቸው መብቶች ወደ መሬት ይውረዱ፤ ከሴቶች ጋር ይገናኙ ብለን ነው። ይህ ግን ስራውን በዋነኛነትና በኃላፊነት የያዘ አስፈፃሚ

አካል የእኛን ራዕይ ተቀብሎ ሴቷን እኩል ተሳታፊና ፍትሃዊ ተጠቃሚ ማድረግ ላይ እስካሁን ፈተና ነው። በየትኛውም መድረክ ላይ ተስማምተው እንሰራለን፣ እየሰራን ነው፤ ግዴታችን ነው ብለው ይወጣሉ:: ከወጡ በኋላ ግን ሄደሽ የሰሩትን ስታይ ሌላ ነው። ለምሳሌ መንግስት ወጣቶችን የስራ ዕድል ፈጠራ ተጠቃሚ ሲያደርግ ሕጉ ሴቶችንም ወንዶችንም አመጣጥኖ እንዲሰራ ነው የሚያዘው። ግን 10 ሰው ቢደራጅ አንድ ሴት ነው የሚገኘው። እዚያ ቀበሌ እዚያ ወረዳ ውስጥ ሴቶች የሉም ወይ? አሉ። በስራ አጥነት ዝርዝር ሲባል ደግሞ 50 በመቶ ሴት 50 በመቶ ወንድ ይሆናል የምታገኚው። ሲያደራጁ ግን ዘጠኝ ለ አንድ ወይም ስምንት ለ ሁለት ነው የሚያደራጁት። ይህ አንዱ ፈተና ነው:: ብዙ ጊዜ በተለያየ መድረክ ላይ መረጃ እያደራጀን ብቁ ሴቶችን ለማፍራትና ሴቶችን ወደ ስልጣን ለማምጣት እየተሰራ ነው ይባላል። ነገር ግን ተመልሰን ዳሰሳ ስናደርግ ብዙም ለውጥ አይታይም። 20 ሰው ስልጣን ተሰጥቶት ከሆነ ሁለት ወይም ሶስት ሴቶች ናቸው የሚገኙበት። በውይይት መድረኩ አምነው ተቀብለው ከሄዱ በኋላ ወደ ታች ካላወረዱት ክፍተት ይፈጠራል::" **(የተከበሩ ወ/ሮ ፋንታዬ ባቡሎ)**

በውሳኔ ሰጭነት ቦታ ላይ ሴቶች የነበራቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ ነበር። አሁን ግን አንዳንድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ላይ መሻሻል ይታያል። እያንዳንዱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በዳይሬክተርነት ቦታ ላይ ስንት ሴት እንዳስቀመጠና ስንት ሴት በትምህርትም ሆነ በስልጠና እንዳበቃ የሚጠየቅበት አሰራር ተዘጋጅቷል። ይህ ክትትል የሴቶችን ተሳትፎ በደንብ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩበት ያበረታታል።

"ምን ያህል ለውጥ መጥቷል የሚለው የኮከሱ ትኩረት ነው። እንደ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ የሚሰጡ ተግባራትና ኃላፊነቶች አሉ። ከዚያ ባሻገር በኮከሱ በኩል የሚሰጡ ኃላፊነቶች በምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ ምን ያህል የሴቶችን ጥያቄዎችና ተጠቃሚነት አነሳችሁ የሚል ነው። ስለዚህ እንደ ምክር ቤት አባላት ኃላፊነቶች በደንብ ለመወጣት ትጥቅ የሚያሲዘን ኮከሱ ነው።" **(የተከበሩ ወ/ሮ የሺመቤት ነጋሽ፣ የምክር ቤት አባልና የኮከስ ሕዝብ ግንኙነት ዘርፍ ኮሚቴ ሰብሳቢ)**

የኮከሱ አባላት እንደሚገልጹት የሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 35 የሴቶችን እኩልነትና ያላቸውን መብት በግልጽ የሚደነግግ ቢሆንም ያን ብቻ ይዞ ሴቶችን ተጠቃሚ ማድረግ ይከብዳል። ግብርናና ጤናን ወደ መሳሰሉ ዘርፎች ሲወሰድ እንዴት ነው ሴቷን ተጠቃሚ ማድረግ የሚቻለው ብሎ ማጥናት ያስፈልጋል።

"ለምሳሌ የጤናን ጉዳይ ብንወስድ በወሊድ ምክንያት አንዲት እናት መሞት የለባትም ከተባለ አብረው መጠየቅ ያለባቸው ነገሮች አሉ። አንቡላንስ አለ ወይ? የተሟላ ጤና ተቋም አለ ወይ? በየደረጃው ያሉት የጤና ተቋማት ምን ይመስላሉ? ቀበሌና ወረዳ ላይ ህፃናት ከተወለዱ በኋላ ተገቢ ክትባት ያገኛሉ ወይ? እናቶች ስለ እነኚህ ጉዳዮች ግንዛቤ አላቸው ወይ? ከሌለስ ይህን ለማድረግ ምን ያህል ታቅዶ እየተሰራ ነው? በወሊድ መቆጣጠሪያ ዙርያ በራሷ መርጣ አራርቃ ለመውለድ ምን የተመቻቸላት ነገር አለ? በጤና ኤክስቴንሽን በወረቀት ላይ የሰፈሩት ነገሮች መሬት ላይ ምን ይመስላሉ? ተብሎ መጣራት አለባቸው። ግን ጥቅል መብት ይዞ ሴቶችን መጥቀም አይቻልም። ለመጠየቅ አመቺና ዝርዝር የሆነ ሕግ ያስፈልጋል። እኛም በዝርዝር የማየት መነፅራችን እየሳላ ሄዷል ለማለት ነው።" **(የተከበሩ ወ/ሮ የሺመቤት ነጋሽ፣ የምክር ቤት አባልና የኮከስ ሕዝብ ግንኙነት ዘርፍ ኮሚቴ ሰብሳቢ)**

ከሴቶችና ከህብረተሰብ ተጠቃሚነት አንፃር የመንግስት በጀት ለተገቢው አላማ ውሏል ወይስ አልዋለም የሚለውን መከታተል ኮከሱ ከሚፈጽማቸው የክትትል ተግባራት መካከል አንዱ ነው። ለዚህም እንዲረዳ ለአባላቱ የበጀት አጠቃቀም ላይ ስልጠና ይሰጣል። ይህም ምክር ቤቱ ያፈፃፀም ግምገማ ሲያደርግ የኮከሱ አባላት በበቂ ሁኔታ ያፈፃፀም ክትትል እንዲያደርጉ ይረዳል። አባላቱ በተመደበው በጀትና በተተገበሩ ሕጎች ስንት ሰው ተጠቃሚ እንደሆነ በተለይም ስንት ሴቶች ተጠቃሚ እንደሆኑ ያረጋግጣሉ። በተጨማሪ ሕጎች በአግባቡ መተግበራቸው የሚረጋገጠው በክትትልና በመስክ ምልከታ ነው። ከአስፈጻሚው አካል በዓመት አራት ጊዜ የአፈጻጸም ሪፖርት ለምክር ቤቱ የሚቀርብ ሲሆን የቀረቡ ሪፖርቶችን ከተያዙ ዕቅዶች ጋር በማመሳከር ግምገማ ይካሄዳል። በተለያዩ ዘርፎች

ከተሰማሩ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ከሚሰበሰበው ሪፖርት በተጨማሪ በመስክ ምልከታ የተሰራውን ስራ እንዲሁም የተገኘውን ውጤት በተጨባጭ ይመለከታል፤ ህብረተሰቡንም ያወያያል::

## የምርጫ አካባቢ ማህበረሰብ ውክልና እና ተጠያቂነት

የኮከሱ አባላት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት እንደመሆናቸው የተመረጡበት ዋና አላማ የመረጧቸውን ክልሎች፣ ዞኖችና ቡድኖች መወከል ነው። በምክር ቤቱ አሰራር አንድ ተመራጭ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ወደየተመረጠችበት የምርጫ ክልል ትሄዳለች። የመጀመርያው ዙር ከየካቲት 1 እሰከ 30 ምክር ቤቱ የሚዘጋበት ጊዜ ላይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከሀምሌ መጀመሪያ እስከ መስከረም መጨረሻ ድረስ ነው።

የኮከሱ አባላት ወደየተወከሉበት የምርጫ ክልል በመጓዝ የማህበረሰቡን - በተለይም ደግሞ የሴቶችን ተግዳሮቶችና ፍላጎቶች ያጤናሉ። ከጤና፣ ትምህርት፣ መሠረተ ልማት ፍላጎቶች አንስቶ እስከ የፖለቲካ አካታችነት ድረስ ያሉ የማህበረሰብ ፍላጎቶችን ይዳስሳሉ። የተገነዘቧቸውን የማህበረሰብ ተግዳሮቶች ለመፍታት ወደሚመለከታቸው የቀበሌ፣ የዞን፣ የክልል ወይም የፌዴራል መንግስት አካላት በመውሰድ የፋይናንስ ድጋፍ በማፈላለግም ይሁን አዲስ ሕግ በማርቀቅ ለችግሮቹ መፍትሄ ያፈላልጋሉ። በተጨማሪም በምክር ቤቱ የወጡ ሕጎች የሴቶችን ፍላጎቶች ያማከለ መሆኑን ለማረጋገጥ የኮከሱ አባላት በየስድስት ወሩ በታችኛው የመንግስት አካል ውስጥ በወረዳ ወይም ቀበሌ ደረጃ ካሉ የሴት አደረጃጀቶች ጋር ይወያያሉ። ከዚህ በተጨማሪ ከክልል ኮከስ አባላት ጋር ስልጠናና የልምድ ልውውጥ ይደረጋል። የዚህም ዓላማ መናበብ እንዲኖር ለማስቻል፣ ጠንካራ ትስስር ለመፍጠርና ሴቶችን ለመጥቀም የተወጠኑት የኮከሱ መርሀ ግብሮች በተዋረድ መስረጻቸውን ለማረጋገጥ ነው። ይሁን እንጂ ሴቶችን በቀበሌ ደረጃ ከማግኘት አንስቶ ችግሮቻቸውን እስከ መፍታት ድረስ በርካታ ተግዳሮቶች ይገጥሟቸዋል።

"እኔ የተመረጥኩት ደቡብ ክልል ላይ አሰራቶጫ ምርጫ ጣቢያ ላይ ነው። እዚያ ስሄድ የድርጅቱን አሰራር ይዘን እንሄዳለን። ይህ የኮከሱ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የመንግስት አቅጣጫ ነው። በጤና፣ በመሰረተ ልማት ላይ ያሉ ችግሮችን ለቅመን መጀመሪያ ወደ ክልል አምጥተን ከክልል መንግስት ጋር እንነጋገራለን። ለምሳሌ ይህ ፕሮጀክት ቆሟል፤ እዚህ ቦታ መብራት የለም፤ ውሃ የለም፤ የሚል የተጠናከረ መረጃ ይቀርባል። በዚያ ካልተፈታ ወደ ፌዴራል ደረጃ ይመጣና ለሚመለከተው አካል ይሰጣል። ፓርላማ ላይ ደግሞ ያን ሚኒስቴር መስሪያ ቤት የሚመራው ሰው ተጠርቶ ይመጣና ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ ይሰጣል። በፓርላማ ስራ የመንግስትን አቅጣጫ ስንሰራ ነው የኮከሱን ስራ አብረን የምንሰራው። ሕዝቡ ወረዳ ላይ ተሰብስቦ ይመጣል። አልፎ አልፎ ቀበሌም እንሄዳለን። በጣም ችግር ያለበት፣ መሰረተ ልማት የሌለበት ቦታ ላይ የምክር ቤት ተወካይ ማነጋገር እንፈልጋለን የሚሉ ካሉ እየተመረጠ ይኬዳል። በዋናነት አንድ የምክር ቤት አባል ሰው የሚያገኘው ወረዳ ላይ ነው። ዞኑ ደግሞ በክልል ስር ነው። በክልል ደረጃ የማይፈቱት ችግሮች ወደ ፌዴራል ይመጡና በጀት ይያዝና ክትትል ይደረጋል። የምክር ቤት አባል ሲኮን ብዙ ስራ አለ። ትናንት ይዘን የመጣነውን ችግር ሳንፈታ ነገ ተመልሰን አንሄድም። ስለዚህ ተሯሩጠን ነው የምናሰራው። በዚህ ረገድ ከፌዴራልና ከክልል መንግስት ጋር ኮከሱም ተጨማሪ ሀይል ሆኖን ስንሰራ ቆይተንናል።" **(ወ/ሮ ወርቅነሽ ዋጆ፣ በምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት ትራንስፖርት ክፍል ኃላፊ/ የቀድሞ ምክር ቤት አባልና የቀድሞ የኮከስ አባል)**

ለተወካዮች ምክር ቤት የሚቀርቡት ሪፖርቶች የሴቶችን ችግር ከመፍታት አንፃር ብዙ የሚቀራቸው ናቸው። እንደ ትምህርትና ጤና ባሉ ዘርፎች የመሰረተ ልማት መስፋፋት ቢታይም ሴቶች አሁንም ስለመብቶቻቸው በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ተሳትፏቸው አናሳ ነው። መራጮችን የሚያገኙ ተወካዮች መራጮችን በክላስተር ለማወያየት የተዘረጋን የመንግስት መዋቅር ይጠቀማሉ። የአንድን አካባቢ ነዋሪዎች ጠርተው በሚያነጋግሩበት ጊዜ የሴቶች ተሳታፊነት ዝቅ ያለ ስለሆነ ብዙ ሴቶች ጋር ለመገናኘት ይቸገራሉ። በአንጻሩ ወንዶች ስብሰባዎች ላይ በመገኘት ስለመብቶቻቸው በመጠየቅና በማወቅ ረገድ የተሻለ ተሳታፊነት አላቸው። በተሰብሳቢዎች የሚነሱትን ችግሮችና ቅሬታዎች በመሰብሰብና በማደራጀት በየደረጃው ወደሚመለከታቸው አካላት አድርሰው መፍትሄ ይፈልጋሉ።

“ሕዝቡ ከምክር ቤት አባል ጋር ለመገናኘት ለስብሰባ ሲጠራ ሴቶች በብዛት እኛ ወደዚያ እንደምንሄድና እንደምናወያይ መረጃው አይደርሳቸውም። ወንዶች ናቸው የሴቶች ጉዳይን ጨምሮ ስላለው ችግር የሚያነሱት:: ይህን ለመቅረፍና ሁሉም ማህበረሰብ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን ኮከሱ ከወረዳ ጀምሮ ነው አመራሮችን ማብቃት ያለበት:: ለምሳሌ የልጆች ክትባት ሲመጣ አንድ የክልል ኮከስ አባል ‘ሂጂ ቀስቅሽ’ ልትባል ትችላለች። ነገር ግን ይህን ማንም ሊሰራው ይችላል። የእርሷ ዋና ስራ መሆን ያለበት እናት ልጇን ለክትባት ያላወጣችበትን ምክንያት አዉቃ ወይም ቤት የምትወልድ ከሆነ ምክንያቱን ጠይቃ በዛች ሴት ላይ ያስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ ስራ መስራት ነዉ።ይሄ አንዱ የክትትል ኃላፊነት ነው። የምክር ቤት ተመራጭ የመራጩን ማህበረሰብ ችግር ባይቀርፍም ድምጽ ያገኛል። በርግጥ ሴቶች ምረጡኝ ስትያቸዉ ምንም ሳይደረግላቸዉም ይመርጣሉ። እንዲያዉም አንዳንድ ቦታ ‘እከሌ የመረጠዉን ነዉ የምምርጠዉ’ ይሉሻል:: ስለዚህ በሴቶች ላይ ብዙ የሚሰሩ ስራዎች አሉ። በክልል መዋቅሮች ውስጥ ያሉ ሴቶችም በፌዴራል ደረጃ የሚጸድቁ ሕጎችን እንዴት ማውረድና መከታተል እንዳለባቸው በደንብ ግንዛቤ ቢያገኙ፣ በጀት ቢገኝ፣ የየቀበሌው ተወካዮችን ሁለት ሶስት ቀን በደንብ አሰልጥነናቸው ብንመጣና ስራው ከምን ደረሰ እያልን ብንከታተል መዋቅሩ ታች ድረስ ይደርሳል። አለበለዚያ ግን ሰማይ ላይ እንደሚቀር ነው የሚሰማኝ::” **(የተከበሩ ወ/ሮ አበባ ዮሴፍ)**

ኮከሱ ከሚሸከማቸዉ ኃላፊነቶች መካከል ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ይገኝበታል። በዚህ ረገድ ኮከሱ ተጠያቂነትን በሁለት መንገድ ያረጋግጣል። አንደኛ የኮከስ አባላት እንደማንኛውም የምክር ቤት አባል አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች በምክር ቤቱ የሚወጡትን ሕጎች ከማስፈጸም አኳያ ምን ያህል እንደሰሩ ይከታተላሉ። ያልተሰሩም ስራዎች ካሉ ተገቢውን ክትትል ያደርጋሉ። ከመራጮች በሚመጡት ጥያቄዎችና ቅሬታዎች መሰረት ምን ያህሉ እንደተሰራ አይተው ለመራጮች በዓመት ሁለት ጊዜ ሪፖርት ያደርጋሉ። በሁለተኛ ደረጃ የኮከስ አባላት ከሕጎቹ መፈጸም ባለፈ የሴቶችን ተጠቃሚነት ይገመግማሉ። ከክልል የሴቶች አደረጃጀቶች ጋር በመሆን የሴቶችን ተጠቃሚነትና ተሳትፎን ለማስከበር እንቅስቃሴ ያደርጋሉ።

## በጎ አድራጎት እና ማህበራዊ ኃላፊት

ማህበረሰባዊ ቀውሶች በሚፈጠሩበት ጊዜ ሴቶችና ህጻናት ዋነኛ ተጠቂዎች እንደመሆናቸው መጠን ኮከሱ ምን ጊዜም ቢሆን ከእነዚህ ቀውሶች ጋር የተያያዙ ጫናዎች እንዲለዝቡ ለማድረግ ይጥራል። እንዲሁም ኮከሱ የሚሰጠው እርዳታ ሴቶችና ህጻናት ላይ ትኩረት ያደርጋል። ለምሳሌ ኮከሱ በሀገሪቱ ውስጥ ለተፈናቀሉ አካላት መደጎሚያ የሚሆን ፋይናንስ አሰባስቧል። ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ በሶማሌና ኦሮሚያ ክልሎች መካከል በተፈጠረ ግጭት በርካታ ሴቶችና ህፃናት ተጎድተው ነበር። ይህን አስመልክቶ በምክር ቤት ውስጥ ትልቅ ድምጽ ያሰማው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሴቶች አደረጃጀት ኮከሱ ነው:: ከኮከስ ካዝና ወጪ በተደረገ 400,000 ብር ለሁለቱም አካባቢዎች ድጋፍ ተደርጓል። በሶማሌና ኦሮሚያ ክልል ውስጥ የተፈጠረውን ግጭት አስመልክቶ መንግስት ዝም ያለበትን ምክንያት እንዲገልጽ በኮከስ በኩል ጠይቀን መንግስት በምክር ቤቱ በመቅረብ መግለጫ ሰጥቶበታል።

“ከሶማሌና ኦሮሚያ ክልሎች ጋር በመናበብ ከእኛም ከእነሱም በመመደብ ቡድን በማቋቋም ከኮከሱ ካዝና ወጪ ተደርጎ በአልባሳትና በሚያስፈልጋቸው ቁሳቁስ አስፈላጊ ነገሮችን አድርገናል። ያሉበትን ሁኔታ ደግሞ ዝርዝር ጉዳይ ለመንግስት አቅርበን መልሶ ማቋቋምን ጨምሮ ድንኳን በማቅረብ ተለይተው እንክብካቤ የሚደረግላቸው የተለየ ድጋፍ እንዲያገኙና መታከም ያለባቸው እንዲታከሙ አድርገናል። በሀገራችን በ23/10/2012 ዓ.ም በተፈጠረዉ የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ድንገተኛ ሞትን ምክንያት በማድረግ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመርዳት ከምክር ቤቱ፣ ከሚኒስትር መስሪያ ቤቶችና መሰረተ ልማት ድርጅቶች፣ ከአደጋ ስጋት ኮሚሽን ጋር በመተባበር 47 ሚሊዮን ብር የሚገመት የተለያዩ ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጓል። በጎርፍ ምክኒያት ለተፈናቀሉና ለተጎዱ ወገኖች በስድስቱ ክልል (አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ጋምቤላ፣ አፋር፣ ደቡብ እና ሶማሌ) የ13.5 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ተደርጓል። በዋና ከተማዋ አዲስ አበባ በተለምዶ ቆሼ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ጉዳት በደረሰ ጊዜ የኮከሱ አባላት በስፍራው ተገኝተው የተጎዱ ወገኖችን ከመጎብኘት ባሻገር የገንዘብ ድጋፍ አድርገዋል።” **(የተከበሩ ወ/ሮ አበባዬ ገዛኸኝ)**

በ 2011 ዓ.ም የካቲት ላይ በጉጂ ኦሮሞና ጌዲዮ አካባቢ ግጭት በተፈጠረ ጊዜ አስቸኳይ ጉባኤ ተጠርቶ የኮከሱ ሴቶች በሙሉ ከተባባሪ ወንዶች ጋር በመሆን በቡድን ተደራጅተው ወደነዚያ አካባቢዎች እንዲሄዱ ተደርጓል። የኮከሱ አባላት ሴቶችና ህፃናት ከተፈናቀሉበት ወደ ቤት እንዲመለሱ የመንግስት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ አሳይተው የምክር ቤቱን ድጋፍ አግኝተዋል። ስምንት ቡድኖች ተደራጀተው ሄደው አካባቢውን በመጎብኘት ሴቶችና ህፃናት ያሉበትን ሁኔታ መዝግበው መረጃ አደራጅተው ለመንግስት አቅርበዋል። ይህን ችግር ለመፍታት እንደ ሰላም ሚኒስቴር የመሳሰሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የተሰማሩ ቢሆንም ኮከሱ የራሱን አስተዋጽኦ አድርጎ የአካባቢውን ሕዝብ ደግፏል። ይህ የበጎ አድራጎትና የማህበራዊ ኃላፊነት ስራ ኮከሱ ዋና ብሎ ከያዛቸው ተግባራት መካከል አንዱ ነው።

## ትስስሮችን መፍጠር

የኮከሱ አንድ የስራ ትኩረት መርሀ ግብሮቹንና ዕቅዶቹን ዘላቂ ለማድረግ የሚያስችሉትን የስራ ትስስሮችን መፍጠር ነው። ከዚህ አንጻር ኮከሱ ከብዙ ባለድርሻ አካላት ጋር ትስስር ያደረገ ሲሆን ከእነዚህ መካከል የክልል ኮከሶች፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች፣ የቀድሞ የምክር ቤት ሴት አባላት፣ የሴቶች፣ ወጣቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የመንግስት ተቋማት (የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ትምህርት ሚኒስቴር፣ የሰላም ሚኒስቴር) እና ሌሎችም ይገኙበታል። ከዚህ ባሻገር ከዓለም አቀፍ ኮከሶች ጋር፣ ከምሥራቅ አፍሪካ በይነ መንግስታት ኮከሶች ጋር፣ በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያ ከሚሰሩ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር (ለምሳሌ ዩ ኤን ውሜን፣ ጀስቲስ ፎር ኦል፣ ዩ ኤን ዲ ፒ) ትስስርን አድርጓል። እነዚህ ዘርፈ ብዙ ግንኙነቶች ባለ ድርሻ አካላት አብረው ስለሚያቅዱና ስለሚተገብሩ ኮከሱ የሚሰራቸው ስራዎች ምሉዕ እንዲሆኑ፣ ዘላቂነት እንዲኖራቸውና እንዲስፋፉ ዕድል ሰጥተዋል።

## ከክልል ኮከስ ጋራ ያለ ትስስር

ኮከሱ የክልል ፎረም ተብሎ ለሚጠራው ኮከስ አባላት በአስተዳደር ዘርፍና በአመራር ዘርፍ ስልጠና ይሰጣል፤ ክህሎቶችን ያካፍላል። ይህም ሴቶችን አብቅቶ በክልል ኮከሶች ውስጥ የመሪነት ሥፍራን እንዲቆናጠጡ ለማድረግ የታለመ ነው። በዚህ መልክ ሴቶች ቡድኖቻቸውን በተሻለ ብቃት ለመምራት፣ እነርሱም ከነበሩበት የኃላፊነት እርከን በመጨመር የተጽዕኖ አድማሳቸው እንዲሰፋና ከፍተኛ ኃላፊነቶችን እንዲሸከሙ የማስቻል ስራ ተሰርቷል። የሴቶችን መብት በማረጋገጥ በሁሉም መስክ እኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ በኢኮኖሚ እራሳቸውን እንዲችሉ ብሎም ደግሞ መንግስታዊ ኃላፊነት የሚረከቡትን ሴቶች ቁጥር ለማሳደግና በርካታ ሴቶች በፖለቲካ አመራር ውስጥ ጉልህ ድርሻ እንዲኖራቸው ለማስቻል የታሰበ ስልጠናን ይሰጣል።

የክልልና የፌዴራል እንዲሁም የከተማ መስተዳድሮች ምክር ቤቶች የጋራ መድረክ በስድስት ወራት አንዴ ይካሄዳል። ይህ ስብሰባ ከኮከሱ ጋር የተያያዘ ሳይሆን ምክር ቤቶች ምን ማድረግ አንዳለባቸውና ምን ጥሩ ልምድ እንዳለ የሚመክርና አንዱ ክልል ከሌላው የሚማማርበት እራሱን የቻለ መድረክ ነው። በዚህ ስብሰባ የክልል ምክር ቤት አፈጉባኤዎ፣ ቋሚ ኮሚቴ አመራሮች፣ የከተማ መስተዳድሮች ምክር ቤቶችና አመራሮች፣ ከፌዴራል ኮከሱና ከክልል ኮከስ አደረጃጀት አመራሮች ይሳተፋሉ። በስድሰት ወራት አንድ ጊዜ ከሚካሄደው የክልል፣ የከተማ መስተዳደሮችና የፌዴራል ሪፖርቶች የሚቀርቡበት የክልሎች የአፈጉባኤዎች ፎረም መድረክ ስብሰባ ከመካሄዱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ በየክልሉ ያሉ የሴቶች ኮከሶች የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኮከስን ጨምሮ የራሳቸውን ስብሰባ ያካሂዳሉ። ይህ ስብሰባ የየክልሎቹ ምክር ቤቶች ኮከሶች በየክልሎቻቸዉ ተመራጭ ሴቶችን ከማብቃትና የመላዋን ሴት ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን በማስመልከት ምን ጥሩ ልምድ እንዳለ የሚመክር እና አንዱ ክልል ከሌላዉ የሚማማርበት እንዲሁም ለቀጣይም የጋራ አቅጣጫ የሚቀመጥበት መድረክ ነዉ። በዚህ መድረክ ላይ፡-

1. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሴቶች ኮከስ ስድስት ወራት ሪፖርት ግምገማ፤
2. የኮከሱ የዓመት እቅድ ላይ ውይይት፤ እና
3. የክልሎች ኮከስ አደረጃጀት ስራ ሪፖርት ላይ አጫጭር ዉይይቶች ይካሄዳሉ።

ይህ የሴቶች ኮከሶች መድረክ እውቅና አግኝቶ በመንግስት በተፈቀደ በጀት ሲደገፍ ከአምስት ዓመታት በላይ ሆኖታል። በተጨማሪ በዓመት አንድ ጊዜ የፌዴራል ኮከስ አባላት በአካል ተገኝተው የተሻለ ስራ የሰራውን ኮከስ ከየክልሉ፣ ከዞኑ፣ ከወረዳው ወይም ከቀበሌው ለይተው ተሞክሮ ይሰበስባሉ። በተጨማሪም አጭር ቼክ ሊስት አዘጋጅተው ተሞክሮ ሲወስዱ ያገኟቸውን ድክመቶች በየደረጃው እያዩ ድጋፍ ያደርጋሉ። በአንድ ክልል የተገኙ ጥሩ ተሞክሮዎችን ለሌሎች ክልሎች የማካፈል ስራም ይሰራል። የክልል ኮከሶች ሉአላዊነታቸው የተጠበቀ ስለሆነ ለፌዴራል ኮከስ የሩብ ዓመት ሪፖርት አይልኩም። በየሩብ ዓመቱ ቀበሌ ለወረዳ፤ ወረዳ ለዞን፤ ዞኑ ለክልል፤ በተዋረድ የራሳቸውን የጽሁፍ ሪፖርት ያቀርባሉ።

"በሕገ-መንግስታችን ክልል የራሱ ሉዓላዊነት አለው። የክልል ኮከሶችን ከእኛ አቻ አድርገን እነሱን እንደታናሽ እህት አድርገን ተግባብተን አደራጅተናቸዋል። ድጋፍ ሰጥተናቸዋል፤ አሁንም እንሰጣለን። ከክልል ደረጃ ወደታች ለመደገፍ ግን የክልል ኮከሶች እራሳቸው በምክር ቤታቸው በጀት ያስይዛሉ። ኮከሶቹ በክልል ምክር ቤቶች ያስመደቡትን በጀት ታች ድረስ ለስልጠና፣ ለክትትልና ለድጋፍ ያውሉታል። ይህ የበጀት ምደባ ግን በሕግ የተደነገገ አይደለም። በየክልል ምክር ቤቱ በተቀመጡ አፈጉባኤዎች በጎ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው:: ስለዚህ የበጀት ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። የክልል ኮከሶች የሴቶችን መብት ከማስከበር አኳያ ከፍተኛ ስራ መስራት ይችላሉ። ለምሳሌ ታች ድረስ ወርዶ ሴቶችን በማግኘት መብታቸው እየተከበረ ስለመሆኑ ለመከታተል እንዲሁም ሴቶች መብታቸውን ለምሳሌ በሕገ-መንግስቱ፣ በሴቶች የልማት ፓኬጅ አውቀው ጠያቂ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ሴቶች መብታቸውን ማስከበር እንዲችሉ ማብቃት ይቻላል። ስለዚህ የክልል ኮከሶች ቁልፍ ሚና አላቸው።" **(የተከበሩ ወ/ሮ ፋንታዬ ባቡሎ)**

"የፌዴራሉ የምክር ቤት አባላት ነዋሪነታቸው በአዲስ አበባ በመሆኑ ቋሚ የሆነ ግንኙነት እንዲኖረን አስችሏል። ይህ በፌዴራልና በክልል ኮከስ መካከል ያለው አንዱ ልዩነት ነው። በክልል ምክር ቤት ያሉ ኮከሶች ግን የሚገናኙት ጉባኤ ሲኖር ብቻ ሲሆን ያም የሆነበት ምክንያት የክልል ምክር ቤት አባላት የሚኖሩት በክልሉ ውስጥ የተለያዩ ቦታዎች በመሆኑ ነው። የአማራ ክልል ከፌዴራል ኮከስ ተሞክሮ በመውሰድ የክልል ምክር ቤቶች ሴቶችን ቀድመው በመሰብሰብ ከየዞኑ ያሉትን ሰዎች ባህር ዳር ላይ ይሰበስቡና በአጀንዳዎች ዙርያ ውይይት ያደርጋሉ:: ለምሳሌ መሬት ላይ የሚጸድቅ አዋጅ ካለ በዚያ ላይ ቀድመው ተወያይተው እኛ ምን ማድረግ አለብን ብለው ወስነው ወደ ክልል ምክር ቤት ስብሰባ ይገባሉ። ይህ በአማራ ክልል እስከ ወረዳ ድረስ የሚተገበር ሲሆን ከምክር ቤት ስብሰባ በፊት በመገናኘት የኮከስ አቋም ምን መሆን አለበት የሚለውን ተወያይተው ወስነው አንድ አቋም ይዘው ይገባሉ።" **(የተከበሩ ወ/ሮ አበባ ዮሴፍ)**

የኮከሱ አባላት በሴቶች ጉዳይ ላይ ለተሰማሩና በክልል ለሚሰሩ ድጋፍ ይሰጣሉ። የሚያይዋቸውንም ክፍተቶች በመመዝገብ ስልጠና እንዲሰጥ ግፊት ያደርጋሉ። ለምሳሌ ኮከሱ ከደቡብ ክልል ሴቶች ጉዳይ ጋር በጋራ በመተባበር በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ ጅንካና አዋሳ ላይ የሰላም ኮንፈረንስ አዘጋጅቶ ነበር። እንደ የሴት ልጅ ግርዛት የመሳሰሉት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መቆም ለሴቶች ሰላም፣ ጤናና እድገት ያለውን አስተዋጽኦ በተመለከተ ውይይት ተደርጎ የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት ተሞክሯል። ይህ ኮንፍረንስ ከሁሉም ሀይማኖቶች ከተውጣጡ የሀይማኖት አባቶች ጋር የተካሄደ ሲሆን በክልል ምክር ቤት ያሉትን አመራሮች የጨመረ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ሰላም ለሴቶች ምን ፋይዳ እንዳለው ብሎም በግጭት አፈታት ላይ የሴቶች ሚና ምን ይሆናል በሚለው ላይ ተሰርቷል።

## ከወንድ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ጋር አጋርነት

በሴት የምክር ቤት አባላት የተደራጀው ኮከስ በቀድሞ ጊዜ የነበሩና አሁንም ድረስ ያሉ ሴት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የተካተቱበት ማህበር ብቻ ሳይሆን በሂደት የኮከሱ ደጋፊ ሆነው

ሥርዓተ-ፆታን ያማከለ ሕግ እንዲወጣ የሚተጉ ወንዶችንም ተባባሪ አባላት አድርጎ አቅፏል። በአሁኑ ወቅት የተባባሪ ወንዶች አባላት ቁጥር ብዛት 168 ደርሷል። ይህም ካሉት ወንድ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት መካከል ወደ 39 በመቶ ያህሉን ይይዛል። ኮከሱ ከወንዶች ተባባሪ አባላት ጋር መስራቱ የሴቶችን እኩል ተሳትፎና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋጥ የሚያደርገውን ትግል ለማሳካት ወሳኝ ሚና ተጫውቷል። ኮከሱ ለወንድ ተባባሪ አባላት የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠትና የግንዛቤ መድረኮችን በማዘጋጀት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስለ ሥርዓተ-ፆታ ያለው ግንዛቤ በእጅጉ እንዲጎለብት እንዲሁም ምክር ቤቱ በሚሰራው ስራ ሁሉ ሥርዓተ-ፆታን ከግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል።

የተባባሪ ወንዶች አባላትን አስተዋጽኦ የኮከሱ አባላት እንደሚከተለው ይገልጹታል፦

“የእነርሱ እዚህ መግባት ጥቅሙ በተመረጡበት ወረዳም ሆነ ሌላ ቦታ ታች ወርደው ሲሰሩ እንቅስቃሴአቸው የሴቷን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል። ሴቶች ባልተመረጡበት ቦታ እንኳን ቢሆን ልክ እንደራሳቸው ነው የኮከሱን ሃሳብ ይዘው ሄደው የሚሰሩት፤ አምነውበት ነው የሚሰሩት። ስልጠናም ሲሰጥ፣ አጀንዳም ሲቀረጽ አምነው ስለገቡ በጣም ነው የሚያግዙን። ይህ ቢደረግ፣ ይህ ቢቀር ብለው በሀሳብ ራሱ ያግዙናል። ሕግ ላይ፣ ኮሚኒኬሽን ላይ እንዴት ሴቶችን ማብቃት ይቻላል? መድረክ ላይ እንዴት ሴቷ መናገር እንድትችል ማድረግ ይቻላል? የሚለውን አብረውን ነው የሚሰሩት። እነሱም ወደ ታች ሲወርዱ ቼክ ሊስት ይዘው ነው የሚሄዱት። ሴቶች ወደ ኮከሱ የሚቀርቡበትን ሁኔታ ለማስፋት በሚሰራው ስራ በጣም ጥሩ ይሳተፋሉ።” **(ወ/ሮ ወርቅነሽ ዋጀ)**

“አንድ አንድ ጊዜ ፓርላማ ላይ የሴቶች ጉዳይ ሲነሳ የሴቶች ብቻ ይሆናል። ለምሳሌ ጥያቄ ሲጠየቅ ብዙ ጊዜ ስለ ሴቶች የሚጠይቁ ሴቶች ናቸው። ሆኖም ከጊዜ በኋላ ፓርላማ ውስጥ የሴቶችን ጉዳይ ወንዶችም ማንሳት ጀምረዋል። ለምሳሌ አስፈጻሚው አካል አንድ የማፑቶ ስምምነት የተባለ ስምምነት ላይ ተስማምቶ ወደ ምክር ቤቱ አምጥቶ ነበር። ከስምምነቱ ጉዳዮች አንዱ የነበረው እንደ ውጭ ሀገራት ሴቶች በባሎቻቸው ስም መጠራት አለባቸው የሚል ነው። እያንዳንዱ ስምምነት ደግሞ በፓርላማ ካልጸደቀ ተግባራዊ አይሆንም፤ ጸድቆ የሀገሪቱ የሕግ አካል መሆን አለበት። ያንን አዋጅ አስፈፃሚው በሚኒስትሮች ምክር ቤት አጸድቆት ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ደርሷል። ምክር ቤቱ ግን አላጸደቀውም። እዚህ ላይ ወንዶች ተባባሪ አባላት ባያግዙን ኖሮ እኛ 38.8 (በመቶ) ነን ስለዚህ ስምምነቱ ይጸድቅ ነበር ማለት ነው። ሴቶች ወደ ሹመት ሲመጡም እኮ ሹመታቸው በምክር ቤት ነው የሚጸድቀው፤ ወንዶች ካላመኑ ምን ታደርጊያለሽ። ከ50 በመቶ በታች ስለሆንን ምንም ማድረግ አንችልም። ፓርቲውም አምኖብሽ በእጩነት ቢያቀርብሽ እነሱ ካላመኑ ምንም ዋጋ የለውም። ሚኒሰትሮች በፓርላማ ነው የሚሾሙት። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባሉ፤ ፓርላማ ያጸድቃል። የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች ስድስቱ ሴቶች በፓርላማ ነው የጸደቁት። ስለዚህ ወንዶች ሴቶቹ ይሰራሉ የሚል አስተሳሰብ ከሌላቸው ‘አናጸድቅም’ ቢሉስ፣ ‘የእሷን ሹመት ከምታጸድቁ ሌላ ሰው አምጡ ቢሉስ’ 50 በመቶ መሆን አለብን የሚባለው ለዚህ ነው የሚጠቅመው። ቢሆንም ግን አጋሮች እያበዛን፣ የሚደግፉሽ፣ አስተሳሰብሽን የሚጋሩሽ ወንዶች እየተፈጠሩ ካልሄዱ የኛም ቁጥር መጨመር ዋጋ ላይኖረው ይችላል።” **(የተከበሩ ወ/ሮ አበባ ዮሴፍ)**

## ኮከሱ በወንድ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ዕይታ

በተወካዮች ምክር ቤት የሴቶች ኮከስ አባላት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማስገኘት በሚያደርጉት ጥረት ብዙ የሚተባበሩ ወንድ የምክር ቤቱ አባላት ይገኛሉ። በምክር ቤቱ ካሉት 335 ወንድ አባላት ውስጥ 168ቱ ተባባሪ ናቸው። ይህም ሴቶችን የሚጠቅሙ ሕጎችንና ፖሊሲዎችን ከማጽደቅና ከመደገፍ አኳያ ትልቅ ሚና ይጫወታል። ወደ የምርጫ ጣቢያዎቻቸውም ሲሄዱ የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ይከታተላሉ።

“ኮከስ ውስጥ ተባባሪ አባል ነኝ። ኮከሱን አውቀዋለሁ፤ ጥሩ ነገር ይሰራል። እኔን ያውቁኛል፤ ሴቶች ሁሌም ከፊት እንዲሆኑ ነው የምፈልገው።

ለአመራርነት ቦታ ላይም ለሴቶች ቅድሚያ እንስጥ ነው የምለው። ምክንያቱም ሴት እኮ ሁሉን ስራ ነው የምትሰራው። ሴቶች ድርብርብ የሆነ ኃላፊነት አለባቸው። ለምሳሌ በቤተሰብ ውስጥ ተጨማሪ የስራ ጫና አለባቸው። በተጨማሪም በማህበረሰብና በስራም ጫና ይኖርባቸዋል። የወሊድ ፈቃድም ቢሆን አራት ወር መሰጠቱ በቂ አይደለም። ቢያንስ ስድስት ወር ቢሆን ይሻል ነበር። ስራን በተመለከተ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ስምንት ሰዓት መስራት የሚጠበቅባቸው ሲሆን ሴቶች ከዚህ በተጨማሪ ድርብርብ የሆነ የቤት ውስጥ ጫና አለባቸው። ይህን ሁሉ ስራ ሰርተው እንዴት እንደሚቋቋሙት አስገራሚ ነው። ወንዶች በሀገራችን ያለውን ማለትም ወንድ ኩሽና መድረስ ነውር ተደርጎ መቆጠርን በማስወገድ በቤት ውስጥ ያለን የሴቶች ጫና ሊካፈሉ ይገባል።:" **(የተከበሩ አቶ አብዱ ሙሴ አርቴ)**

"በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያሉ ሴት ተመራጮች ባሉበት ትልቅ ቦታ ላይ ሰብሰብ ብለው ያላቸውን አቅም አሟጠው መጠቀም እንዳለባቸው ይታመናል። በሴቶችና በወንዶች በኩል ያለውን ልዩነት ለማጥበብ ጠንካራ ስራዎች ይሰራሉ። እኔም ይህን አቅማቸውን አሟጠው መጠቀም እንዲችሉ የራሴን አስተዋጽኦ ለማበርከት በማሰብ ነው የኮከሱ ደጋፊ አባል የሆንኩት። በተለያዩ ባለሙያዎች አማካኝነት በኮከሱ የሚሰጡ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ወስጃለሁ። ኮከሱ በሴቶች ጉዳይ ላይ የተሻለ ግንዛቤ ፈጥሯል ብዬ አስባለሁ። አንዳንድ በቅርበት ለማውቃቸው ሴት አመራሮች ጥሩ አቅም እየፈጠረላቸው እንደሆነ እረዳለሁ። እኔ የንግድ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መሪ ነኝ። እዚያ ውስጥ ያሉ ሴቶች አስፈፃሚውን በመገምገም የሚመጡትን ሕጎችና ረቂቅ አዋጆችን በመመርመርና በመምራት ጭምር ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው። በምክር ቤታችን ከጊዜ ወደ ጊዜ የሴቶች አቅም እየተሻሻለ ነው። ከወንዶችም ወደ ተሻለ ደረጃ እየመጡ ነው የሚል እምነት አለኝ። መስክም ሲኬድ ጉዳዮችን በመመርመር ሪፖርትም ሲገመገም ሴቶች አይችሉም ተብሎ አይታሰብም። ሴቶች ብዙ ኃላፊነቶች አለባቸው። እነዚህን ሁሉ አጣጥመው ስራቸውን ይሰራሉ። ሴቶች የሚሰጣቸውን ተልዕኮ በብቃት፣ በጥራትና በሚጠበቅባቸው ጊዜ ውስጥ የማጠናቀቅ ስራ ላይ የተሻሉ ናቸው። ኃላፊነትም ሲወስዱ ጥሩ ምክንያት ፈጥሮ ነገሮችን የማዘግየትና የመሰላቸት ነገር አይንፀባረቅባቸውም፤ ቁርጠኛ ናቸው። ከአቅም በላይ ችግር ካላጋጠማቸው በቀር አይዘናጉም። የተሰጣቸውን ስራ አጠናቀው መስራት ባይችሉ እንኳን አሳማኝ ምክንያት ያቀርባሉ። ነገ እሰራዋለሁ በሚል ምክንያት አይደረድሩም። ይህ መገለጫቸው ነው። አንዳንድ ወንዶች ምክንያት ያበዛሉ፤ ነገሮችን በይደር የማየት ሁኔታ አለ። እኔም ጭምር ይደርሳል ብሎ ነገሮችን አቅልሎ የማየት ነገር አለብኝ። ግን ትንሽም ትልቅም ነገር በሰዓቱ መፈፀም አለበት። ቡድን የመምራት፣ አብሮ ያለውን የስራ ባልደረባ ቀርቦ የመምራት፣ ወደ ራስ የመሳብ ስጦታ አላቸው። አሁን የእኛን ኮሚቴ የምትሰበስበው ሴት ናት። የቡድን ስራው ማህበራዊ ግንኙነት በመፍጠር፣ በማሳመን፣ ተልዕኮዎች እንዳይንጠባጠቡ አድርጎ ኃላፊነትን የመወጣት ብቃቷ ከፍተኛ ነው። ስራ ላይ ወንዶች ትንሽ ትዕዛዝ የመስጠት ባህርይ አለን። ሴቶች ግን የማግባባት አቅምም አላቸው። ሰው ያከብራሉ፤ ትዕዛዝ ብቻ አይሰጡም። ችግርም ካለ ያዳምጣሉ፤ የማሳመን ጥበብ አላቸው። ወንዶች ሴቶች በየትኛውም የስራ መስክ ላይ ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ የሚል እምነት ሊኖራቸው ይገባል። ከተቻለም መደገፍ፣ አለን የሚሉትን ልምድ ማካፈል አለባቸው። በተፈጥሮ ለወንዶች ብቻ የተሰጠ የተለየ ችሎታ የለም። ሁሉም ሰው ቀስ በቀስ በሚያደርገው እንቅስቃሴና በተሰጠው እድል ነው ልምድን የሚያዳብረው። ስለዚህ ወንዶች አለን የምንላቸውን ልምዶች ለሴት እህቶቻችን ማካፈል አለብን። እኛም ከእነርሱ ብዙ መማር እንችላለን። ለምሳሌ ሴቶች በአመራርነት ያላቸውን ጥበብ ማየት እንችላለን። ወንዶች አንዳንድ ጊዜ በቀላል መንገድ መፍታት የሚቻልን ጉዳይ ወደ ቁጣ እንወስዳለን። ሴቶች ግን በቀላሉ ይህን የመፍታት ችሎታ አላቸው። ይህን ከእነርሱ ልንወስድ እንችላለን። እኛ ያለንን ካካፈልን፣ ወንዶች ለሴት እህቶቻችን ያለንን ልምድ ማካፈል ካልቻልን ቢያንስ እነሱን አለማደናቀፍ። 'አይችሉም' የሚል ኋላ ቀር አስተሳሰብ አለማራመድ ይኖርብናል።

ሴት እህቶችንም ራሳቸውን ማውጣት አለባቸው። የሚያገኙትን እድል በአግባቡ መጠቀም አለባቸው። እኔ ጋር የነበሩ ሁለት ሴቶች የንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆነው የሚሰሩ ነበሩ። እኔ ሰብሳቢ ሆኜ በምመራበት ጊዜ በምሰጣቸው ስራ በጣም ጎበዞች ስለነበሩ ሁሌ እናንተ አመራር መሆን አለባችሁ እላቸዋለሁ። የመምራት አቅም አላችሁ፤ በየትኛውም ቦታ ላይ አልችልም እንዳትሉ፤ ወንዶች ናቸው ሁሉም ቦታ ላይ የሚሽቀዳደሙት የሚለውን አስተሳሰብ ጣሉት እላለሁ። ሴቶች ከወንዶች አንሰው ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል የሚል አመለከከትም ትክክል አይደለም። ወንዶች ከየት አመጡት? ይህ መቅረት አለበት። እዚህ ላይ ከተሰራ ውጤታማ እንሆናለን። የተሰጣቸውን መብቶችና ጥቅሞች የማስከበር ስራ ላይ ገና ነን። ከሕግ አንፃር መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች አሉ። ሴቶች በኢኮኖሚ መዳበር፣ በፖለቲካው መብቃት፣ የማንንም ፈቃድ የሚጠይቁበት ነገር መሆን የለበትም።” **(የተከበሩ አቶ ዘውዱ ከበደ፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ንግድ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ)**

“የኮከሱ ተባባሪ አባል ነኝ። በኮከሱ መድረኮች ላይ ያለኝን ሀሳብ እሰጣለሁ። የሚያስፈልጋቸውን ነገር በተቻለ አቅም ለማሟላት ዕቅዳቸው ተግባራዊ እንዲሆን የበኩሌን አደርጋለሁ። የወንዶች የበላይነት እንዲቀር፣ ኋላ ቀር አስተሳሰብ እንዲወገድ፣ እኩል መሆናቸውን በተግባር ለማረጋገጥ፣ የወጡ ዕቅዶች ተግባራዊ በማድረግ የሴቶችን ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት ከፍ ለማድረግ የራሳችንን አስተዋጽኦ እናደርጋለን። ዋናው ነገር እንደ ኮከስ በተጨባጭ አቅሙ እንዲጠነክር በማድረግ ዕቅዳቸው ተግባራዊ እንዲሆን በምክር ቤት ደረጃ ከማጽደቅ ጀምረን አሁን ራሱን የቻለ ጠንካራ አደረጃጀት ተፈጥሯል። ይህን በማየቴ ደስተኛ ነኝ። ከኮከሱ ጋር የያዝናቸው ተግባራት እንዳለ ሆኖ በምክር ቤታችን የተሰጠው ትኩረትና ከተያዘው ዕቅድ አንጻር ሴቶች በአመራር ቦታ ላይ ውጤታማ እንዲሆኑ በማድረግ በኩል ጥሩ እየተሰራ ነው። ሴቶች ወሳኝ ተቋማትን ነው እየመሩ ያሉት። ለምሳሌ የበጀትና ፕላን፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ ሙያና ከፍተኛ ትምህርት፣ የማህበራዊ ጉዳይና ህጻናት ጉዳይን ወዘተ. ቁልፍ ቁልፉን እየመሩ ያሉት እነሱ ናቸው። በዚህ ረገድ ጥሩ ስራ እየተሰራ ነው። ይህም የሆነው ራሳቸውን በትምህርት በማብቃታቸውና በስራ እየበሰሉ በመምጣታቸው ነው። ስራን አጥብቆ በመያዝ፣ በሥነ-ምግባርና በኃላፊነት ስራን ቆጥሮ በመስጠት፣ በመድረክ አያያዝ ሁሉ በጣም ጎበዝ ናቸው። ፓርላማው ትልቁ ዕቅድ የሴቶችን ተሳትፎ ከቀበሌ እስከ ፌዴራል እኩል ማምጣት ነው። በቁጥርም በቀጣይ የሴቶችን ተሳትፎ 50 በመቶ ማድረግ ነው። ይህን ክልሎች ደርሰውበታል። ፌዴራልም እንደዚያው መምጣት አለበት። ለምሳሌ ትግራይ ላይ በምክር ቤትም፣ በአስፈጻሚ ደረጃም፣ በወረዳም ሳይቀር 50 በመቶ ነው። ግማሽ አካል በሌላ ተፅዕኖ መኖር የለበትም። በትምህርትም በአስተሳሰብም እኩል ተሳትፎ ለማምጣት መስራት አለብን። ለምንስ ከ50 (በመቶ) አይበልጡም? ስለዚህ አስተሳሰቡ ነው መቃኘት ያለበት እንጂ ይችላሉ።” **(የተከበሩ አቶ ገብረ እግዚአብሔር አርአርያ፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዲኤታ)**

”ኮከሱ እንደ አንድ የምክር ቤት ክንፍ ከሁሉም የተሻለ ነው። ቋሚ ኮሚቴዎችም በራሳቸው ጠንካራ ናቸው። ነገር ግን ይህ ክንፍ ቢጠናከር ምክር ቤቱን ይበልጥ ያግዛል ብዬ አምናለሁ። ኮከሱ በየጊዜው እያደገ ነው የመጣው። ስልጠናዎች እንዲመቻቹ ከተለያዩ አካላት ጋር ይሰራሉ። ኮከሱ ያዘጋጀው ‘መሪነት ከምክር ቤት አኳያ’ በሚል የተሰጠ ስልጠና ነበር። በዚያ ስልጠና ምንም እንኳን የተማርኩት ‘ሊደር ሽፕ’ ቢሆንም እራሴን እንዳሳድግ፣ እኔ እንደ መሪ እንዴት ነው የምመራው? እንዴት ነው እየሰራሁ ያለሁት? በራሴ ተቋም ውስጥ የሚለውን ለማወቅ ጠቅሞኛል። በዩናይትድ ኔሽን ዴቨሎፕመንት ፕሮግራም ድጋፍ የተዘጋጀው ‘ሰላምና የሴቶች ሚና’ የሚል ስልጠናም ወስጃለሁ። በእሱም የራሴን እውቀት አግኝቻለሁ። ሴቶች በሰላም እጦት ተጠቂ ናቸው። ሰላምም እንዲመጣ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ መሆናቸውንና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ግንዛቤን የመፍጠር ስራ መስራት እንደሚያስፈልግ ግንዛቤ የፈጠረ ስልጠና ነበር። ይህም በራሴ የአመለካከት ለውጥ እንዳመጣና ተጨማሪ እውቀት እንዳዳብር

አድርጎኛል። ኮከሱ የምንሰራውን ስራ በመተባበር የሚሰራ ነው። የኮከሱ ወንድ ተባባሪ አባላት እራሳቸው በኮከሱ ብዙ ይጠቀማሉ። በእኛ በኩል ሀሳብ እንሰጣቸዋለን። የሚያመጧቸው አጀንዳዎች በምክር ቤቱ ተቀባይነት እንዲያገኙ እናግዛቸዋለን። ለምሳሌ የአቅም ግንባታ አጀንዳ ቀርጸው ያመጣሉ። እነዚህ አጀንዳዎች ጠቃሚ ስለሆኑ በተለያዩ ሰበቦች እንዳይደናቀፉ የምክር ቤቱ የበላይ አመራር ሊፈቅድ ይገባል ብለን ሀሳብ እናቀርባለን። አቅም ግንባታ ስራው የተለያየ ቦታ ከተለያዩ አካላት ጋር የሚሰራ በመሆኑ ፕሮግራም እንዲያዝላቸው ሁኔታዎች እንዲመቻቹላቸው እናደርጋለን። የስልጠና ጊዜያቸው ከምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ ጋር እንደይጋጭም የማመቻቸት ስራ እንሰራለን። መልዕክትም ለሰልጣኞች በማስተላለፍ እናግዛለን። ይህ የሚጠቅመው ለእነሱ ብቻ አይደለም፤ ለእኛም ነው። ምክር ቤቱም ተጠቃሚ ነው። ምክር ቤቱ በመንግስት የተሰጠው ተልዕኮ አለ። ያንን ተልዕኮ ሊያሳካ የሚችለው የአባላት ተሳትፎ ነው። ስለዚህ ሴቶች እዚህ ላይ ትልቁን ሚና ይጫወታሉ።መንግስት ያስቀመጠውን ፕሮግራም ለማስፈጸም ይህን ኃይል መጠቀም የግድ ነው።

ሁለተኛ እኔ የተመደብኩበት ተልዕኮ በእነዚህ ሰዎች አማካኝነት ሳይደነቃቀፍ በታቀደው ልክ ስራዎች እንዲሰሩ ሊያደርግ ይችላል። ይህ የተደራጀ ኃይል ነው። ሌላ ቦታ ይህ ኃይል ጠፍቶ ነው ነገሮች የሚንጠባጠቡትና በተፈለገው መንገድ የማይሄዱት። እዚህ ምክር ቤት ውስጥ ግን በተቻለ መጠን በዓመት ውስጥ የታቀዱት እንዲጸድቁ በማድረግ ስራዎች ሳይደነቃቀፉ በጥሩ ሁኔታ እንዲሄዱ አድርገናል። በዚህ ውስጥ የሴቶች ሚና ትልቅ ነበር። ስለዚህ ይህን አደረጃጀት ስንጠቀም በአንድ በኩል የተመደብኩበትን አላማ እንዳሳካ ይረዳኛል፤ በሌላ መልኩ ደግሞ በግለሰብ ደረጃ በሚያዘጋጁት መድረኮች ላይ የማገኘው እውቀት ለቀጣይ ህይወቴ ይረዳኛል። ለዚያ ነው ቁርጠኛ ሆኜ እነሱ ጋር የምሰራው። ሁለተኛ ምክር ቤቱን በማንቀሳቀስ አንድ መግባባት ፈጥሮ እንዲንቀሳቀስም የራሱ አስተዋጽኦ አድርጓል። አባላትን በመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ዙሪያ ማንቀሳቀስ ከፈለግኩኝ በዚህ በተደራጀ ኃይል አማካኝነት መጠቀም እችላለሁ ማለት ነው። ለምሳሌ በዚህ ምክር ቤት ውስጥ አንድ ትልቅ አከራካሪ አዋጅ ነበር፤ መድኃኒትና መጠጥን የሚመለከት። የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በስፋት ተሳትፈውበታል። ይህን የመጠጥ ማስታወቂያ በሚዲያ እንዳይነገር የሚከለክለውን አዋጅ ስናጸድቅ የሴቶች ሚና ትልቅ ነበር። (የመጠጥ ማስታወቂያ ) አስፈላጊ አይደለም በሚል ሲሟገቱ የነበሩት ሴቶች ናቸው። እኔ ደግሞ ያ አዋጅ አዋጅ ሆኖ የህብረተሰብን ጥቅም ሊያስጠብቅ በሚችል መልኩ እንዲወጣ ነበር የምፈልገው። ስለዚህ በምክር ቤቱ ያሉ ሴቶችን በማሳተፍና አዋጁ አዋጅ ሆኖ እንዲወጣ ማድረጌ ለእኔ አንዱ ስኬት ነው ብዬ እንደ ምሳሌ የማነሳው ነገር ነው። ይህ አዋጅ በሴቶች ህይወት ላይ ለውጥ ያመጣል። አዋጁ እንዲጸድቅ የተፈለገው ማህበራዊ ቀውስን እንዲከላከል ነው። የዚህ ማህበራዊ ቀውስ ቀዳሚ ተጠቂ ደግሞ ሴቶች ናቸው። " **(የተከበሩ አቶ ጫላ ለሚ፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ተጠሪ ሚኒስቴር ዲኤታ)**

# የመጪ ጊዜ ዕቅድ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሴት አባላት ኮከስ ከአስርተ ዓመታት በላይ የሚታይና የሚቆጠር ውጤት በማስመዝገቡ ስኬታማ ነበር ለማለት ያስደፍራል። ይሁን እንጂ በሀገሪቱ በሥርዓተ-ፆታዊ እኩልነት ረገድ ካለው ተጨባጭ ሁኔታና "ሥርዓተ-ፆታዊ እኩልነት የተረጋገጠበት ዲሞክራሲያዊና የበለፀገች ኢትዮጵያን ተገንብታ ማየት" ከሚለው የኮከሱ ራዕይ አንፃር ሲተያይ ኮከሱ ያስመዘገባቸውን ስኬቶች አጠናክሮ ከመቀጠል ባሻገር ብዙ መስራት ይጠበቅበታል።

ኮከሱ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ የሚጠበቅበትን ስራዎች ቅደም ተከተል አውጥቶ መስራት እንዳለበት የኮከሱ አባላት ይመክራሉ።

"የኢትዮጵያ ሴቶች በፖለቲካ እኩል እንዲሳተፉና ወደ ውሳኔ ሰጪነት እንዲመጡ አቅም እንዲፈጥሩ በትምህርት፣ በጤና፣ በኢኮኖሚው ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆናቸው ይረጋገጥ ብለን በየደረጃው መስራት ይጠበቅብናል። ከሰራንበት ይቻላል! ሁሉን በአንዴ አይደለም፤ ግን ቀዳሚውን ማየት አለብን። ለምሳሌ ሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለማድረግ ምን መደረግ አለበት? የሀገሪቱ እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (ጂቲፒ) ላይ 30 በመቶ ሴቶችን ተጠቃሚ አደርጋለሁ ይላል። ነገር ግን ምን ያህል ሴቶች በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅተው ይንቀሳቀሳሉ? ስንት እማ-ወራዎች በግብርናው ተጠቅመዋል? ስንት ሴቶች ተማሩ? ስራ የፈጠሩ ስንት ሴቶች አሉ? በየአካባቢው ያለች የሴት አመራር እንዴት ሴቷን አደራጅታ ስራ ትፈጥራለች? የመሳሰሉትን በማለት ቅደም ተከተል ማስቀመጥ ነው። በተጨማሪም የግብርና ፓኬጅ 30 በመቶ ሴቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ ይላል። እውነት በእያንዳንዱ ክልል ውስጥ ሴቶች ተጠቃሚ ናቸው ወይ? ለምሳሌ በየአካባቢው የመሬት ባለቤት ቢሆኑም ባሎቻቸው መሬቶቻቸውን የሚነጥቋቸው አሉ። ንብረታቸውንና መሬታቸውን እንዳይነጠቁ መብታቸውን ማሳወቅ የመሳሰሉት ላይ ሊሰራበት ይገባል።"**(ሲስተር መብራት ታደሰ)**

የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ እና ውሳኔ ሰጪነት ማሳደግ ኮከሱ ሊሰራባቸው ከሚገቡ ተቀዳሚ ጉዳዮች አንዱ ተፅዕኖ በማሳደር ሴቶች በፖለቲካ እንዲሳተፉና ወደ ውሳኔ ሰጪነት እንዲመጡ ማድረግ ነው። ከእነዚህም እርምጃዎች መካከል መንግስት፣ ገዢው ፓርቲ እና ተፎካካሪ የፓለቲካ ፓርቲዎች የሴቶችን ተሳታፊነት እንዲያሳድጉ ተፅዕኖ ማሳደር ዋነኛው ነው።

"መንግስት በሁለተኛው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ላይ 30 በመቶ ውሳኔ ሰጪነት ላይ ሴቶችን አመጣለሁ ብሎ ነበር ። ይህ በፌደራል በአስፈጻሚው አካል በካቢኔ ደረጃ 50 በመቶ ደርሷል። የመዘለቁን ጉዳይ ሴቶች ራሳቸውና መንግስት የሚያውቀው ቢሆንም እድል የተሰጣት ሴት ኃላፊነቷን በብቃት ለመወጣት እራስዋን ማብቃት አለባት። አብዛኛውን ጊዜ አመራር ላይ ባሉ ሴቶች ላይ ድካማቸውን ማጉላት ይታያል። ከዚህ የተነሣ የተቀመጠውን ራዕይና ተልእኮ የማስፈፀም ውጤት ሲገመገም በሰበብ አስባቡ ሴቶችን ከስልጣን ማንሳት ሊኖር ይችላል። ከክልል ጀምሮ ወደ ታች ባለው የውሳኔ ሰጪነት ቦታዎች ላይ 30 በመቶ የሴቶች ውክልና እስካሁን ገና ነው። በክልል ደረጃ በአስፈፃሚው አካል ውስጥ ሴቶች በስልጣን ላይ ያላቸው ውክልና ከ14 እስከ 22 በመቶ ሲሆን ይህ የሚያሳየው ውክልናቸው ማነሱን ነው። ይህ እንዲሻሻል የእቅዳችን አንድ አካል አድርገን እየሰራን ነው። በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል ለውጦች አሉ። ማንም ቢመጣ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስተርም ቢመጡ ጠንከር አድርገን ነው የምንመልሰው (ቻሌንጅ የምናደርገው)። ሕገ-መንግስታችን መነሻችን ነው፤ የሴቶች ፖሊሲ መነሻችን ነው፤ በሴቶች ተጠቃሚነት

ዙርያ የወጡ ሕጎችና ደንቦች መነሻችን ናቸው። ሕጉን ተስማምተን ከነሱ ጋር ስላስቀመጥን ሕጉን የመፈፀም ግዴታ አለባቸው። በዚህ ጉዳይ ቢያኮርፉ ቢያጉረመርሙ እንኳን እኛን ማስቆም አይችሉም። እኛ አቅም በፈቀደ መጠን እየሄድን ቢሆንም ግን 'ሴቶች ይችላሉ'፤ 'ይመራሉ'፤ እንዲሁም 'ብዙ የበቁ ሴቶች አሉ' የሚለው አስተሳሰብ ብዙ ወንዶች ጋር ዝቅተኛ ነው:: ከሕግ አስፈፃሚዎች ጋር ስናይ አሁንም በነበረው አስተሳሰብ የወንዶች የበላይነት አልተሰበረም። እምንፈልገው ደረጃ ላይ ለመድረስ ገና ብዙ ስራ ይጠይቃል። ይህ የፖለቲካ ውሳኔ ጭምር ነው።" **(የተከበሩ ወ/ሮ ፋንታዬ ባቡሎ)**

"የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሳደግ ሀገራት የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። አንዳንዶቹ ኮታ ስርዓት በመጠቀም ሲሆን አንዳንድ ሀገራት ግን የኮታን አስፈላጊነት አይስማሙበትም። ለምሳሌ በዓለም የኮታ ሲስተምን በመጠቀም የሴቶችን የፓርላማ ተሳትፎ ካሳደጉት ሀገራት ለመጥቀስ ያህል፡-ሩዋንዳ 63.8 በመቶ፣ ቦሊቪያ 53.1 በመቶ፣ አንዲራ 50 በመቶ፣ ኩባ 48.9 በመቶ፣ ሲሽልስ 43.8 በመቶ፣ ሴኔጋል 42.7 በመቶ፣ ኢኳዶር 41.6 በመቶ እና ደቡብ አፍሪካ 41.5 በመቶ ደርሰዋል። እነኝህ ሀገራት የኮታ ስርዓት ተጠቅመው ነው እዚህ ከፍተኛ ቁጥር ላይ የደረሱት። እኛ የፓርቲ ፍቃደኝነት ነው የምንጠቀመው። እያንዳንዱ ፖለቲካ ፓርቲ ይህን ያህል ሴት አሳትፋለሁ ብሎ ነው ለምርጫ የሚያቀርባቸው። የኮታን ጥቅምና ጉዳት በተመለከተ በዘርፉ ያሉ ምሁራን እራሱ በአንድ ሀሳብ ላይ አልተስማሙም። አንዳንዶቹ ኮታ የምንጠቀም ከሆነ ብቁ ሰው ላናገኝ እንችላለን ሲሉ፤ አንዳንዶች ደግሞ በዚህ ሀሳብ አይስማሙም። የጥራት ችግር አይደለም፤ መጀመርያውኑ ለሴቶች ዕድሉ ባለመሰጠቱ ነው ይላሉ። ፓርቲ 'ኮሚትመንቱም' መጥፎ አይደለም ግን አስገዳጅ ሁኔታዎች ቢኖሩት ለምሳሌ በምርጫ ቦርድ ሕግ ውስጥ ፓርቲዎች ሴቶችን በብዛት እንዲያሳትፉ ሊያበረታቷቸው የሚችሉ ማበረታቻ ዘዴዎችን በምርጫ ሕጉ ማካተት አስፈላጊ ይመስልኛል። 'ፓርቲዎችን ሊያበረታታ የሚችል ምንድን ነው' የሚለውን በማጥናት መተግበር፤ ፓርቲዎች ሴቶችን እንዲያመጡ በቂ በጀት መመደብ ሊሆን ይችላል። ሴቶችን ለማምጣት ባለው ፍላጎት ልክ ሌላ አስፈላጊ ግብአቶችን ማሟላት ሊሆን ይችላል፤ ብቻ በምርጫ ሕጋችን እና በፖለቲካ ፓርቲዎች ፖሊሲ ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ ሊያሳድግ የሚችል አሰራር መኖሩን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው ብየ አስባለሁ። በቀጣይ ደግሞ ምን መሆን አለበት ለሚለው ሀገራችን እንደሌሎች ሀገራት በከፍተኛ ሁኔታ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ በፓርላማ ያረጋገጡበትን ዘዴ ብንከተል ጥሩ ነው። ምክንያቱም ያለ ኮታ ተሳትፎአችን ያደገው በፌደራል ፓርላማ ውስጥ ነው። በአስፈፃሚ ደረጃ አሁን 50 በመቶ ደርሶ ያየነው የሴቶች ተሳትፎ በጠቅላይ ሚኒስትራችን የፖለቲካ ቁርጠኝነትና በሴቶች ላይ ያላቸውን ፅኑ እምነት የሚያመላክት እንጂ ነገ ሰዎች ሲቀየሩ የሚቀር ሊሆን ይችላል። ሲስተም መኖር አለበት። ወይ ኮታ ሲስተም መጠቀም አሊያም ለፓርቲዎች አስገዳጅ ሕግ ማካተት። እንደኔ እምነት ለተወሰኑ ጊዚያት 'ጀንደር ባላንስ' እስኪመጣ ድረስ የኮታ ሲስተም የሚለውን አሰራር ብንከተል ጥሩ ነው ብዬ አስባለሁ።" **(የተከበሩ ወ/ሮ ነጮቴ ፍላቴ)**

## ተደራሽነትን ማስፋት እና ተጠያቂነትን ማጠናከር

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሴት አባላት ኮከስ ማጠናከር ካለበት ስራዎች መካከል አንዱ ተደራሽነትን ማስፋትና ተጠያቂነትን ማጠናከር ነው። የኮከሱ አባላት በሕዝብ ተመርጠው በምክር ቤት ውስጥ የወከላቸው ማህበረሰብ ድምጽ እንደመሆናቸው ከወከላቸው ሕዝብ ጋር ቅርብና ጠንካራ ግንኙነት መፍጠር አለባቸው። ስለዚህም ኮከሱ ግንኙነቱን ከሕዝብ ጋር ማጠናከሩ አባላቱ የወከሉትን ማህበረሰብ ፍላጎት እንዲያውቁ፣ ተሳትፏቸውን እንዲያነሳሳና እንዲያነቃቃ፣ ለፍላጎቶቻቸው ምላሽ እንዲሰጥ እንዲሁም ሕዝብን በአግባቡ እንዲያገለግል ያስችለዋል። ከዚህም ባሻገር ለሕዝብ ተጠያቂነቱን እንዲያጠናክር ይረዳዋል። ለዚህ ደግሞ ኮከሱ የጀርባ አጥንት ከሆኑት የክልል ፎረሞች ጋር ያለውን ግንኙነት ይበልጥ ማጎልበት ይገባዋል።

ኮከሱ ይህን ለማሳካት እንደ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና ዜና መጽሄት ያሉ ነባር መገናኛ ብዙሃንንና እንደ ተንቀሳቃሽ ስልክ መተግበሪያዎችና ማህበራዊ ሚዲያዎች የመሳሰሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የመራጩን ማህበረሰብ ድምጽ

በመደበኛነት መስማትና ምላሽ መስጠት ላይ ጠንካራ የቤት ስራ ይጠብቀዋል። ኮከሱ ተደራሽነቱን በማስፋት ዙሪያ አባላቱ አስተያዬታቸውን ሰጥተዋል።

“ኬንያ ውስጥ አንድ ተሞክሮ አይቼ ነበር። ቅዳሜና እሁድ ላይ የማህበረሰብ ሬዲዮ ፕሮግራም አላቸው። በዚያ በደቡብ ክልል በሳምንት አንድ ቀን በደቡብ ሬዲዮ ይተላለፋል። ኮከሱን እንዲህ አድርጎ ማደራጀት ይቻላል ብዬ አስባለሁ። ሴቷ ብዙም መረጃ ላታገኝ ትችላለች፤ ግን ታች ድረስ ወርዶ ቢሰራ ተደራሽነቱን ቢያሰፋ፣ ኔትወርክ ፈጥሮ የመስራት ነገር ቢፈጠር ጥሩ ይመስለኛል። አንድ ችግር ሲፈታ ለሌላው አስተማሪ ስለሚሆን አንድ ተጠቃሽ ሴት ችግሯን ለመፍታት የሄደችበት ርቀት ተገልጾ ሌሎች ሴቶች ያንን አይተው ከዚያ ችግር ነፃ እንዲወጡ ማድረግ ይቻላል። ኮከሱ የሰራቸውን ስራዎች ለሌላው ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ ይኖርበታል። በየዓመቱ ያከናውናቸውን ተግባራት ሌሎች እንዲያውቁትና እንዲማርባቸው ማድረግ አለበት። ለዚህ ደግሞ ተነሳሽነት ሊኖር ይገባል፤ ሰፋ አድርጎ ማቀድ ያስፈልጋል።” **(የተከበሩ ወ/ሪት አንችናሉ ይግዛው ተፈሪ)**

“የኮከሱ ስራ ሰፍቶ ክልል ምክር ቤትም ስንሄድ ይሄ ኮከስ እዚያ መገኘት አለበት። እዚህ ሲጠናከር እዚያም የሚጠናከሩ ስራዎች ቢኖሩ ጥሩ ነው። እዚህ ፓርላማ ብዙ ሴቶችን እንፈልጋለን ስንል ታች ያለውን ካላጠናከርን ከየት ይመጣል። ምክንያቱም ከታች ነው ወደ ላይ የሚመጡት። እኛም በአካል ወደ ሕዝቡ እየሄድን ተምሳሌት መሆን አለብን። ለሴት ተማሪዎች ተምሳሌት ሊሆኑ የሚችሉ የፓርላማ አባላት ወይም ደግሞ አመራሮችን ማየት እነሱም እዛ ቦታ እንዲደርሱ ያነሳሳቸዋል። ስለአመራር ማስተማር አለብን። ከክልል ምክር ቤት አባላት ጋር ብቻ ሳይሆን ከዚያ ያለፈ ትምህርት ቤት ያሉ ሴቶችም እዚያ እንደርሳለን ብለው እንዲያስቡ የሚያደርጋቸውን ስራ መስራት ይቻላል። ለምሳሌ ፌዴራል ላይ ያለውን ከፌዴራል ትምህርት ቤቶች ጋር መስራት ይቻላል። በተለይ ለሴቶች ስልጠና መስጠት፣ ብሮሸሮች አዘጋጅቶ ኮከሱ ምን እየሰራ እንደሆነ ማሳወቅ ተጠቃሽ ዘዴዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ይሄ ወጣት ሴቶችም ወደ አመራር እንዲመጡ ተስፋ ይፈጥራል ብዬ አስባለሁ። ከዚያ ያለፈ ደግሞ በካሪኩለም ውስጥ ብናካትት ለምሳሌ ብቁ የሆኑ ሴቶችን ታሪክ በካሪኩለም ውስጥ ብንጨምርበት መሰረቱ ታች ስለሆነ ከትምህርት ቤት ጀምሮ ልጆችን ማብቃት እንችላለን። ሴት ተማሪዎች ሴቶች መሪ መሆን ይችላሉ የሚል እንዲሁም ሀገሪቱ በሴቶች መቀየር ትችላለች የሚል ሀሳብ ያድርባቸዋል። ይህ ማለት እዚህ ያለን ብቻ ተጠናክረን ፓርላማ ውስጥ ብቻ ያለውን የውሳኔ መስጫ ቦታ መያዛችን ብቻ በቂ አይደለም። ቀጣይ ከክልል ምክር ቤቶችና ከትምህርት ቤቶች ጋር መስራት እንዳለብን ነው የሚሰማኝ ።” **(የተከበሩ ወ/ሮ ነጮቴ ፍላቴ)**

## የአቅም ግንባታ ስራን ማጠናከር

ምንም እንኳን ረጅምና አጭር ጊዜ ስልጠናዎችን መስጠትና አቅም መገንባት ኮከሱ ተጨባጭ ውጤት ካስመዘገበባቸው ስራዎች አንዱ ቢሆንም ወደፊት ኮከሱ የሚያዘጋጃቸው ስልጠናዎች ተከታታይነትና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ተደርጎ አስቀድመው መታቀድ እንዲሁም ውጤታማነታቸው በክትትልና በምዘና መረጋገጥ ይኖርባቸዋል። ኮከሱ ይህን ማድረጉ በስልጠና አማካኝነት የሚያካሂደው የአቅም ግንባታ ስራ ተጨባጭ ውጤት እንዲያመጣ ይበልጥ ያስችለዋል።

በተጨማሪ ኮከሱ ከተለያዩ ሀገራት የሴቶች ኮከሶች ልምድ መቅሰምና የተገኙ ተሞክሮዎችን ስርዓት ዘርግቶ ተግባር ላይ ማዋል ቢችል ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን ያግዛል።

በአጠቃላይ የኮከሱ ስራና አስተዋጾ በተለያዩ ዘርፎች የሚታይ ነዉ። የሴቶችን መብት፣ እኩልነትና ተሳታፊነት ከማረጋገጥ አኳያ የተጫወተዉ ሚና ጉልህ ነዉ። በመሆኑም ወደፊት የኮከሱን ስራ አጠናክሮ ለመጪዉ ትውልድ የተሻለን ሀገርና ስርዓት ለማዉረስ ተግቶ መስራቱን ይቀጥላል።

# አባሪዎች

### አባሪ 1. የቃላት መፍቻ

**መንግስት፡-** የአንድ ሀገር ሕዝብና ግዛት መስተዳድር /ከፍተኛ ፖለቲካዊ ድርጅት

**ገዢ ፓርቲ፡-** ሀገራዊ ምርጫን አሸንፎ ለማስተዳደር ኃላፊነትን የተረከበ የፖለቲካ ድርጅት

**ተፎካካሪ ፓርቲ፡-** ከገዢ ፓርቲ ዉጪ የሆነ ተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅት

**የተወካዮች ምክር ቤት፡-** ከተላያዩ የሀገሪቷ ክፍል ተመርጠዉ የመንግስት የሕግ አዉጪ አካልን የሚመሰርቱ መማክርት ሸንጎ

**የምክር ቤት አባል/ ተወካይ/ ተመራጭ፡-** አንድን የምርጫ ክልል በሕዝብ ተመርጦ/ጣ እዚያ በመወከል የተወካዮች ምክር ቤት አባል የሆነ/ች

ሥርዓተ-ፆታ፡- በፆታ ላይ የተመሰረቱ የእኩልነት፣ የመብት፣ የደህንነትና የተሳታፊነት ጉዳዮችን የሚጠቀልል ዘርፍ

**ኮከስ፡-** ለተወሰነ አላማ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተቋቋመ አደረጃጀት(ማህበር)

**የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሴት ተመራጮች ኮከስ፡-** የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሴት አባላትና ተባባሪ ወንድ አባላት አደረጃጀት (ማህበር)

የክልል ፎረም፡- የክልል ምክር ቤት ኮከስ

**የሴቶች ኮከሶች መድረክ፡-** በሴቶች ጉዳይ ላይ የሚሰራዉ በተወካዮች ምክር ቤት ስር የተቋቋመ አደረጃጀት ከክልል አቻዎቹ ጋር የሚያደርገዉ ዉይይት

**የአፈጉባኤ ፎረም መድረክ፡-** የተወካዮች ምክር ቤት መሪ ባለበት የሚደረግ የክልል ምክር ቤቶች ዉይይት

**አፈጉባኤ፡-** በብዙ ሰዎች ስም ኃላፊነት ጉባኤዉን ወክሎ የሚናገር የጉባኤው አለቃ፣ ተጠሪ፣ መሪ፣ ስነ-ስርዓት አስከባሪ

**አስፈፃሚ አካላት/መስሪያ ቤት፡-** ሕግ፣ መመሪያ፣ ጉዳይ ተግባራዊ የሚያደርግ/የሚያስደርግ የመንግስት አካል/ ሕግ አስፈጻሚ አካላት

**የምርጫ ክልል፡-** በምርጫ ጊዜ ተወዳዳሪዎች ተመርጠዉ ለመወከል የሚወዳደሩበት የአስተዳደር ክፍል

**የምርጫ ጣቢያ፡-** በምርጫ ጊዜ ዜጎች ድምጻቸዉን ለመስጠት የሚሄዱበት ስፍራ

**አደረጃጀት፡-** በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ የተመሰረቱ መዋቅሮች

**ዘርፎች፡-** ክፍል/ወገን/የስራ መደብ

**ቋሚ ኮሚቴ፡-** በተለዩ ጉዳዮች ላይ የሚመክር የማይፈርስ የተመራጮች ቡድን

**የመስክ ምልከታ፡-** የስራ ሂደቶችን ለመገምገም ከመደበኛ ስራዉ ርቆ ስራዉ በሚከናወንበት ቦታ በመገኘት የሚደረግ ጉብኝት

**ዳሰሳ፡-** የተሰራን ስራ መቃኘትና መገምገም

የተጽዕኖ ግምገማ፡- የአንድን ድርጊት ወይም ዉሳኔ ዉጤት ምዘና

**አቅም ግንባታ፡-** ችሎታን፣ እዉቀትን ወይም ክህሎትን ማዳበር

**ውትወታ/ተሟጋችነት፡-** ጥብቅና መቆም ወይም አቋም ይዞ መከራከር

**ክትትል፡-** የስራ ሂደትንና ክንዉንን መገምገም

ተባባሪ ወንድ፡- የኮከሱን ስራና ግቦች ለማሳካት የሚረዳ/ የሚያግዝ ወንድ የተወካዮች ምክር ቤት አባል

**መረጃ፡-** ስለ አንድ ድርጊት/ሁኔታየሚጠቁም የቃል ወይም የጽሁፍ ማስረጃ

**ማህበራዊ ኃላፊነት፡-** የአንድን ህብረተሰብ ፍላጎት ማዕከል ማድረግ

**ትስስር፡-** የጋራ ግብን ለማሳካት በተላያዩ እርከንና ደረጃ ላይ በሚገኙ አካላት መካከል የሚደረግ ትብብር

**የከተማ መስተዳድር፡-** በክልሎች ስር የማይተዳደሩ፣ ራስ ገዝ ከተሞች

**ፍትሃዊ ተጠቃሚነት፡-** ትክክል/ሕግን የተከተለ እና ሁሉን የሚያሳትፍ የአግልግሎት አጠቃቀም

**የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የድርጊት መርሀ ግብር፡-** ለሁሉም ሰዉ የሚገቡ መብቶችን ለማስከበር በቅደም ተከተል የተዘጋጀ የስራ እቅድ

**የማፑቶ ስምምነት፡-** በአፍሪካ ሴቶች መብትና ሁኔታ ላይ የጸደቀ ስምምነት

**እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ጂቲፒ) :-** የኢትዮጵያ መንግስት ሀገሪቷን መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ ሀገራት ደረጃ ለማሳደግ የነደፈዉ የእድገትና ለዉጥ ዕቅድ

## አባሪ 2. የፎቶ ትውስታ

## አባሪ 3. መድረኮቻችን: መረጃዎች

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES' REPRESENTATIVES OF THE FDRE

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሴት ተመራጮች ኮከስ

2013 ዓ.ም